አንደኛ እትም ነሐሴ 2003 ዓ.ም.

የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።

© All Rights Resereved

# አበሻው

ደራሲው፡- ጆን ክሪስቶፍ ሩፈን

ተርጓሚ፡- አያሌው ምትኩ ብሩ

1999 ዓ. ም.

# I

# ከሞት የተረፈው ሰው

## ትዕዛዝ

# 1

በሉዊስ አሥራ አራተኛ የዘይት ቀለም ቅብ ሥዕል የግራ ጉንጭ ላይ፣ በአስፈሪ ግርማ ሞገስ ሰፍቶ በተመልካች ዐይን ውስጥ የሚገባ የተሸራረፈ ጥቁር ጠብታ ታይታያል። በምሥራቁ ዓለም ውስጥ የዘይት ቀለም ቅቦችን እንደቁምጥና በሽታ እየሸራረፈ በመብላት መልካቸውን የሚያበላሸው ነገር፣ ቀስ በቀስ በዚህ ሥዕል ውስጥ በየዕለቱ እየተስፋፋ ነው። የባነ ቡኒ ሽበ የመሰለ፣ ጉልህነት የሌለው አስጠሊታ መስመርም ወደ ጆሮ ግንዱ አቅጣጫ እየተሣበ መሆኑ ይታያል። ቀረብ ብሎ ለሚመረምር ሰው፣ በስዕሉ አካል ላይ ጥቁር አክሲል በተጨማሪ ይመለከታል። በእግር ጣቶቹ ላይ ካሉት ነጠብጣቦች ሌላ፣ የቀረው ሁሉ የሚሰቀጥጥ ነው። በአጭሩ የፀሀዩ ንጉሥ ሥዕል ክፉኛ ተበላሽቷል።

ይህ ሥዕል፣ ካይሮ በሚገኘው የፈረንሣይ ቆንሲል መሥሪያ ቤት ላለፉት ሦስት ዓመቶች ተሰቅሎ ቆይቷል። ሥዕሉ ሲሰራ የራሱ የንጉሡ ግላዊ ቁጥጥርና እይታ አልተለየውም ነበር። ሥዕሉን በመጀመሪያ የሣለው ሂያንዝ ሪጋድ ሲሆን ስፍራውም ፓሪስ በሚገኝ የሥዕል ሥራ ቦታ ውስጥ ነበር። ከዚያም በባህር ወደ ካይሮ ይላካል። እንደመጥፎ ሰድል ሆኖ ካይሮ ውስጥም ይሁን በቅርብ ርቀት በሚገኙ የምሥራቅ ሜዲትራኒያን ጣቢያዎች ሊገኝ የሚችል ታዋቂ ሠዓሊ የለም። በዚህ የተነሣ ቆንሲሉ ሙሴ ዴ ማይሌ፣ በማያስደስቱ ሁለት እኩል ምርጫዎች መካከል ውሣኔ ማድረግ ነበረበት። አንደኛው መጥፎ ምርጫ ይህ በንጉሡ ሥዕል ላይ የሚታየው አስቀያሚ ጠባሣ፣ ሕዝብ እያየው እንዲኖር በመሥሪያ ቤቱ ሕንፃ የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ ተሰቅሎ እንዲቆይ መፍቀድ ነው። ሁለተኛው የማያስደስት አማራጭ ደግሞ፣ ብቁ ሙያ ለሌላቸው እጆች ምስጢሩን ገልጾ መስጠትና ሥዕሉ ፍጹም እንዲበላሽ የማድረግ ዕድል ነው። እንዲህ አጣብቂኝ ውስጥ የከተተውን ምርጫ ቁርጥ ያለ ውሣኔ ሰጥቶ ከመደመደሙ በፊት ዲፕሎማቱ ሙሴ ማይሌ፣ ጉዳዩን እያብሰለሰለ ለሦስት ወራት አቆየው።

ከሦስት ወራት በኋላ የጥገና ሥራውን ለማከናወን ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ካይሮ ውስጥ የሚኖር አንድ መድሃኒት ቀማሚ ግለሰብን መረጠ። ሰውዬው፣ በወቅቱ ካይሮ ውስጥ ከሚኖሩ ፈረንሣዊ ዝርያ ካላቸው መካከል ሲሆን፣ በአየር ጠባይ ምክንያት የተበላሹ የሸራ ላይ ሥዕሎችን የማደስ ችሎታ አለው ተብሎ የሚነገርለት ነው። ግለሰቡ፣ ረዥምና ጉብጥ ያለ ነው። ፊቱ ጥቅጥቅ ባለው በጥቁር ጉብስማ ጢሙ ሣቢያ ወደ ዓይኖቹ ሰርጎድ ብሎ የገባ ይመስላል። የራስ ፀጉሩ ድብን ብሎ የተጠመዘዘ ጥቅል ይመስላል። ግዙፉን ሰውነቱን በተሸከሙት ረዣዥም ቅልጥሞቹ ሲራመድ፣ ያስጠላል። ይህ ሰው በሥራው ላይ በሚሆንበት ጊዜ ግን የሰውነት እንቅስቃሴው ፍፁም የተስተካከለ ነው። ሌሎች ሰዎች ሜትር ዠረሚ በሚባለው ስም ያውቁታል። ሜትር ዠረሚ ታማኝ ዜጋ የመሆኑ ዝና ይነገርለታል። ቆንሲል ዴ ማይሌ፣ የንጉሡን መልክ ለአንድ አክራሪ ፕሮቴስታንት አደራ በማለት የመስጠቱ ሃሣብ አልተዋጠለትም። ምክንያቱም ሰውዬው፣ በአንድ በሆነ ሰዓት ላይ የተስፋ መቁረጥ ሙከራ ሲፈፅም ይችላል። እንዲህ ያለው ባህርይ ደግሞ ቅጥ አምባሩ በጠፋው የካይሮ የውጭ አገር ማህበረሰብ መካከል ብርቅ አይደለም። ነገር ግን ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ሌላ ምርጫ አልነበረውም።

ሜትር ዠረሚ የሥዕሉን ሁኔታ ከተመለከተ በኋላ፣ የማደሱ ሥራ አሥር ቀናት እንደሚፈጅበት ገለፀ። በማግስቱ ከአንድ ኑቢያዊ አገልጋይ ጋር ሰባት ጫማ ከፍታ ባለው የሥራ ክፍል ውስጥ ገባ። ኑቢያዊው ባሪያ፣ ለመድሃኒት መቀመሚያነት የሚውል የአበባ ዘይትና ጥሩ ጠረን የሌለውን የቀለም ማቅጠኛ ቅመም እያደባለቀ እንዲበጠብጥለት ተብሎ ከቆንሲሉ ቤት የመጣ ረዳት ነው። እንዲታደስ በተባለው ሥዕል ላይ የአዳሹ ባለሙያ እጅ ባረፈበት ቁጥር በቦታው መገኘት እንዳለበት ቆንሲል ሙሴ ማይሌ፣ አበክሮ ተናግሯል። ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ሲሆንና የቀለም ቅይጡ ተዘጋጅቶ ሲያበቃ አገልጋዮች ቆንሲል ዴ ማይሌን ይጠሩታል። የተበጠበጠው ቀለም የሚያገለግለው በትክክለኛነቱ ነው። ሙሴ ማይሌ፣ የሥዕሉን እድሣት በቅርብ ለመቆጣጠር በጅማሮው ሰዓት ላይ ይገኛል። ሙሴ ማይሌ፣ የሥዕሉ እድሣት ገና ሲጀመር በጨርቅ ላይ የተንጠባጠበና በጉልህ የሚታይ ሀምራዊ ቀለም ሲመለከት መተቸት ይጀምራል። በጅማሮው ላይ የቀለሙ ወዝ ገና ሣይቀዘቅዝ ሥራው በጣም የሚያበረታታ ነው። ቀለማቱም ሣይበዙ ቁልጭ ብለው ይወጣሉ። በሽራው ላይ በጊዜ ምክንያት የተፈጠሩ እጥፋቶችም ሙሉ በሙሉ ይወገዳሉ። ይህን ሁሉ ሲመለከት ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ተስፋው ይለመልማል። ነገር ግን ሜትር ዠረሚ የቀለም ብሩሹን ወደንጉሡ ሥዕል ባቀረበ ቁጥር፣ በጥርስ ሃኪም ወንበር ላይ ተቀምጦ መቆንጠጫ ጉጠቱን በተመለከተ ቁጥር እየተሣቀቀ እንደሚያፋሽግ ሕመምተኛ በማከታተል ያዛጋል። በዚህ ሣቢያ ሥራው ብዙ ጊዜ ይቋረጣል።

በመጨረሻው ላይ የንጉሡን ጉንጭ መዝምዘት የነበረው ነቀርሣ የሚታደስበት ሰዓት ደረሰ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ቀለል ያለ ነጭ ጋዋኑን ለብሶ በሥዕሉ ፊት እንዲደረግለት ባዘዘው አነስተኛ አግዳሚ ላይ በጭንቀት ተቀምጧል። ባለቤቱ፣ የባሏን እጆች በጡቶቿዋ ላይ ጫን አድርጋ ከአጠገቡ ተቀምጣለች። ሁለቱ ጥንዶች እንደዚያ ተቀምጠው ሲታዩ እጅግ የሚወዱት ሰው ሲሰቀል በጭንቀት እንደሚመለከት የቤተሰብ ቡድን፣ ሽቅብ እየተቁለጨለጉ የሚመለከቱት ይመስላሉ። በወርሃ ግንቦት ከሰዓት በኋላ በሚኖረው አጋማሽ ጊዜ ላይ፣ ከኑቢያ በረሃ የተነሣው ሞቃታማ ነፋስ ከተማዋን ለሦስት ቀናት በደረቅ ሙቀት እያነፈራት ነው። ሜትር ዠረሚ፣ የተደፋ ጀልባ የመሰለ ቆብ ጭንቅላቱ ላይ ካጠለቀ በኋላ አገልጋዩ የማለስለሻ ብሩሽ አቀበለው። ዠረሚ፣ ብሩሹን በባለግርማ ሞገሱ የንጉሡ ፊት ላይ አነጣጠረ። ይህን ጊዜ ሙሴ ዴ ማይሌ ከአግዳሚው ላይ ብድግ አለ።

*«ቆይ!»*

*መድሃኒት ቀማሚው በመደነቅ ቆመ።*

*«ይህን ለመሥራት ሙሉ በሙሉ እርግጠኛነቱ . . . ?»*

«እምን፣ ክቡር ሆይ»

ሜትር ዠረሚ በፊቱ ላይ የታየበትን ሁኔታ የሚመስል ስሜት አንፀባረቀ። ቁጣውና ግልፍተኛነቱን ሲያወጣው ሲል እንደምንም ብሎ ራሱን ገታ። ይህ ጥረቱ ግን በፊቱ ላይ ይታወቅበት ነበር። የማትረምረም ትንፋሽ ሲወጣው፣ በጣም የፈላ የማንቆርቆሪያ ውሃ የሚያሰማው ዓይነት ቀጭን ፉጨት ወጣው። ይህም ቢሆን ፈንድቶ አላፈተለከም። እጅግ ቢበሣጭም ቀማሚው በጨዋ ትዕግስት አግራሞቱን ገለፀ።



«አሁን ለማድረግ የሞከርኩት የላይኛውን ክፍል በስሱ ነካ ለማድረግ ነው። ቡሩሹ ሽራውን ለዓመል ያህል መንካቱን ሊያስተውሉ ይችላሉ፣ ክቡር ሆይ» ሲል ቀማሚው ገለፀ።

ሥራውን የመወሰን መብት ለሜትር ዠረሚ ተትቶለት ቢሆን ኖሮ፣ የሉዊስ አሥራ አራተኛን አፍንጫ በደማቅ ቀይ ቀለም ሁለት እጥፍ ያሳድገው ነበር። ጆሮዎቹንም ከአርቲፊሻል ፀጉሩ ጋር የተጫጫሩ የውሻ ጆሮዎች ያስመስላቸው ነበር። እንደፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች እርሱና መላው ቤተሰቡ በዚህ ንጉሥ እጅ ሥቃይ ደርሶባቸዋል። እርሱንም ቢሆን ሌሎች ሊገነዘቡት ከሚችሉት በላቀ መልክ በድሎታል። የዕለቱ ፕሮግራም ያለአንዳች ክንዋኔ ቢጠናቀቅም ሁሉንም ሥራ ገሃነም ይግባ ለማለት ሜትር ዠረሚ ለመጀመሪያ ጊዜ ለራሱ ቃል ገብቶ ነበር።

ቆንሲሉ፣ በዚህ ሥዕል አዳሽ ብሩህ እይታ ውስጥ ምናልባት ሊመለከት የቻለው ታላቅ ነገር ስላለ ይመስላል አግዳሚው ወንበር ላይ ተመልሶ ዘጭ ካለ በኋላ «ማድረግ ካለብህ እንግዲያው ቀጥል» ሲል ተናገረ።

ዠረሚ የሁለቱንም እጆቹን ጣቶች በጥርሶቹ መሃል ነክሶ ዐይኖቹን ጭፍን አደረጋቸው።

በዚያው ቅፅበት ከባድ የማንኳኳት ድምፅ በበሩ መዝጊያ ላይ ሁለት ጊዜ ተሰማ። ሠዓሊው ወደኋላው ፈቅ አለ። ሱዳናዊው አገልጋይ ትላልቅ ዐይኖቹን ወደ ሰማይ አቀናቸው። ሙሴ ዴ ማይሌ በስሜት የቀሉትን እይኖቹን በለጠጣቸው። ሥጋትና ጭንቀት የተሞላው ፀጥታ በክፍሉ ውስጥ ነገሠ።

በድጋሚ ሦስት ማንኳኳቶች በበሩ ላይ ተሰሙ። እነዚህኞቹ ምቶች ከቀድሞ ይልቅ ከበድ ያሉ ናቸው። ሥዕሉ በሚታደስበት ጊዜ ፈፅሞ ሁከት እንዳይሰማቸው በግልፅና በተደጋጋሚ ቆንሲሉ ራሱ የሰጠውን ጠንካራ መመሪያ ጥሶ ወደ አዳራሹና ወደ ቢሮው የሚያመራውን ትልቁን በር እንዲህ ለማንኳኳት ነፃነቱን የወሰደው ሰው የሚያጠራጥር አይደለም። ዲፕሎማቱ፣ የለበሰው ጋዋን በሚገባ መቆለፉን ካረጋገጠ በኋላ ፈጠን ብሎ በመራመድ በሩን በርግዶ ከፈተው። በበሩ ፊት ሙሴ ማቼ ቆሟል። በአሰቃው የቁጣ አተያይ ሣቢያ ፈጠን ብሎ ከወገቡ ጐንበስ በማለት ታዛዥነቱን ለመግለፅ ሞከረ።

«የጃኒሣሪዎች አጋ ለክቡርነትዎ መልዕክት ልከዋል። አበክረው እንዳስገነዘቡት ከሆነ ጉዳዩ ያልተለመደና አስቸኳይ ነው። በምንም ዓይነት ሁኔታ በዚህ ሥራ ላይ ባሉበት ጊዜ እንዳይረበሹ የሰጡትን ትዕዛዝ መዘንጋት ባይኖርብኝም፣ ሊዘገይ ለማይችል ጉዳይ ቱርኮች የተለየ እንሳለፅ ስላላቸው መመሪያዎን ችላ አልኩ።»

ማቼ፣ ፓሪስ ከሚገኘው የምሥራቃውያን ቋንቋዎች ትምህርት ቤት የተመረቀ ሰው ነው። ስለዚህም «የቋንቋ ሰው» በመባል ይታወቃል። የዚህ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ዲፕሎማቸውን ከተቀበሉ በኋላ፣ ዲፕሎማት ከመሆናቸው በፊት ወደ አንድ ኤምባሲ ይላካሉ። ሙሴ ማቼም ያጋጠመው ይኸው ነው። ዋናው ቆንሲል፣ ለወጣቱ ማቼ የተለየ አመለካከት አለው። ማቼ፣ ዋናውን ቆንሲል ሊያረካው በሚችል መልክ ደረጃውንና አቅሙን የሚያውቅ ሰው ነው። ሙሴ ማቼ፣ ከጨዋ ቤተሰብ በመወለዱ ሳይሆን በሚያጋጥሙት ጥያቄዎች ሁሉ ላይ የራሱን ገደብና ብልህነቱንም የሚያሣይ ሰው ነው።

«ለመሆኑ እንዳች ደብዳቤ አለ?»

«የለም ክቡር ሆይ። የኢጋው መልዕክተኛ ከፈረሱ ላይ እንኳን ሳይወርድ ነው ጌታው፣እርስዎን በቤታቸው ሆነው እየጠበቁዎት መሆናቸውን ብቻ የነገረን።»

«እና እነዚህ ውሾች፣ ስብሰባ እየጠሩኝ መሆኑ ነው፣ አይደል? ለዚህ ጥሩና በቂ ምክንያት ሊኖራቸው እንደሚችል ተስፋ አደርጋለሁ። ይህም ካልሆነ፣ ፓሻው ራሱ በሰሁኔታው መስማቱ አይቀርም» ሲል ድምፁን ዝቅ አድርጐ ሙሴ ማይሴ ተናገረ።

ሙሴ ማቼ፣ በተረከዙ እንደመሽከርከር ብሎ፣ ከቆንሲሉ ጋር ትክሻ ለትከሻ ለመነካካት በሚያስችለው ቅርበት ተጠጋው። ሁለቱ ሰዎች በክፍሉ ውስጥ ለነበሩት ሰዎች ጀርባቸውን ሰጥተው ቆሙ። ወጣቱ ማቼ፣ የመንግስትን ምስጢር በአደባባይ እንደሚያውጅ ዓይነት በማንሾካሾክ ተናገረ። እንዲህ ያለው የዲፕሎማቶች ሥራ የመልካም ሥርዓት መገለጫ ቢመስልም የማታለያ ስለሆነ ሲለመድ ተጨማሪ ባህርይ ይሆናል። በዚህ አጉል ባህርይ ቅር በመሰኘት ሜትር ዠረሚ ትክሻውን ሰበቀ።

«እጋው፣ ክቡርነትዎ በፈለጉት ጊዜ ሊጠቀሙበት የሚችሉትን አንድ ፈረንሣዊ ሰው ትናንት ካይሮ ከተማ ውስጥ አስረዋል» ሲል ሙሴ ማቼ አንሾካሾከ።

«ታዲያ ይህም ምክንያት ሆኖ ሥራችንን ማወክና ማቋረጥ አለበት?, ዕድል ፊንታቸውን ለመሞከር ወደዚህ ከሚመጡት አሣዛኝ ምስኪኖች መካከል በየሣምንቱ አንዱን ይይዛሉና፣ ሥራ ያስፈቱናል? ቢሆንስ እኔን ምን የሚመለከተኝ ነው?»

«ብቻ... » በማለት ሙሴ ዴ ማቼ፣ ከበፊቱም ይልቅ በጣም ዝቅ ባለ ድምፅ አጉረመረመ። ቆንሲሉ የሙሴ ዴ ማቼን ንግግር ለመለየት የከንፈሮቹን እንቅስቃሴ መከታተልና ማንበብ ነበረበት። «ሰውዬው ማንም ተራ እስረኛ አይደለም። እንዲያውም እስከሁን የምንጠብቀው የንጉሡ መልዕክተኛ ነው» ሲል ተናገረ።

ሙሴ ዴ ማይሴ የድንጋጤ ድምፅ አሰማ።

«እንዲህ ነው እንዴ? ጌቶቼ! እንግዲያውማ ጊዜ ማጥፋት የለብንም። የዛሬው ፕሮግራማችን እዚህ ላይ ያበቃል» ሲል ሜትር ዠረሚ እንዲሰማው በማሰብ ጐላ ባለ ድምፅ ተናገረ

ቆንሲሉ፣ ክፍሉን ለቅቆ ሲወጣ የተደበላለቀ ስሜት በፊቱ ላይ ይነበብበት ነበር። የክብርና ያለመደሰት ስሜቶች ይታዩበት ነበር። በውስጣዊ ስሜቱ ግን ሲገጥመው ከሚችለው ሥቃይ የሚገላግለው ማንኛውም ነገር ቢሆን የተሻለ እንደሆነ እርግጠኛ ነበር።

ሜትር ዠረሚ፣ ከወጣቱ አገልጋይ ጋር በመሆን እየማለና እየተገዘተ የሥዕል ቡሩሹን ወደ ብልቃጡ ውስጥ ወረወረው። በዚህን ጊዜ ለንጉሡ የሥዕል ጉንጭ ሲባል ከተዘጋጀው ውድ ሃምራዊ ቀለም ውስጥ ብዙ ፍንጥቅጣቂዎች በጥቁሩ ልጅ ጥቁር ግንባር ላይ ተረፓበት።

በዚያን ዘመን፣ ጥሩ ገስጋሽ የካይሮን ከተማ በሶስት ሰዓታት ውስጥ መዞር ይችላል። ከተማዋ ገና ትንሽ ብትሆንም፣ አገር ጐብኚዎች ግን በደምሣሣው አስቀያሚ፣ ጐስቋላና የማትማርክ የሚሏት ነበረች።ጠባቦቹን መንገዶችዋን ተከትሎ ወደ ከተማዋ እምብርት ዘልቆ



የሚገባ ሰው እይታውን የሚጋርድበት ባለሁለት ፎቅ ድርድሮች ይገጥሙታል። በጉዳናዎቹ አናት ላይ እንግዳ ተንገሮችን የሚያስፈሩ ባለቀይ ቀለም ሹል ቅጠሎች ካሉዋቸው ረገኸርም ትርንጫፎች በስተቀር የተጊያጊያጠ ነገር አይታይም። በከተማዋ ውስጥ ጐላ ብለው የሚታዩት ሕንፃዎች የቤዮች ቤተመንግስት፣ በአንድ አቅጣጫ ወደሩማይላ አደባባይ ሲል ክፍት ከሆነው የፈርኦኖች መኖሪያ ከነበረው ግንብና ከብዙ መስጊዶች በስተቀር የለም። በዚህ ምስቅልቅል ውስጥ ሁሉም ነገር ለዓይን አይሞላም። ከተማዋ ውበትን ሁሉ ገፍትራ ስሚት የማትስብ ናት። ደስታና ፍቅርም ከአናዎቹ የሕንፃ ግድግዳዎችዋና ከጥቋቁሮቹ የመግቢያ በሮችዋ በስተጀርባ የቀሩ ይመስላል። ከአጉራባች የባላገር መንደሮች ከሚመጡ ነጋዴዎች በስተቀር በዋና ዋና ጉዳናዎችዋ ውስጥ የሚዘዋወሩ ሰዎች ጥቂቶች ናቸው።

እንግዳ ሰው፣ በካይሮ ነዋር ሰፈሮች ውስጥ እምብዛም ደፍሮ አይገዝም። በአሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ በኦቶማን ቱርክ፣ ሡልጣን በነበረው በካየር አድ ዲን ባርባሮሣና በፈረንሣይ መካከል ስምምነት ተደርሷል። ይህ ስምምነት ከድል በኋላ የተደረገ ነበር። በስምምነቱ መሠረት አውሮፓውያን በነፃነት የመነገድና የተወሰኑ መብቶችን አግኝተዋል። ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች ስጋት እንደገባቸው ይኖራሉ። በሌላ በኩል ግብፃውያኑ ባለማቋረጥ እርስ በርሣቸው እንደተጣሉ ናቸው። ስምምነቱና ግቡቡነቱ የተገባቢጦሽ ካልሆነ በስተቀር፣ ፓሻው በራሱ ታጣቂ ሚሊሺያዎች ወደመቃብሩ ይወርዳል። የክብር ዘበኞች ከአገረ ገዥዎች ጋር ፀበኞች ናቸው። አገረ ገዢዎች ከኢማሞች ጋር አይስማሙም። ኢማሞች ከፓሻዎች ጋር አይጣጣሙም። በዚህ ስምምነት ሳቢያ ፈረንሣውያን ነፃ ቢሆኑም በተቻለ መጠን ከተወሰነላቸው አካባቢ እንዳይርቁ አጥብቀው ይጠነቀቃሉ።

በዚያን እለት፣ ያ ወጣት በነዚያ ጠባብ የካይሮ ጐዳናዎች እንደዚያ ተዝናንቶ የመጓዙ ነገር በጣም የሚገርም ነበር። ወጣቱ፣ ከአንድ ተራ የአረብ ቤት ሲወጣ ደካማውን የሣንቃ በር ወደ ኋላው ወርውሮ በመዝጋት ነበር ወደ ጐዳናው ውስጥ የገባው። መውጫውና መግቢያው በማይታወቀው በካይሮ ውስብስብ ጐዳና ውስጥ አቅጣጫውን ይዞ ሲጓዝ እንደአገሬው ሰው ማይባደፍ ነው። ይህም ሆኖ ፈረንሳዊነቱ በግልፅ ያስታውቃል። እርሱም ቢሆን ባዕድነቱን ለመደበቅ አልተጨነቀም። ከማለዳው ጀምሮ ከሃምሲን ተብሎ የሚጠራው ነፋስ፣ የአሸዋ አቧራ ትንፋሹን ከበረሃው ወደ ከተማው ይረጫል። ወጣቱ ከሴታው ክፍት የሆነ ከናይለንና ከጥጥ ቅይጥ የተሠራ ቀላል ሸሚዝ ለብሷል። ሱሪውም ከጥጥ ጨርቅ የተሠራ ባተሁለት ሆኖ ጉርድና በቀላሉ የሚተጣጠፍ ጫማ ተጫምቷል። በጭንቅላቱ ላይ ግን ምንም አላደረገም። የባህር ሃይል የሱፍ ጃኬቱን በክንዱ ላይ አንጠልጥሏል። እየተጓዘ ሣለ፣ ከሐሰን መስጊድ ፊት ለፊት ሁለት አረቦች መንገድ እያቋረጡ ገጠሙት። ወዳጅነትና ፈገግታ የተሞላበት ሠላምታ ሰጡት። እርሱም አፀፋውን በአረብኛ ቋንቋ በአንድ ቃል መልሶላቸው መንገዱን ቀጠለ። ይህ ወጣት ቱርካዊ ባለመሆኑ በምንም መልክ ባለሥልጣን አይደለም። ነገር ግን በከተማው ውስጥ የሚኖር እያንዳንዱ ሰው፣ ይህ ወጣት፣ ጆን ባፕቲስት ፖንሴ የሚባል መሆኑንና በፓሻው ጠንካራ የመኖሪያ ምሽግ ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ እንዳለው ያውቃል።

ጆን ባፕቲስት ፖንሴ ጥሰቅ ያለ፣ ወንዳ ወንድና ጠንካራ ሰውነት ያለው ነው። ቁመናው መለሎ፣ ደረቱ ሰፊና ጫንቃውም ደንደሣም ነው። ይህን እርሱም ያውቃል። እንዲያውም በዚህ ቁመናው ሳቢያ የአርባ ቀን ዕድሉ ለምን በፀሃዩ ንጉሥ አጠገብ ለጀልባቸው ቀዛፊነት እንዲመለመል እንዳላደረገው ራሱን ይጠይቃል። የራስ ቅሉ በጠንካራው ደንደሱ ላይ በማይገመት ሁኔታ የተተከለና ረዘም ብሎ ጥሩ ቅርፅ ያለው ነው። የፊቱ ገፅታም ቢሆን

ለስለስ ያለና ወጣትነት የሚታይበት ነው። ጥቁሩ የራስ ፀጉሩ ፊቱን እንደከፈፍ ይከብበዋል። ዛጉልማ ዓይኖቹ ከመሀል ሆነው ብርሃን የሚፈልቅባቸው ይመስላሉ። ነገር ግን የፊቱ ገፅታ ተስተካክሎ ያልተሰራ መሆኑን ማስተዋል አያቅትም። የአንደኛው አገጩ አጥንት ከሌላኛው ይልቅ በመጠኑ ከፍ ያለ ነው። የዓይኖቹ አቀማመጥ ለማስደንገጥ ሲባል የተቀመጡ ይመስላሉ። በዚህም ለአተያዩ ግርማ ይሰጡታል። እነዚህ ወጥነት የሌላቸው ቅርጾቹ በዚያ ቁመናው ላይ አንዳች ምስጢራዊ ሃይል ያለው ያስመስሉታል።

በግንቦት ወር ላይ ሃያ ስምንተኛ ዓመቱን የሚይዘው ጆን ባፕቲስት ፖንሴ፣ ካይሮ በቆየባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ እጅግ በጣም የታወቀ ሃኪም ሆኗል።

በጉዳናው መሃል ሲጓዝ፣ በእጁ የያዛትን አንዲት ትንሽ ሣጥን ወደ ፊትና ወደ ኋላ ያወዛውዛታል። ሣጥኗ፣ በሸርከኛው ርዳታ ራሱ ቀምሞ ባዘጋጃቸው ልዩ ልዩ መድሃኒቶች የተሞላች ነች። በሣጥኗ ውስጥ ያሉት የመድሃኒት ብልቃጦች ርስበርሳቸው ሲጋጭ የታፈነ ቅጭልጭልታ ያሰማሉ። የእርምጃውን እንቅስቃሴ ተከትለው ከነዚያ የመስታወት ብልቃጦች ወጥተው እንዲሰሙ በሚያደርጋቸው ዜማዊ ቅጭልጭልታዎች፣ ወጣቱ ፖንሴ ደስተኛ ነው። ምንም እንኳ ከየመስኮቶቻቸው መጋረጃና ከእንጨት ርብራብ ሣንቃዎቻቸው ጀርባ ተከልለው የሚከታተሉት ሰዎች እንዳሉ ቢያውቅም፣ በዚህ ሣይረበሽ በፈገግታና በሰላማዊ ስሜት ወደፊት እየተመለከተ ይራመዳል። ከነዚህ ቤቶች መካከል ብዙዎቹን ያውቃቸዋል። በብዙዎቹ ቤቶች ውስጥ የህክምና አገልግሎቱን ሰጥቷል፣ ወይም ለሻይና ለእራት ግብዣ ተጠርቶ ተስተናግዶባቸዋል። የከተማዋን ሰፊ አካል ጥቂት፣ የትንሹን አካልዋን ደግሞ ብዙ ሚስጥሮችን በሚገባ ያውቃል። አጠቃላይ ነገሮችን ለማወቅ ባለው ከፍተኛ ጉጉት የተነሣ በተለይም የወሲብ ፍላጐት ስሜትና ሴራ፣ በጨለማው ውስጥ የሚነሣሱበትንና የሚነግሱብትን የሴቶች ጉዳይ ያውቃል። እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን በፍቅር ስሜትም ይሁን በግብዝነት ሣይደነቅ የተቀበላቸው ናቸው። በውስጣቸውም ጭልጥ ብሎ በመግባቱ ወይም የርሱ ሀርይ ስለሆነ ያለይሉኝታ ቀጥሎባቸዋል። ድርጊቱ ሁሉ አገርና አካባቢን የማያውቅ፣ የሚቃብዝ እንስሳ የሚያደርገው ይመስላል። እንዲህ ባለ ተንከራታች እንስሳ ላይ የብዙ ሺህ ስልጡን አዳኞች አይኖች፣ እያንዳንዷን እንቅስቃሴውንና ዱካውን እንደሚከታተሉ ያውቃል። ይህም ሆኖ ቀጥሎባቸዋል።

ጉዞውን በመቀጠል በአንድ የሾቶ ሱቅ አጠገብ አልፎ በመጨረሻው ክሃሊኘ ወይም የካይሮ ቦይ በተባለው ዳርቻ ደረሰ። የትንሿን ምንጭ የፍሰት አቅጣጫ ተከትሎ ለጥቂት ጊዜ ሽቅብ ተጓዘ። ይህ ቦታ በዚህ ወቅት ደረቅ ነው። ማዕበል ሲጀምር ግን ሲያነፍር የሚችል ሃያል ትንፋሹን ይለቀዋል። ፖንሴ፣ በዝግታ ተጠማዝዞ ድልድዩን ለማቋረጥ ተጓዘ። ቦታው ሁልጊዜም በሰዎች እንደተሞላ ነው። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ አንድም በአካባቢው ያሉት ሱቆችና ቤቶች ድልድዩን ተከትለው የተሰሩ ስለሆነ ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ በአሮጌው ካይሮና በአረቦች መኖሪያ መካከል ያለው ብቸኛው መተላለፊያ መስመር ይኸው በመሆኑ ነው። በዚህ ዕለት ግን የሕዝቡ ብዛት ከወትሮው እጅግ ይልቃል። ጆን ባፖቲስት ፖንሴ በመከራ እየተጋፋ ይጓዛል። ድልድዩ መካከል ሲደርስ ግን፣ አንዳች ያልተለመደ ክስተት እንዳለ ተገነዘበ። ከቤቶቹ መካከል ከአንዱ ውስጥ ወፍራም ጥቁር ደመና እየተግተለተለ ይወጣል። እሣቱ፣ ከአንድ የጨርቃ ጨርቅ ነጋዴ ሱቅ ውስጥ የነበረ የሸክላ ምድጃ ሲደፋ፣ የተያያዘው ከሰል በመረጨቱ እንደተቀጣጠለ ሲያወሩ ሰማ። ብዛት ያላቸው ግብፃውያን በቅርባቸው ከሚገኝ የጉድጓድ ውሃ በባልዲ በመቅዳት እየሮጡና እየተጣደፉ በእሣቱና በሚጨሰው ቤት ላይ



ይረጫሉ። እሣቱ በቁጥጥር ሥር በመዋሉ የከፋ ጉዳት አላደረሰም። ይሁን እንጂ እንዲህ ባለ መንደር አንዳች ትንሽ ነገር በተከሰተ ቁጥር ሰዎች ከየአቅጣጫው እየጐረፉ ለመመልከት ስለሚሰባሰቡ መጨናነቁ የግድ ነው። በዚህ የተነሣ ከድልድዩ ማዶ መሄድ አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን ጆን ባፕቲስት ፖንሴ እየተጋፋ ወደፊት ይራመዳል። ራቅ ብሎ፣ እርሱ ከመጣበት አቅጣጫ ወደ ድልድዩ መግቢያ ላይ በጭንቅንቁ መካከል በሁለት ፈረሶች የሚሣብ ጋሪ ከጉዞው ተገትቷል። ሲመለከተው የፈረንሣይ ቆንሲል ምልክት ያረፈበት ጋሪ መሆኑን ለየ። ይህን ጊዜ፣ ትዕይንቱን እንደ ጆል ፈዝዘው የሚመለከቱትን ሰዎች እባካችሁ አሳልፉኝ ብሎ እየጠየቀና እየለመነ ከመቆየት ይልቅ በትከሻው እየሰቀሰቀና በጉልበቱ እየተጋፋ ቀረበ።

ምንም እንኳ በመድሃኒት አዋቂነት የተመዘገበ ቢሆንም፣ ፖንሴ ምንም ዓይነት የህክምና ሙያ ዲፕሎማ አልነበረውም። በዚህ ሣቢያ የህክምና ተግባሩ ሁሉ ህገወጥ ነው። በጉዳዩ ላይ ቱርኮች ምንም ዓይነት ተቃውሞ አያነሱም። የሚቃወሙትና በተጠያቂነት የሚወነጅሉት የራሱ አገር ሰዎች ናቸው። በተለይም ሙያዊ የምሥክር ወረቀት ያለው ሃኪም በመሃከላቸው ከተገኘማ አያላውሱትም። እንደዕድል ሆኖ በዚህ ወቅት ካይሮ ውስጥ ሌላ ሐኪም አልነበረም። የራሱ አገር ሰዎች በተደጋጋሚ ስሙን ሊያጠፉ ሞክረዋል። እርሱም ይህን በመፍራት ከዚህ ቀደም ሁለት ከተሞችን ለቅቶ ለመውጣት ተገዷል። ከሕግ አስከባሪ ሃይሎች ዓይን መራቅ ማለት በራሱ አርቆ አስተዋይነት መሆኑን ይረዳል። ሕጉ፣ ፈረንሣውያንን በተመለከተ ከሆነ ሃላፊው ቆንሲሉ ነው።

ጋሪውን በማለፍ ላይ እያለ ጭንቅላቱን ወደ ትክሻው ዘንበል በማድረጉ ፊቱ በከፊል ይታያል። በመሃሉ አንድ በኩራትና በልበሙሉነት አቤት እንዲል የሚያስገድደው ድምፅ በጥሪ ገታው። «ጌታው እባክህ . . . ጥቂት ጊዜህን ልትሰጠን ትችላለህ?»

ጆን ባፕቲስት፣ ቆንሲሉ ቢሆን በማለት ፈርቶ ነበር። ነገር ግን እንደ እድል ሆኖ የጠራውና የገታው ድምፅ የሴት ነበር። ጋሪው ዘንድ ሲደርስ አንዲት እመቤት በጋሪው መስኮት በኩል ጭንቅላቷን ዝቅ አድርጋ አወጣች። መስኮቶቹ ሁሉ በተዘጉበት ጋሪ ውስጥ በነበረው ሙቀት ሳቢያ በላብ ተጠምቃለች። ላቧ ቁልቁል በመፍሰሱ ጉንጮችዋን የተቀባችው ቀለት ታጥቧል። በዚህ የተነሣ ፊቷ አሸቦ በመምሰል መሸብሸብ ጀምሯል። ይሁንና የጊዜን ርዝመት ለመደበቅ ራሷን በራሷ እየኳኳለች የተጊያጊያጠችባቸውና የሰዎችን ዓይኖች የሞኙታታልልባቸው ጌጦችዋ ፊቷን ይበልጥ አጥምቀውታል። እየተንጠባጠበ ያለውን የፊትዋን ቀለት በመጥረግ ፈገግታ አቀረበች።

«ሠረገላችን እንዳይፈጥን ያደረገው ጉዳይ ምን እንደሆነ ልትነግረን ትችላለህ? ለመሆኑ በአደጋ ውስጥ ነን እንዴ?»

ጆን ባፕቲስት፣ የቆንሲሉን ባለቤት በአንድ ጊዜ ለይቶ አወቃት። ከዚህ ቀደም አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ያህል በፈረንሣይ ለጋሲዮን የአትክልት ሥፍራ አይቷታል።

«ተመልካቾችን የሰበሰባቸው ከቤቶቹ አንዱ በእሣት ተያይዞ ነው። ሆኖም ሁሉም ነገር በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ተለመደው ሠላማዊ ሁኔታ ይመለሣል»

የቆንስሉ ባለቤት እፎይታ ማግኘቷን ገልፃ፣ ጆን ባፕቲስትን አመስግና፣ ጭንቅላቷን መልሣ ወደ ጋሪው ውስጥ በማስገባት በተደላደለው መከዳ ላይ ተዝናንታ ተቀመጠች። ወዲያውም የንፋስ ማራገቢያውን ማወዛወዝ ቀጠለች። በዚህን ጊዜ ሴትየዋ ብቻዋን እንዳልሆነች ጆን ባፕቲስት ተገነዘበ። ከሴትዮዋ ጐን በዳር በኩል፣ በክሃሊጁ ወይም በካይሮ ቦይ ማቢያ አግድሞሽ በመጣው በፀሃይ ብርሃን ጨረር ደምቃ የምትታይ ወጣት ልጃገረድ ሠረገላው ውስጥ ተቀምጣለች።

የአንዱ እንከን የሌላውን ፀጋና ውበት ይደብቀዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሁለቱ ሴቶች ሲታዩ ፍፁም ተቃራኒዎች ነበሩ። በአሮጊቷ እመቤት ፊት ላይ የተጋገረው የኮስሞቲክስ ቅራፊ፣ በወጣቷ ፊት ላይ ከሚታየው ፅዱ ገፅ ጋር በተነፃፃሪነት የሚታይ ነው። የአሮጊቷ ቁንጥንጥ ስጋት ከወጣቷ ርጋታና ዘና ማለት ጋር ተቃራኒ ነው። ጆን ባፕቲስት እንዲገልፃት ቢጠየቅ ምን ብሎ እንደሚጀምር አያውቅም። ወጣቷ የተንጠለጠለውን ፀጉርዋን በሰማያዊ የሃር ሪቫን ቋጥራዋለች። ጆን ባፕቲስት፣ ወጣቷን ቀንጆ በመደነቅ ተመለከታት። ምንም እንኳን በባህሪው ረጋ ያለ ቢሆንም በዚህ አድናቆቱ ራሱን ማረጋጋት ተሣነው። ጋሪ ነጅው አሰንጋውን ሲያጮኸው ሠረገላው ወደፊት ተንቀሣቀሠ። በሁለቱም ዓይኖች ውስጥ የነበረው የፀጥታና የዝምታ ንግግር ተቋረጠ። ጆን ባፕቲስት መናገር ተስኖት፣ ግራ ገብቶት፣ ግን ደስ ብሎት ብቻውን ድልድዩ ላይ ቆሞ ቀረ።

«ያበሳጫል! እንዲህች ያለች ሴት ካይሮ ውስጥ ከዚህ በፊት አይቼ አላውቅም» ሲል ለራሱ ተናገረ።



# 2

ሙሴ ዴ ማይሌ የተወለደው፣ ዝቅተኛ ከሆነ አንድ የመሣፍንት ወገን በምሥራቅ ፈረንሣይ ዉስጥ ነው። ቤተሰቡ በርግጥ አሁንም እንጥፍጣፊ ሃብት አለው። በአጠቃላይ ከመጀመሪያውኑ መነሻ ሃብት ስላልነበራቸው ጨርሶ ድህነት ውስጥ ገብተዋል ብሎ መደምደሙ ተገቢ አይሆንም። በአንድ በኩል እያደገ በመጣው የከበርቴው መደብ፣ በሌላው በኩል በከበርቴ ገበሬዎች እየተከበበ ያለው ይህ የመኳንንት ቤተሰብ አንዳችም የሚሠራው ወይም በይዞታነት ያለው ምንም ባይኖረውም ተደሣች ነው። ከሌላው ጋር ራሣቸውን እንዳያወዳድሩና ዝቅ እንዳይሉ ያደረጋቸው እነርሱ የመሣፍንት ወገኖች መሆናቸው ነው። ከዚህ ሁሉ እንደሚወጡና አንድ ቀን ደህንነት እንደሚመጣ ቅንጣት አይጠራጠሩም። ምን ያህል የትውልድ ሃረግ ርቀት ይኑራቸው፣ ብቻ ከዘራቸው አንዱ ከፍ ካለ ደረጃ ከደረሰ /ይህ ደግሞ አንድ ቀን ይሆናል/፣ እነርሱ ሁሉ ከወደቁበት ቀና ይላሉ። ይሁን እንጂ ይህን ተስፋቸውን እውን የሚያደርግ ተአምር ወዲያውኑ አልታየም። ነገር ግን የእናታቸው የመጀመሪያው የአጐት ልጅ የሆነው ሉዊስ ፖንቻርትሬይን፣ የዐፃዩ ንጉሥ ሚኒስቴርና በኋላም ጠቅላይ ሚኒስቴር ሲሆን ለረዥም ጊዜ ሲጠብቁት የነበረው ሁኔታ እውን ሆነላቸው። ማንም ሰው በራሱ ችሎታም እንኳ ቢሆን አገኘው ቢባል፣ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ግን ያለደጋፊ አይሆንለትም። ፖንቻርትሬይን እዚህ ደረጃ ሊደርስ የቻለው የርሱ የሆኑ ብዙ ሰዎች በየቦታው ስለነበሩት ነው። እነዚህን ሰዎች በየቦታው ያስቀመጣቸውና የሚጠብቃቸው እርሱ ነበር። በዚህም ማቢያ በአንድ አጋጣሚ እነርሱም ውለታውን ይከፍሉታል። ፖንቻርትሬይን ይህን ስለሚያውቅ ቤተሰቡን መጥቀምን አልዘነጋውም።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ በአክራሪ ሃይማኖተኛነት ውስጥ የተገኘ፣ ከመፃህፍትም ሆነ ከሕይወት ተሞክሮ ምንም የሚያውቀው ያልነበረው ወጣት ነበር። ከዚህ ባዶነቱ በማዳን ካይሮ ውስጥ የቆንሲልነት ሥራ ያገኘለት ጠንካራው አጎቱ ነበር።

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የአጐቱ ውለታ ቢኖርበትም ቅሉ፣ እርሱም ስለመጭው ጊዜ ብርቱ ፍርሃት ነበረው። የአጐቱን ውለታ በራሱ ጥረት ብቻ ሊከፍል እንደማይችል ያውቃል። ይህ ታላቅ ሥልጣን ያለው አጐቱ፣ ምናልባት አንድ ቀን በተራው ውለታ ይጠይቀው ይሆናል። አጐቱ የሚጠይቀው ውለታ፣ ምናልባት ሙሴ ዴ ማይሌ ራሱን ለአደጋ ሣያጋልጥ የማይገኝ ይሆን ይሆናል።

ካይሮ የሚገኘው የቆንሲላ ጽሕፈት ቤት፣ በምሥራቅ ሜዲቴራኒያን ውስጥ ካሉት ሁሉ የሚያስቀና ቦታ ነው። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ተጠሪነቱና ሪፖርት የሚያደርገው ኮንስታንቲኖፕል ለሚገኘው የፈረንሣይ ኤምባሲ ነው። ይህ ደግሞ ትንሽ ራቅ የሚል ሥፍራ ነው። የቆንሲል ጽሕፈት ቤቱ የሚያከናውነው ተግባር በካይሮ የውጭ አገር ነዋሪዎች መንደር ውስጥ ችግር ፈጣሪ የሆኑ ጥቂት ነጋዴዎችንና ጆብደኞችን በተመለከተ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማውጣትና ተቀባይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። እነዚህ ሰዎች ባልተለመዱ ተከታታይ ሁኔታዎች ሳቢያ ያለ ዕርዳታና ድጋፍ መውጫው ጠፍቷቸው

ወደአገራቸው መመለስ ባለመቻላቸው እንደወጡ የቀሩ ናቸው። በድፍረት የሚሠሩትን እንደ ፀጋ ይቆጥሩታል። ገንዘብን እንደ ሃይል ምንጭ ያስቡታል። በስደት የቆዩበትን የዘመን ርዝማኔ እንደ ክብር ይመለከቱታል። እንዲህ ካለው አስተሣሰባቸው እንዲታቀቡ ሊያስታውሣቸው የሚችለው ደግሞ ሙሴ ዴ ማይሴ ነው። ከዚህ በተረፈ ዋናውና ዐብዩ ተግባር፣ ፖንቻርትሬይን ደግሞና ደጋግሞ ሁል ጊዜም ሳይሰለች የሚናገረው በወቅቱ ካሉት የቁርኩ ሃይሎች ጋር መግባባት ነው። በሌላም በኩል ስምምነቱ ሕዝባዊ ሥርዓት እንዲከበር ይረዳል። ይህ ካልሆነና ከፈረንሣይ ቆንሲል በኩል አንዳች የራስ መነቅነቅ እምቢታ ቢታይ ቱርኮች ችግር ፈጣሪ የሚሉትን የውጭ አገር ዜጋ ያባርሩታል። ስለዚህ የፈረንሣይ ማህበረሰቦችን በሰላም ማለንበት የቻለው ይህ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የሚጠቀሱ ጥቅሞችም አሉ። በካይሮ የሚገኘው ቆንሲል ምንም ዓይነት ኪራይ አይከፍልም። እንዲያውም በየዓመቱ አራት ሺህ ሊቭሬ ይቀበላል። በተጨማሪም ለጽሕፈት ቤቱና ለቤት አገልጋዮቹ በሚል ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሊቭሬ ያገኛል። በዓመት አንድ መቶ በርሜል የወይን ጠጅ ለማስገባት መብት ሲኖረው በአንድ በርሜል የሚከፈለው ቀረጥም ሁለት ተኩል ፒያስትሬ ነው። ከዚህ የሚገኘው ትርፍ የትና የት ነው። እነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች ሙሴ ዴ ማይሴን ሃብታም አድርገውታል። የዚህ ሁሉ ማጠንጠኛው በውስጡ ታላቅ ውስታ እንዳለበት እንዲሰማው ያደረገው ጀመር። ለጠባቂውና ለተከላካዩ ለፖንቻርትሬይን በፈረንሣይ የምሥራቅ ሕንድ ኩባንያ መርከቦች ተጉዞ፣ አሌክሣንደርያ ወደብ ሰንብቶ የሚሄድ ደብዳቤ መፃፉን ተያያዘው። በነዚህ ረዣዥም ደብዳቤዎች ውስጥ የሚበዛውና ዋናው ቅመም፣ ማንም እንደሚገምተው ውዳሴና ምስጋና ነው። ቢሆንም ግን እነዚህ እንደማር የሚጣፍጡ የውዳሴና የምሥጋና ቃላት ምናልባት አንድ ቀን ፖንቻርትሬይን ያቀለሽልሹትና ያስጠሉት ይሆናል የሚል ስጋት አለው። ስለዚህም ቆንሲል ዴ ማይሴ፣ እነዚህን የታላቅነት የሙገሣ ቃላት የአካባቢውን ሁኔታ ከሚገልፁባቸው የተለያዩ ጉዳዮች ጋር እያዋዛ ማለዘብ ጀመረ። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ፅሁፉ ከጭብጡ ወጣ ይል ጀመር። የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩን ምላሽ ባያውቅም፣ በገደብ የለሽ አገላለፁም ይክራ ጀመር። አንድ ጊዜ የሚዲተራኒያንና የቀይ ባህርን ለማገናኘት በይ መቆፈር መቻሉን ጠቅሷል።

ሙሴ ዴ ፖንቻርትሬይን፣ ለደብዳቤዎቹ ሁሉ መልስ ይሰጣል። እንዲያውም አስተያየቶችንና አንዳንዴም በፖለቲካው ጉዳዩ ላይ ጥቂት ማስታወሻዎችን ያክልባቸዋል። አሁን ወር በሞላውና በመጨረሻው በተላከው ደብዳቤ ላይ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ የቀጥታ ትዕዛዝ ያለበት የሚመስል ፅሁፍ ላከ። በደብዳቤው ላይ ከቬርሣይለስ ቤተመንግስት ተነስቶ በሮም አድርጐ አንድ የጀስዊት ቄስ ተልኮ ስለሚመጣ ቆንሲሉ እንዲጠብቀው፣ይህ ወንጌላዊ ቄስ ይዞት ከሚመጣው ከማንኛውም ዓይነት ትዕዛዝ ጋር በቅን መንፈስ እንዲተባበር የሚጠይቅ ነው። የደብዳቤው መንፈስ የራሱንና የንጉሥ ሉዊስ 14ኛን ምኞቶች እንደያዙ እንዲገምት የሚጠይቅ ነበር።

በፅሁፍ ሰፍሮ የሚተላለፍን መልዕክት ሊያጋጥም የሚችለውን አደጋ ለማስወገድ ሲባል፣ አንድ መልዕክተኛ መልዕክቱን በቃል ይዞ እንዲሄድ ማድረግ፣ በላኪውና በተቀባዩ መካከል የሚኖረውን ምስጢር በጣም ጥብቅ ያደርገዋል። የደብዳቤው መንፈስና ሊከተል



የሚችለው የሥራ ጉዳይ ሙሴ ዴ ማይሴን አሣሰበው። ውሎ ሲያድርና ጊዜም እያለፈ ሲሄድ ግን የተባለው የጀስዊት ቄስ ብቅ ሳይል ቀየ። የነገሥታት ፖሊሲዎች የሚጨበጡ አይደሉም። በየጊዜውና ሣያቋርጡ መልካቸውን ይለዋውጣሉ። ምናልባት የተባለውን የጀስዊት ቄስ ሌሎች ዲፕሎማቶች በሌላ አቅጣጫ ለአጣዳፊ ጉዳይ ወስደውት ይሆናል። ይህ ካልሆነ ቄሱ በጉዞው ላይ ደብዛው ጠፍቶ ቀርቷል። ሙሴ ዴ ማይሴ የአዕምሮ ዕረፍት አገኘ።

አሁን ግን ይህ ተንኘር መሆኑ የሚያጠራጥር ሰው ብቅ አለ። ሲደርስ ደግሞ በአጋው የክብር ዘቦች እጅ እስረኛና ግማሽ አካሉ እርቃኑን ሆኖ ነው። አጋው፣በራሱ ዕውቀትና ተሞክሮ ቆንሲሉ ምን ጊዜም ትክክለኛ ነው ብሎ የሚያምን ሰው ስለሆነ፣ ይህን ምርኮኛ ለመልቀቅ አላመነታም። በአንፃሩ የቄሱ ጉዳይ በሰዎች መካከል ከፍተኛ ጉጉት ቀስቅሷል። ይህ የተባለው የፀሃዩ ንጉሥ መልዕክተኛ መሳው አካሉ በጭቃ ተለውሶ፣ ነገር ግን ለአንድ ግለሰብም ይሁን እዚያ ለሚገኙ ሁሉ የፖለቲካ መልዕክት ይዞ መምጣቱን ለመግለፅ ፍፁም ድፍረት የነበረው ሰው ስለሆነ፣ ፖሻውና በከተማው ውስጥ የሚገኙ ሌሎች የውጭ ሃይሎች የዚህ ምርኮኛ ምስጢር በሚገባ እስካልተገለፀ ድረስ ጉዳዩ እንዲዳፈን አይሹም።

ሙሴ ዴ ማይሴ፣ በእንግዳ መቀበያው አዳራሽ ውስጥ እየተንጐራደደ እነዚህን ሃሳቦች በአዕምሮው ያመላልሣቸው ጀመር። እንግዳውና እርሱ ለብቻቸውም እራት የሚበሉበት ቦታ እንዲዘጋጅላቸው ትዕዛዝ ሰጠ። ሁለቱ ሰዎች ለብቻቸው መነጋገር ከመጀመራቸው በፊት የቆንሲሉ ባለቤትና ሴት ልጁ፣ ለካህኑ የአቀባበል ሰላምታ አቅርበው ክፍሉን ለቅቀው ወጡ። ኑቢያዊው የቆንሲሉ አልባሽ፣ ተጓዡ እንግዳ የሚታጠቡበትን ቀዝቃዛ ውሃ በባልዲ ይዞ በደረጃው ላይ እየተጣደፈ ሲራመድ ይሰማል። በሁሉም መልክ ሲታይ የቀድሞው ምርኮኛ እፎይታ ያገኙ ይመስላሉ። ሙሴ ዴ ማይሴ ግን ትዕግስት በማጣት በእንግዳው ላይ የቁጣና የብስጭት ስሜት ይሰማው ጀመር። በአዳራሹ ውስጥ መንጐራደዱን አቋረጠና እንዲታደስ ሲያደርገው በነበረው ሥዕል አንፃር በሚገኝ አግዳሚ ላይ ተቀመጠ። የተመለከተው ነገር እቅሉን እንዲስት አደረገው። የንጉሡ ፊት አንዳችም ስም የሚያስነሣ ስህተት የለበትም። የቆሸሸው ሁሉ ተወግዶ የንጉሡ የፊት ቆዳ ገፅታ ወደቀድሞው ዕዱነቱ ተመልሷል። ይሁን እንጂ በጣም በቅርበትና በከፍተኛ ጥንቃቄ ሲመረመር፣ በተፈጥሮ በነበረው ሽታ ላይ በስሱ የቀላ ቦታ ይታያል። ይህ ዓይነት ቀለም በህፃን ልጅ ፊት ላይ ቢሆን ኖሮ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በደረሰ የጥፊ ምት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችል ነበር። ግርማ ሞገስ ባለው የንጉሡ ፊት ላይ ሲሆን ግን፣ ያለልክ የተቀባ የጉንጭ ቀለም መስሎ ንጉሡም በመልካም ጤንነት ላይ የሚገኝና ህዝቦቹም ባለፀጋ ተስፋ መሆናቸውን የሚያመላክት ይሆናል።

«ሜትር ዠረሚ ነገ ማለዳ ከማንኛውም ሥራው በፊት እዚህ እንዲገኝ ንገረው!» ሲል በበር ጠባቂው ላይ አምባረቀበት።

ያ ባለጌ መናፍቅ፣ ሙሴ ዴ ማይሴ ተጠርቶ እንደወጣ ሥዕሉን ለማደስ ደፍሯል። ውጤቱም የተሳካ ነበር። ይህ በራሱ "ተመስገን እምላኬ!" ያሰኛል። ግን ምን ድንገተኛ መቅሰፍት ደርሶ ይሆን? ሥራው በርግጥ የተዋጣለት ነው። ክፍያም የሚገባው ነው። ስለክፍያው አስቀድሞ ስምምነት ተደርጓል። በአንፃሩ ግን የሰውዬው አልታዘዝ ባይነት የሚያስቀጣው ነው። እንዲህ ባለው ወሮበላ ላይ ሥልጣንን ለማሣየት ከዚህ የተሻለ ዘዴ የለም። በዚህ መሠረት ቆንሲሉ ለዚህ ባለጌና ደፋር መድሃኒት ቀማሚ ሁለት ምርጫዎችን

ያቀርብለታል። አንደኛው የአንድ ሳምንት እስር ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ከክፍያው ላይ የሚቀነስ የገንዘብ ቅጣት ነው። ሜትር ዠረሚ ደግሞ ከነዚህ ሁለት አማራጮች መካከል የገንዘብ ቅጣቱን እንደሚመርጥ ቆንሲሉ ቅንጣት ታህል አይጠራጠርም። የሥዕሉ መልክ ዕድሣት በስኬት ተከናውኗል። ይህ ማለት ከሙሉ የእጅ ዋጋ ክፍያ ላይ ቅናሽ በሚያስከትል ድል አድራጊነት ጣፍጦ የታጀበ ነው። አባ ቬርሣው ለአራት ሲመጡ፣ ቆንሲሉ እጅግ ደስ በሚል ተቀበላቸው።

«ወዳጄ ሆይ!» አሉ የጀስዊቱ ቄስ፣ የቆንሲሉን ሁለት እጆች በእጆቻቸው ውስጥ ይዘው። «ባንተ ውብ አቀባበል ከእስሬ ተፈታሁ። እንዲያውም ወደ ሕይወት የተመለስኩ ያህል ነው። መታጠቢያው፣ ንፁሆቹ ልብሶች፣ ያማረው ባለሥነስርዓት ቤት ሁሉ ነፃ አድርገውኛል። እንዲህ ያሉ ነገሮችን ለማግኘት ምን ያህል ጓጉቼ እንደነበረ ብታውቅ ትደነቃለህ»

የምስጋና እምባዎች የቄሱን ዐይኖች ሞሏቸው። ማኪያቬሊ የተናገረው እውነት ከሆነ፣ ሌሎችን የምንወዳቸው ባደረግንላቸው መልካም ነገር ከሆነ፣ ቆንሲሉም ለአባ ቬርሣው ያደረገላቸው ሞቀ ያለ የርህራሄ ና ከመጠን በላይ የሆነው እንክብካቤና አትኩረት ምንም መደነቅን ሊፈጥር አይችልም።

«ክብርት ማዳም ዴ ማይሌን በመተላለፊያው ላይ ማገኘት አክብሮቴን ገልጫለሁ። በእራት ገበታ ላይም አብራን እንደማትሆን ተረድቻለሁ። የቤትህን የውስጥ ሥነስርዓት በምንም ዓይነት ልጥሰው አልፈልግም» አሉ አባ ቬርሳው።

«የለም በፍፁም፣ በፍፁም። ለብቻችን የምንወያይባቸው ጉዳዮች አሉን። እነዚህን የሥራ ጉዳዮች ለመነጋገር የሚያመቸውን የእራት ሰዓት መጠቀም ይኖርብናል»

«እውነት ነው። ሴት ልጅህን፣ ማዳሞዜል ዴ ማይሌንም፣ በድንገት አግኝቻት ነበር። ስለውበቷና ስለጠንቃቃው ሥነ-ምግባርዋ ምስጋና ይገባሃል። አስተማሪዎችና ትምህርት ቤቶች በሌሉበት እንዲህ ባለ የባዕድ አገር እንዴት አድርገህ ልታስተምራት ብትችል ነው?»

«እስከ አሥራ አራት ዓመት ዕድሜዋ ፈረንሣይ ውስጥ ነበረች። አብራን እንድትሆን ያደረግነው ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ነው»

ሁለቱ ሰዎች ከዚህ በፊት ጨርሶ አይተዋወቁም። አሁን የጀመሩት ጭውውት ግን እንደ ረዥም ጊዜ ጓደኛሞች ቀጥሏል። በጨዋታቸው መሃል። «እንዲህ ባለ ርጥበት አዘል የአየር ጠባይ ባለበት አገር፣ በሚደንቅ ሁኔታ የተጠበቀ ነው» ሲሉ ቄሱ የንጉሡን ሥዕል አደነቁ። በመቀጠልም የቆንሲሉን ጤንነትና በያዘው የሥራ ደረጃ ላይ ያለበትን ሃላፊነት በሚመለከት ጥቂት ጥያቄዎችን ጠየቁት። በመጨረሻም ገበታ ላይ ሲቀመጡ ጭውውታቸው ወደ ክስታራ ጉዳዮች ተለወጡ።

«አባቴ? የጉዞዎን ዝርዝር ጉዳይ ለማወቅ እፈልጋለሁ። ሁሉንም ነገር። የተሣፈሩበት መርከብ ተሰባብሮ ሲወድቅ እንደጠፋብዎ ገልፀውልኝ ነበር?»



«ብጣም መጥፎ መሰባበርና መስጠም ነበር። የእግዚአብሔር ቸርነት ባይሆን ኖሮ ይኸኔ ሞቼ ቀርቼ ነበር»

በመቀጠልም፣ ከሮማ ከተማ እንዴት እንደለቀቁ ረዥም ታሪካቸውን ማውጋት ቀጠሉ። መርከቡ ተሰባብሮ የፀደቀው ከቆጵሮስ ደሴት እይታ ሣይሰወር ነበር። እኒህ ጀስዊት ቄስ አደጋ እንደማይቀር ሲገነዘቡ፣ በመርከቡ ላይ ከሚገኙ ጀልባዎች አንዱ እንዲወርድላቸው አዝዘው ከሌሎች ጥቂት ሰዎች ጋር ይሣፈራሉ። የባህሩ ሞገድ ከአንድ ማዕበል ከበጣጠሰው የጠረፍ ቋጥኝ ጋር ያጋጫቸዋል። ያች ለአንድ ሰው ብቻ የምታገለግል ጀልባቸው ጥልቀት ባልነበረው ቦታ ላይ ብትንትኗ ይወጣል። ግን ልክ በአንድ ከማይፈልጉት ውሃማ መቃብር ላይ እንደተጣሉና ይህ እየጉደለ ፣ ሁሉም እንደሚያውቀው ከምዕራት ፍርድ በኋላ ከሞት እንደገና እንደወጡ ያህል አባ ቬርሣው የቅሬታ ውጋት ተሰማቸው። ችግራቸውን፣ ህይወታቸውንና የተቀበሉትን ትዕዛዝ ለእግዚአብሔር በመተው በመሞታቸው አምነው ነበር። በመጨረሻው ሰዓት ላይ ትዝ የሚላቸው፣ በቀዝቃዛ፣ ጥቁርና በሚናወጥ ውሃ ውስጥ ሰምጠው የመሞታቸው ጉዳይ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ የሚያስታውሱት በአንዲት ትንሽ ጀረት አጠገብ ባለ አሸዋ ላይ እጆቻቸው ከርሣቸው ጋር ከባህሩ በተተፋ በአንድ ምሰሶ ላይ ታስረው መንቃታቸውን ነው። በዚያን ሰዓት ብቻቸውን፣ እርቃናቸውን፣ በፍርሃት እየተንዘፈዘፉ፣ በቶፈን ተይዘው ልክ አዳም በተፈጠረበት ዕለት እንደነበረው መስለው ነበር። ይሁንና እግዚአብሐር አልተዋቸውም። በዙሪያው ነዋሪ የሆኑ አሣ አስጋሪዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ከሞት አትርፈዋቸው በሚችሉት አቅም አልብሰዋቸው፣ እንደለመዱት መረቦቻቸውን በሚጥሉባቸው የግብፅ ጠረፍ ከሁለት ቀናት በኋላ አደረሷቸው። በርሣቸው ጥያቄ አሌክሣንደሪያ አጠገብ ባለ የባህር ዳርቻ አወረዷቸው። ጥሩ መተላለፊያ በሌለበት የኦቶማን ግዛት ውስጥ መሆናቸውን ሲረዱ ከተማውን መሸሽ ቀጠሉ። ከዚያም በአሌክሣንደሪያ ዙሪያ ጥምጥም ባለው በረሃ ተጉዘው ወደ ደቡብ ራቅ ብለው ተጓዙ። ለጀልባ ቀዛፊዎች የሚከፍሉት አንዳችም ሰባራ ሳንቲም እንደሌላቸው በመናገርና በመደራደር ወደ ካይሮ የሚያደርሣቸውን መንገድ በመጠየቅ አባይ ወንዝ ደረሱ፡

«የቀረው የምታውቀው ነው» ሲሉ በትህትና ተናገሩ።

ቄሱ ታሪካቸውን በሚናገሩበት ወቅት፣ ሙሴ ዴ ማይሌ አንድ ሺህ ጊዜ ያህል የማዳነቅና ተስፋ የመቁረጥ ድምፅ ያሰማ ነበር።

«ያጋጠመኝ መከራና ስቃይ፣ እዚህ የመድረሴንና አንተ ስታገኘኝ የነበርኩበትን ሁኔታ ማስረዳት ከቻለ በቂ ነው። ዋናውና አብዩ ጉዳይ ግን ሌላ ነው» ሲሉ የጀስዊቱ ቄስ ይበልጥ ክስተር ባለ ድምፀት ተናገሩ።

«አ! እውነት ነው። የንጉሡን መልዕክት ማለትዎ ነው» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ።

አባ ቬርሣው ወንበራቸው ላይ ተስተካክለው ተቀመጡ። አንዴ ወይም ሁለቴ ዓይኖቻቸውን በዝግታ እርገበገቡና ትህትና ባልተለየው ሁኔታ ውይይቱን ቀጠሉ። ሙሴ ማይሌ፣ የንጉሡን ሥዕል መልክት ሲያደርግ ራሱ ንጉሡ ከበላያቸው መገኘቱን ያበሰረው መሰለው።

1/25/10

«እቅጩን ለመናገር ምንም መልዕክት ይገኛል አልመጣሁም» አሉ የጄስዊቱ ቄስ።

«ነገር ግን ሲናገሩ እኮ . . . »

ጥቁር የለበሱት ቄስ፣ ዱ ማይሴ ዝም እንዲሉና ይህ ጉዳይ ጊዜ የሚወስድ ነው ለማለት ፈልገው እጃቸውን ከፍ አደረጉ።

«ምንም መልዕክት የለም ስልህ፣ በፅሁፍ መልክ ያመጣሁት የለም ለማለት ነው። በሌላ አነጋገር ንጉሣችን ራሣቸው በቀጥታ የፃፉት ወይም የገለፁት ነገርም የለም። ወደፊት ልታደንቀው እንደምትችለው የዚህ ምስጢር መጠበቅ በሁሉም መልኩ እጅግ አስፈላጊ ነው። እንዲጋጠመኝ አደጋ ሁሉ ሳደርሰው የማልችለውን መልዕክት ብቀበል ኖሮም ጥፋትና ነውር ይሆንብኝ ነበር።»

«በዚህ እስማማለሁ» አለ ሙሴ ዴ ማይሴ

«ምንም ዓይነት መልዕክት የለም ብልህም፣ በንጉሡ መንፈሣዊ አባት በኩል ራሣቸው ንጉሡ የሚሰማቸውን የገለፁበት ጉዳይ አለ»

«የንስሃ አባታቸው፣ አባ ዴ ላ ቾይስ ናቸው?»

የጄስዊቱ ቄስ የአይን ቆባቸውን አጨማደዱ። ሙሴ ማይሴ፣ በደረት እቅፉ ሙሉ እጅግ ብዙ ሃብት የታቀፈ ሕፃን ይመስል በሚያምር ስልት ይመለከታቸዋል።

«እንደምታውቀው የጄስዊት ሥርዓትን የሚከተሉት እኒህ ቅዱስ ሰው፣ የንጉሡን ምስጢር የሚናገሩት እጅግ በጣም ለሚቀርቧቸውና ለሚተማመኑባቸው፣ ለምሣሌ በቬርሣይለስ ቤተመንግስት የሃይማኖትን ጉዳይ በቀናኢነትና ያለዕረፍት በሚያስቡት እንደ ማዳም ዴ ማይንቴኖ፣ እንደ ዋናው መሪ ቄሣችን እንደ ሙሴ ፖንቻርትሬይን፣ በምሥራቅ ሜዲቴራኒያን ለሚገኙት የእየሱስ ማህበረሰቦች መሪ እንደሆኑት ረዳታቸውና ተወካያቸው እንደ አባ ፍሌሪአው እና አሁን ደግሞ እንዳንተ ላላችሁት ብቻ ነው።»

ሙሴ ማይሴ፣ ለዚህ ጠንካራ ለሆነው ሃይል ፍላጎት እጅ በመስጠትና በተደረገለትም አክብሮት የተነሣ በዓይኖቹ ግጥም ያለውን እምባ ለመደበቅ ሲል ራሱን ደፋ።

«ጉዳዩን በጥቂት ቃላት ጠቅለል ማድረግ ይቻላል። እንደምታውቀው በአሁኑ ጊዜ የክርስትና እምነት ከጠላቶችዋ ጋር በጦርነት ላይ ነች። የኦቶማን ቱርክ መስፋፋትም ለጊዜው ተገትቷል። የሚቀጥለው እርምጃ ጊዜ ይወስዳል እንጂ ዳግም በድል መንቀሣቀስ ይኖራል። ነገር ግን በክርስቶስ እየሱስ አምነው ለመኖር በሚሹ ወገኖች መካከል እጅግ ከባድ አደጋ ተቀስቅሷል። ይህ የሃይማኖት ተሃድሶ የሚባለው አስቀያሚ የእፍ ቁስል የሆነው ነገር፣ የእግዚአብሔርን የእጁን ሥራ በውስጥ ባሉ ጠላቶች ለማፈራረስ አደጋ እያሴረ ነው። እንዲህ ያለው ራሱን ቀና የሚያደርገውን ሰይጣናዊ እንቅስቃሴ፣ የፈረንሣይ ንጉሥ ራሣቸው ተቃውመውታል። ለምሣሌ በፕሮቴስታንትነት ላይ የሚደረገውን ተቃውሞ በራሣቸው ፈቃድ በናንቴስ አዋጅ ሰርዘውታል። አውሮፓም ውስጥ አልጋቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ ጠላቶቻቸውን



ፊት ለፊት ተጋፍጠዋቸዋል። ዊልሄልም የሚባለው የኦሬንጅ ግዛቱ ከሃዲ የፕሮቴስታንት መስፍን ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ነው። ትግሉ ግን በሜዲተራንያንና በሚያዋስኑት አገሮች ብቻ የተወሰነ አይደለም። ዛሬ ዓለም ሁሉ በዚህ ውጊያ ውስጥ ገብቷል። የክርስቶስ ኢየሱስ መልዕክት የሰው ዘር በማያውቃቸው ቦታዎች ሁሉ ላይ መድረስ ይኖርበታል። በአረማውያንም ዘንድ እንዲስፋፋ መደረግ ይገባዋል። ከዚህም በተጨማሪ በሚገባ ባልታወቁና ባለፉት ሁለት ክፍለ ዘመኖች ለክርስትና እምነት የፍልሚያ ሜዳዎች መሆን ወደጀመሩት አሜሪካ፣ ኢንዲስ፣ሩቅ ምስራቅ ወደሚባሉት አዲሶቹ ቦታዎችም መስፋፋት ይኖርበታል። በየጊዜው ተመሣሣይ ጉዳዮች ይገጥሙናል። በመጀመሪያ አንቀበላችሁም የሚሉን ትክክለኛው እምነት ውጭ መኖርን የለመዱት ህዝቦቹ ራሣቸው ናቸው። እነዚህ ሕዝቦች ለዘለዓለሙ ውጦ ሊያስቀራቸው የሚችለውን የሞራል አደጋ መገንዘብ አይችሉም። በሁለተኛ ደረጃ ይህ ተሃድሶ የሚባለው ተፎካካሪ ሃይልም ከኛ ጋር ተፋጥጦ ይገኛል። በርግጥ የዚህ ዲያብሎሳዊ ሙከራ፣ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል እጅግ ከሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንዳይደርስ የሚያደርግ ሙከራ ነው።»

እንደ እውነቱ ከሆነ ውይይቱ ወደ ፖለቲካና የሃይማኖት ጉዳይ ፅቅፅበት ሲለወጥ፣ የኒህ ደካማ ቄስ ችሎታና አንደበተ-ርቱዕነት በእጅጉ አስደንቆታል።

«የፈረንሣይ ንጉሥ በረዥም የዘውድ አገዛዝ ዘመናቸው ብዙ ጉዳዮችን ተምረዋል» በማለት ቄሱ ንግግራቸውን ቀጠሉ። «በታሪክ አጋጣሚ ከሆኑት ይልቅ አርቀው የማየት ችሎታ ያላቸው ናቸው። የንስሃ አባታቸውን ድንቅና አስገራሚ ችሎታ በትክክል የተረዱ ናቸው። ለደረሱበት ታላቅ ዓለማዊ ሥልጣን የበቁበትን ቁም ነገር የተሞላበት ትግል የተረዱ ናቸው። በዚህ ዓለም ውስጥ በእውነተኛው አምልኮና አሁንም በጨለማ ውስጥ በሚዳክሩ ሃይሎች መካከል ያለው ፉክክር ነፍስና ስጋቸው የሚጠገኑባቸው ሰው ናቸው። እስከ መጨረሻዋ ህቅታቸው ድረስ ለዚህ ለመታገል ቆርጠው ያሉ ናቸው። ምንም እንኳ ትግል የሚሹ ብዙ ጉዳዮች ቢኖሩም አንዳንዶቹ ከሌሎች ቅድሚያ የሚጠይቁ ናቸው። ቱርኮች በጊዜ ሂደት ዋጋቸውን ያገኛሉ። እኛ አሁን በጥሩ እድል ላይ እንገኛለን። እሳቱ እንዳይጠፋ እዚህ የሚገኙትን ጥቂት ክርስቲያኖች እናግዛቸዋለን። አስቸጋሪው የኦቶማን ሃይል መስነጣጠቅ ሲጀምር፣ መከላከያዬ ነው ብሎ በሚተማመንበት በያንዳንዱ ጉድባው ሰርስረን እንገባለን። በርግጥ አሁን ሰዓቱ አይደለም። ነገር ግን በቅርብ ያለች ርዳታችንን የምትፈልግ አገር እየጠራችን ነው። ልንቆጣጠረው ለማንችለው የታሪክ መዘውርና ለድንቅ የተራራ ሰንሰለቶችዋ ምስጋና ይግባቸውና ተለይታን የምትገኝ ትልቅ አገር አለች። ይህች አገር አሁንም በጨለማ ውስጥ ነች። ለማለት ያህል ልበለው እንጂ ይህቺ አገር በኛ ደረጃ ከመሆን ያለፈ የምትፈልገው የላትም። አገሪቷ የክርስቲያኖች አገር ነች። ይሁንና እምነቷ ባልተገባ መስመር የተገነባ በመሆኑ ዝብርቅርቅ ብሎ ያደነ ነው»

«አቢሲኒያ ነች!» አለ ሙሴ ዴ ማይሴ እንደ መፍዘዝ ብሎ።

«አቢሲኒያ። አዎን፤ ይህች በቅጡ ያልታወቀች ነገር ግን በእጅጉ የአማንያን አገር የሆነች፣ ሊበረቡሩዋት የቃጡትን ሁሉ ውጣ ያስቀረች፣ ነገር ግን አሁንም የኛን ድጋፍ የምትሻ አገር ናት»

ጀስዊቱ ቁስ፣ የሙሴ ዴ ማይሌን እጅ ለመያዝ ትርፍራፊ ባለበት ሣህን ላይ በመሣብ ጕንበስ አሉ።

በዚያች አገር አንድ የኤምባሲ ተግባር እንድታከናውን ሃላፊነቱን ጥለውብሃል»«የፈረንሣይ ንጉሥ ይህችን አገር መልሰው ወደ ቤተክርስቲያናቸው በመቀላቀል ክብራቸውን ከፍ ማድረግ ይፈልጋሉ። ግርማዊነታቸው



# 3

ጆን ባፕቲስት ፖንሴና ማትር ዣረሚ በመድሃኒት ቅመማና ሽያጭ ንግድ ሥራ ላይ በሽርክና በመሠማራታቸው፣ በአንድ ቤት ውስጥ በጋራ መኖር ጀመሩ። ቤቱ እንደ እስቱዲዮም ያገለግላቸዋል። ይህ ቤት በፈረንሣውያን ማህበረሰቦች መኖሪያ የመጨረሻው ዳር፣ ሰላምና ፀጥታ በነገሠበት ጕዳና ላይ በመሆኑ ብቻቸውን ሆነው ሲያከናውኑት ለሚችሉት ሥራ አመች ነው።

«ሃሎ! አንተ አስማተኛ ሽማግሌ፣ ለመሆኑ አለህ እንዴ?» በማለት ጕላ ባለ ድምፅ እየተናገረ ጆን ባፕቲስት ምስቅልቅል ያለውን የወንደላጤ ቤታቸውን በር በርግዶ ገባ።

በላይኛው ፎቅ ላይ፣ በቅጥር ግቢው ውስጥ ያለውን አፀድ እንደልብ ለማየት የሚያስችል ሰፊ በረንዳ አለ። መስኮቶች ሁሉ መጋረጃዎቻቸው ወርደዋል። ሌሎች ብዙ መስኮቶች በሸክላ ጡብ ድፍን ተደርገው ተዘግተዋል። ፖንሴ ሲደርስ፣ ጓደኛው ጕራዴ ይዞ ፍዝዝ ብሎ በበረንዳው መደገፊያ ላይ ደገፍ ብሎ አገኘው።

«ይህን መሣሪያ ጨብጠህ እዚህ ብቻህን ምን እየሠራህ ነው?»

«ቆንሲሉን አሁን ገደልኩት» አለ ዣረሚ

«እውነትህን ነው?»

ጆን ባፕቲስት ጓደኛውን አንዳች ነገር እንዳወከውና እንዳበሣጨው አወቀ።

«እውነቴን ነው የምልህ። አሥራ ሁለት ጊዜ ነው የገደልኩት። ማየት ትፈልጋለህ፣ ተመልከት» ይህን ተናግሮ፣ የገደል ስባሪ የሚያክለው ማትር ዣረሚ፣ ስላሰፈው ሃማብ ርግጠኛ እንዳልሆንና ከባላጋራው ጋር በጕራዴ እንደሚፋለም ሰው ወደ ፊቱ ዘሎ ወረደ። ግድግዳው ዘንድ ሲደርስ በብዙ ጥረት ጕራዴውን በባላጋራው ሰውነት ውስጥ ሰንዝሮ ሲወጋውና ሲሰንጥቀው የሚያሰማውን ዓይነት ዝቅ ያለ የበቀል ድምፅ አሰማ። የጕራዴው

ጫፍ፣ የግድግዳውን ልስን ዘልቆ ሲወጋው፣ አንድ ትንሽ ሽራፊ ነገር ተቀርፎ ሲወድቅ የሁለት የጡብ ሸክላዎች ቀይ መልካቸው ተጋለጡ።

«ብራቮ፣ በውነት መሞት ይገባዋል» በማለት ጆን ባፕቲስት

አጨበጨበ። «ለመሆኑ ከዚያ በኋላ እፎይታ ተሰማህ?»

«እጅግ በጣም ነዋ!»

«መልካም አሁን እንግዲህ ተረጋግተሃል። እስቲ አጠቃላይ ሁኔታውን አስረዳኝ»

ጆን ባፕቲስት ወንበር ስቦ ተቀመጠ። ጓደኛው ወደፊትና ወደኋላ እየተንጎራደደ በያዘው ጉራዴ እግሩን ይጠበጥባል።

«የዚህ ቆንሲል እስር መርሮኛል። በዚህ የተነሣ መልኩን ሳየው ግደለው! ግደለው! የሚል ይመጣብኛል።»

«ይህማ እንግዳ ጉዳይ አይደለም» አለ ጆን ባፕቲስት ፈገግ እያለ። «እንደሚመስለኝ ይህን ሥራ እንዳትቀበል ከመጀመሪያም የወንድምነት ምክሬን አካፍዬህ ነበር»

«እንዳልቀበለው! አስገድዶ ሲጠራኝስ?»

«እኔን በግዳጅ ጠርቶኝ ቢሆን ኖሮ አልሄድለትም ነበር» አለ ጆን ባፕቲስት

«እንደዚያ ነው እንዴ? ልንገርህ። አየህ፣ አንተ የኘሮቴስታንት ተከታይ አይደለህም። ስለዚህ ከኔ ይልቅ በጣም በተሻለ ሰላምና ደህንነት እዚህ መኖር ትችላለህ። ከዚህም በላይ ፖሻው ያማክርሃል። የግል ሃኪሙ ያህልም ያከብርሃል። እኔን ግን ከአንድ ምስኪን የዕፅዋት ቀማሚነት ሌላ ማንም አይደለሁም። በርግጥ ጥያቄው ይህ አይደለም። ማይሌ አስገድዶ ጠራኝ። እኔም እሺ ብዬ ፣ ሥራውንም ሠርቼ ጨረስኩ»

«እና ታዲያ ተካፈልህ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀው

«በትክክል እምናለሁ!»



«እንግዲያውማ ሁሉም ነገር ጥሩ ነው»

«አይምሰልህ። አንተ ቆንሲሉን አታውቀውም። ጠባቂዎቹ ባሻቸው ሰዓት መጥተው ወደ እስር ቤት እንደሚከትቱኝ አስባለሁ። እስካሁንም አንዳች ነገር ሳያስተውል የቆየው ምናልባት በሥራ ተወጥሮ ቢሆን ነው።»

«ቢሆንስ ምን ሊያደርግ ይችላል። የተመደብክበትን ሥራ ማከናወን ወንጀል አይደለም»

«በርግጥ አይደለም። ክቡር ቆንሲሉ ግን ከዚህ ባሻገር መሆን የሚፈልግ ሰው ነው። የግድ ተማስተሃል የሚል ሰው ነው። ሕግ አስከባሪውም፣ ዳኛውም እርሱ ራሱ ነው። ስለዚህ ከራሱ ጋር ክርክር አይገጥምም። ይህ ስሕተም ሽማግሌ የገንዘብ መቀጫ ይጥልብኝና ከማገኘው ክፍያ ላይ ይቆርጥብኛል»

«ክፈላ! በዚህ ካበቃልህም የታሪኩ ፍፃሜ ይሆንልሃል»

«አላደርገውም። ከዚህ ይልቅ እርሱን ገድዬ ወደ ሌላ አገር እኮበልላለሁ»

ገንዘብን በተመለከተ ሜትር ዠሬሚ ሙሉ በሙሉ የፕሮቴስታንት የውሣኔ ስሜት አለው። ሌላው ቀርቶ በትክክልና በተገቢ መንገድ ያላገኘውን ሰባራ ሣንቲም እንኳ የማይቀበል ሰው ነው። እንዲሁም ደግሞ ሊከፈለው ከሚገባው ውስጥ አንዲት ሣንቲም ብትጎድልም አይቀበልም።

«ዠሬሚ፣ እስቲ ረጋ በል። በቅጣት ሣቢያ ተጠያቂ አድርጎ ሊይዝህ መብት የለውም። በኛ ደረጃ ቆንሲሉ ሊያደርግ የሚችለው የገንዘብ መቀጮ ወይም የእሥር ጊዜን በአማራጭነት ማቅረብ ነው። ለዚህ ደግሞ የላብህን ዋጋ ከሚበላብህ መታሰሩን ምረጥ። ተቆልፎብህ የምትቆየው ለሁለት ቀን ያህል ነው። ከዚያ በኋላ ዳግመኛ ከርሱ ጋር አንዳችም ነገር አትሠራም። ይህ ማለት ባላደረግሁት ኖሮ እያለ እድሜ ልኩን ሲንዘነዝበት የሚኖርበት ጉዳይ ይሆናል»

ቆንሲሉን ከረዥም ጊዜ በፊት ድምጥማጡን ሊያጠፋው ይችል በነበረው በጓደኛው ባፋጭ ምክር ሜትር ዠረሚ ረካ። የጓደኛውን ጥበብ የተምላበት ብልጠትም አደነቀ።

ለእፍታ ያህል ሁለቱም በፀጥታ ቆሙ። ጆን ባፕቲስት፣ ወደ ጓዳ ገብቶ ሁለት ሹሩቤ ብርሌዎችንና የሚጠጣ ይዞ መጣ። ሁለቱም ጠጡ።

«ከጥቂት ጊዜ በፊት በክሃሊጅ ድልድይ አጠገብ የእሣት ቃጠሎ ደርሶ ነበር። ለአጭር ጊዜም ቢሆን ሽብር ፈጥሮ ነበር። የቆንሲሉ ሚስትም የነበረችበት ጋሪ በተሰበሰበሰው ሕዝብ ምክንያት ከመንቀሣቀስ ተገትቶ ነበር።

ምንም የተለየ ስሜት ስላጣበት ሜትር ዠረሚ «እሀ» አለ።

«በነገራችን ላይ» ሲል ጆን ባፕቲስት ሌላ መጠጥ ለራሱ እንደገና እየቀዳ «በቆንስላው ውስጥ በቆየህባቸው ረዥም ጊዜያት ውስጥ . . . »

ጓደኛው ትከሻውን አነቃነቀ።

«ለመሆኑ ከማዳም ዴ ማይሌ ጋር አብራ ያለችውን ወጣት ልጃገረድ ታውቃታለህ?»

«ምን ትመስላለች?»

ጆን ባፕቲስት፣ የማስታውሰው በልጃገረዲቷ ፀጉር ላይ የነበረውን ሪቭን ነው በማለት ራሱን ማጋለጥ አልፈለገም።

«በደንብ አድርጌ ላያት አልቻልኩም።»

«ለመሆኑ ፈዛዛ ቢጫ ፀጉር፣ ትላልቅ ሰማያዊ አይኖች ያሏትና ያዘነች የምትመስል ናት?»

«ይመስለኛል፣ አገላለፅህ ትክክል ነው» ሲል ወጣቱ ሰው በፍጥነት መለሰ

«እሷማ የዚያ የበስባሳ ቆንሲላችን ልጅ ነች



«ተፈጥሮ ይቅር ለማለት ፈጣን ነች» አለ ጆን ባፕቲስት

«አይቻታለሁ ብትል የማይመስል ነገር ነው። ወጣቷ ልጅ በሰላማዊ መልክ የትም ወጥታ አታውቅም። እዚህ በቆየሁባቸው ሁለት ዓመቶች ውስጥ፣ አንድም ሰው፣ በመሠረቱ አንድም ሰው አይቷት አያውቅም። እኔ እንኳን በጨረፍታ ያየኋት በአዳራሹ ውስጥ ባለው መተላለፊያ ማዕዘን በኩል እጥፍ ስትል ነው። በርግጥ ዛሬ የጴንጤቆስጤ የበዓል ዕለት ነው። ሁለቱ ሴቶችም በቪሲታንዲን የእመምኔቶች ገዳም ቅዳሴ ላይ ለመገኘት ስላቀዱ ነው ያየሃቸው። በታላላቅ በዓላት ጉዞ ካልሆነ በስተቀር አባቷ እንደሃብት በቤቱ ውስጥ ደብቆ ነው የሚያስቀምጣት»

«እንደዚያ ከሆነ ትክክል ነው። መደበቅና መጠበቅ ያለባት ነች» አለ ጆን ባፕቲስት።

«ቆንሲሉ እኮ ጭራቅ ነው» ሲል ሜትር ዠረሚ መለሰ።

ከሆደ ባሻ የድምፅ ቅላጼው በመነሣት ዠረሚ ቂሙን እያመነዠከ ይመስላል።

ጆን ባፕቲስት በመክዳው ግንብ ላይ እግሮቹን አመሳቅሎ ወንበሩ ላይ ተዘርግቶ ተቀምጧል። ከጣሪያው በላይ፣ ከበረንዳው መቀመጫ አናት በላይ ያለው ሰማይ፣ ሃምራዊ እየመሰለና በመጥለቅ ላይ ያለችው ፀሀይ እንደ ሃረግ የተንሸረሸረገውን ደመና እያቀላችው ነው።

ከርሱ መኖሪያ ሠፈር በላይ ያለችው ወጣት ልጃገረድ ያጋጣሚ እንዕብራቂ፣ ትውስታውን ወደ ቬነስ፣ ወደ ፖርማና ወደ ሊዝቦን ወሰደበት። በርግጥ በነዚህ ከተሞች ውስጥ ማንኛውም ነገር ይሣካ ነበር።

ጆን ባፕቲስት፣ ከዙረት ሕይወት የሚገኘውን መልካም ነገር መያዝ የጀመረው ገና ከወጣትነቱ ጊዜ ጀምሮ ነው። ከአንድ የተለየ የህብረተሰብ ክፍል የመደብና የሥልጣን እርከን ውጭ በመሆኑ ይህ ተጓዥ ነፃ ሰው ነው። ስለሆነም ከማንም ጋር በእኩልነት የመነጋገር ዕድል ያለው ነው። መነሻ ምንጩ ምንም ይሁን ምን፣ አንድ ዘዋሪ ሰው ብልህ ከሆነ የልዑል ባለሟል ወይም የልዕልት ፍቅረኛ ሊሆን ይችላል። ሌላው ቢቀር ይህ ሊሆን እንደሚችል በዓይነ ህሊናው ሊመለከት ይችላል። ፖንሴ ግን፣ ጮሌነትና ሊሆን ይችላል ብሎ የወደፊቱን ነገር

የማሰብ ጉዳይ ይጐድለዋል። እነዚህ ከዚህ በላይ የተነገሩት ሁሉ እርሱ በኖረባቸው ከተሞች በተደጋጋሚ እውነት መሆናቸውን አረጋግጧል።

ፖንሴ ወደ አገሩ ባህልና ሥርዓት ውስጥ ተመልሶ ሲገባ፣ ተገቢ ቦታውን ይይዛል። ልክ እዚህ ካይሮ በሚገኘው የፈረንሣይ ማህበረሰብ ውስጥ እንዳለው ዘር ማንዘሩን ለመደበቅ ቢሞክርም፣ የአንዲት አገልጋይና የአንድ ማንነቱ የማይታወቅ ሰው ልጅ ከመሆኑ ሌላ ማንም አይደለም። በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው የልዩነት ቦታ አዲጋች እንቅፋት ነው። እንዲህ ያለው እንቅፋት ደስታን ይገፍፋል። ዛሬ ያየውን የተለየ እንግዳ ፍጡር ይቅርና ህልሙም እንኳ የርሱ እንዳይሆን ይገፍፍበታል።

«ይህ ከተማ እየሰለቸህ አልመጣም?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀ።

«በሌላ ልለውጠው ብችል ደስታውን አልችለውም ነበር» በማለት በተመሣሣይ ሃሣብ ውስጥ ነጉዶ የነበረው ሜቴር ዠረሚ መለሰለትና «ግን የት መሄድ እንችላለን?» ሲል አከለ።

በምሥራቃዊው የሜዲተራኒያን አገሮች ሁሉ፣ ሁሉቱም እንደሚያውቁት እዚህ ያጋጠማቸውን ዓይነት ቅሬታ ይገጥማቸው ነበር። ይህ የሚሆነው አካባቢው ባዕድ ስለሚሆንባቸው ሣይሆን፣ የራሣቸው አገር ተወካዮቻቸው በዚያ አካባቢ መገኘታቸው ሲበዛ የርጉ ዝንቦችና ግዴለሾች ስለሚሆኑባቸው ነው። ለዚህ ሁሉ መፍትሄው ወደ አውሮፓ መመለስ ነበር። እዚያ በርግጥ ያለ አንዳች የሥራ ፈቃድ፣ እዚህ የጀመሩትን የእጅ ሥራ ጥበብ ሙያቸውን፣ በማያቋርጥ የሕግ ክትትል ሥር ሆነው መሥራት አይችሉም።

«ይበልጥ በራሣችን የምንተማመን እንድንሆን ደፍረን ወደ አዲሱ ዓለም መሄድ ይኖርብናል» አለ ጆን ባፕቲስት።

ይህ ድንቅ ሃሣብ ይመስላል። ስለሆነም ረጋ ባለና በሰከነ መንፈስ በሚገባ ለመነጋገር እንዲችሉ፣ በጠመዝማዛው ጉዳና አድርገው ወደ አሮጌው ካይሮ ክፍል ደስ እያላቸው



የጆስዊቱ ቄስ፣ ወደ ክፍላቸው ሄደው ዕረፍት ለማድረግ እንዲችሉ እንዲፈቀድላቸው ጠየቁ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ክርኖቹን ጠረጴዛው ላይ አስደግፎ፣ ውስጡ በሃሴት ተሞልቶ፣ ብቻውን ቀረ። የኤምባሲ መክፈትን ጉዳይ ከጠቀሱበት በኋላ ሙሴ ማይሌ ፣ የቄሱን ሌሎች ማብራሪያዎች ማዳመጥ ትቶ ነበር።

ይህ የኤምባሲ መክፈት ጉዳይ በቆንሲል ዴ ማይሌ ላይ ያልታሰበ ድንጋጤ ፈጥሮበታል። ነገር ግን ስሜቱ እንዳይነበበት በከፍተኛ ጥረት ሊደብቀው ሞክሯል። በክፍሉ ውስጥ ብቻውን ለመቆየት እንዲችል በማለት ጠባቂውን አሰናብቶ፣ በውስጡ የታፈነውን እምባውን ለቀቀው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አስተናጋጁ መጥቶ በአንድ ትልቅ አልጋ ላይ ለመተኛት እንዲችል ረዳው። ይሁን እንጂ ሀሳናውን ስቶ እንደተኛ ቀረ።

ይህ ሁሉ ሲሆን የዲፕሎማቱ ባለቤትና ሴት ልጁ ወደ ሺሲታንዳይን የእመምኔቶች ገዳም ካደረጉት ጉዞ ገና መመለሣቸው ነበር። የተከፋውን ቆንሲል እንደተመለከቱ ዙሪያውን ፈጥነው ከበቡት።

ማዳም ዴ ማይሌ፣ ከቤት የምትወጣው ከስንት አንዴ ነው። በቤቱ ውስጥ ካሉት ክፍሎች አንዱ፣ ሙሉ በሙሉ ለርስዋ አገልግሎት ብቻ እንዲውል ተደርጓል። የዚህን ክፍል አንድ ጥግ የፀሎት ቦታ አድርጋዋለች። የተለያዩ የሴት ዕቃዎችዋንና የልብስ መስፊያ መኪናዋን በሌላው ጥግ አስቀምጣቸዋለች። በነዚህ ቦታዎች ላይ ተራ በተራ እየተገኘች የሚሰማትን ቅሬታ፣ ጥያቄም ሆነ ምሥጋና ትናገራለች። ባሏን በፍፁም ታማኝነት ታመልከዋለች። ይህ ባህርይ ዳብሮባት የወደፊቱን ሕይወት በጨለምተኛነት እንድታስበው አድርጓታል። ይህች ምስኪን ሴት፣ ተራና የማይረቡ የቆንስላውን ችግሮችና ኑሮ እንደአስደንጋጭ አደጋ ማሰብና መገመት ጀምራለች። እንዲህ ያለው አስተሣሰብ ያደረባት፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ራሱ የሚያጋጥመውን ማንኛውንም ዓለማዊና የሥራ ግጭት ሁሉ እያጋነነና እያስፈራራ ይነግራት ስለነበረ ነው። እንዲህ ባለው ሕይወት ውስጥ ስለኖረች፣ የሚነገራት ሁሉ፣ እንዲህ እንደዛሬው አንድ ቀን ባለቤቷ ዝርግት እንዳለ እንደሚቀር እንድትገምት ያደርጋት ነበር። ይህ እንደሚደርስ ብትገምትም፣ ከሆነ በኋላ እርሷ ልታከናውነው ስለሚገባት ጉዳይም እንዲሁ አንድ ቀን እንኳ ሳታሰላስል ቀርታ አታውቅም። አሁን ግን ባጋጠማት ድንጋጤ አልጋውን እየዞረች ማልቀስዋን ቀጠለች። ወጣቷ ልጅ ግን አዕምሮዋን ሰብስባ፣ አለንጋ የመሰሉ ጣቶችዋን በመጠቀም በአባቷ አንገት ላይ የታሰረውን ክራቫት ለማላላት ሞከረች።

ሙሴ ማቼ ዱካው ሳይሰማ መካከላቸው ከች አለ። የቆንሲሉን ሁኔታ ከተመለከተ በኋላ ሃኪም እንዲጠራ ሃሣብ አቀረበ። ሁለቱም ሴቶች ሃሣቡን ተቀበሉት።

«ይሁን፣ ግን ማን አለ?» ስትል ወጣቷ ማዳሞዜል ዴ ማይሌ እየፈራች ጠየቀች።

«ፕላኩስ?» በማለት ሙሴ ማቼ ዝቅ ባለ ድምፅ ጠቆመ።

ቆንሲሉ፣ በርግጥ ብድግ ብሎ ተቀመጠ።

«እሱ አይሆንም! » ከሴኮንዶች በኋላ ፍፁም እንደዳነ በመግለፅ በአንድ መከዳ ላይ ተቀመጠ።

የአንድ ሰው ስም ምን ያህል አስደንጋጭና አስፈሪ እንደሆነ ከዚህ መረዳት ይቻላል። ዶክተር ፖላኮ፣ የአንድ የመርከብ ላይ የቀዶ ጥገና ሃኪም ነበረ። በዚሁ ጊዜ ከአንዲት ተዋናይት ፍቅር ይዞት ተከትሏት ይመጣል። ተዋናይቷ ወይዘሮ በሞት ስትለይ፣ እርሱ ካይሮ ውስጥ ያለረዳት ይቀራል። የካይሮ ሰዎች በሙሉ የሚያውቁት፣ የመጨረሻው እውነተኛ ሐኪም ከአራት አመት በፊት አገሩን ለቅቆ ከሄደ በኋላ ለፈረንሣውያን ማህበረሰብ አባላት የህክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ የተፈቀደለት ባለሙያ ዶክተር ፖላኮ ብቻ ነበር። እንዳለመታደል ሆኖ ስለመድሃኒት ያለው አስተሳሰብ ጊዜ ያለፈበት ነበር። ዕውቀቱም የተስተካከለ አልነበረም። የሕክምና ዘዴውም ጭካኔ ያለበት ነበር። በነዚህ ምክንያቶች የተነሣ፣ ማንም ሰው ስለህክምና ሊያማክረው ፍቃደኛ አልነበረም። ምንም አይነት የጤና መታወክ ሲደርስ፣ ሐኪሙ ዶክተር ፖላኮ ነው ከተባለ፣ ልክ አንድ ሰው የራሱን ትንፋሽ ዋጥ ሲያደርግ እንደማይታፈነው ሁሉ፣ የፈረንሣውያን ማህበረሰብ አባላትም በርሱ ላለመታከም ሕመማቸውን ዋጥ አድርገው ይችሉት ነበር። ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ነጋዴዎችና ተራ ሰዎች፣ ሌሎች ፈዋሾችን መፈለግ ጀመሩ። ለአይሁዳውያንና ቱርካውያን አስመሣዮች፣ ዝነኛው መድሃኒት ቀማሚ ጆን ባፕቲስት ፖንሴ ሆነ። ይሁን እንጂ ህክምናን በተመለከተ እነዚህን ህገወጥ ሰዎች ማንም እንዳይጠይቃቸው ቆንሲሉ በግልፅ ከልክሏል። በዚህ ግቢያ፣ ከእንግዲህ በኋላ፣ ካይሮ በሚቆይባቸው ጥቂት ዓመታት፣ ለሌሎች ምሣሌ ሆኖ ለመገኘት ሲል ህመሙን ሊያስታግሱለት የሚችሉ እንኳን ቢሆኑ ወደነርሱ ድርሽ ላለማለት ወስኗል።

በቆንሲሉ የማገገም ዕድለኛነት፣ እዚያ የነበረው ሁሉ የእፎይታ ትንፋሽ ተነፈሰ። የክፍሉም ድባብ ሰላም ሰፈነበት። ማዳም ዴ ማይሌ ቡና እንዲቀርብ አዘዘች።

አራቱም ሠዎች ቡና ይዘው ክብ ሠርተው ተቀመጡ።

«ይህን ያህል የሚያስከትለው መዘዝ የለውም። ምጣችን ትንሽ ከበድ ይል ነበር። የአየሩም ጠባይ ምንም አይልም። ወይን ጠጁ ግን . . . » ሲል ቆንሲሉ አስረዳ

ከዚህ የበለጠስ ምን ሊናገር ኖሯል? ለርሱ የተነገረውን ታላቅ ምስጢር ለነዚህ ለፍላፊ ሴቶች መንገር እንደሆነ አስቸጋሪ ነው። ቢነገር እንኳ ምናልባት ለማቼ ነው። አዎን፣ ማቼ ይህን ምስጢር ማወቅ ይገባዋል። በመጪው ጊዜ ውስጥ ይህ ሁሉ ውርስ፣ ብዙ ጥረት ይጠይቅ ይሆናል። ለዚህ ደግሞ ረዳት ያስፈልጋል። የጄስዊቱ ቄስ ይህን በርግጥ ይረዳሉ። ማቼ፣ ያለ አንዳች ገደብ ሲያገለግል የኖረና ፍፁም ታማኝ ሰው ነው። ከወጣቷ ሴት ልጁ ጋር ማቼ ሲነጋገር የተመለከተው ቆንሲል፣ ተደፈርኩ በሚል ሁኔታውን አልወደደውም። ለምሣሌ፣ እዚህ እፊቱ እንኳ፣ ይኸው እንዳቸው ወደ ሌላኛው ፊታቸውን አዙረው፣ የቡና ሲኒዎቻቸውን ሙጭጭ አድርገው ይዘው ይታያሉ። በርግጥ ምስኪን ሕፃን ስለሆነች እንዲህ ባለው ጉዳይ ላይ እንዳችም ስህተትና ጥፋት አይታያትም። ማቼ ግን ማድረግ ከሚገባው በላይ አጥብቆ እየተመለከታት መሆኑን ምሎ መናገር ይቻላል።



ከማዳሞዜል ዴ ማይሌ ጋር ለቅርብ የፍቅር ግንኙነት ሣይሆን፣ ለጉርብትናው ሲባል ግንኙነት እንዲኖረው የተፈቀደለት ወጣት፣ ሙሴ ማቼ ብቻ ነበር። ምንም እንኳ ከእንቅልፉ ሲነቃ ደስ የማይል ጠረኑን ትቶ ቢኖሃና ሲበዛ አስቀያሚ ሆኖ ብታገኘውም፣ ወጣቷ ልጃገረድ ከርሱ ጋር መጫወትን ትደሰትበታለች። ማቼ የተለየ ሰው ነው። ሲያዳምጣት በከፍተኛ ጥሞት ነው። አሁን ግን እርስዋ ተገልላ በምትገኝበት ሁኔታ ላይ ጭውውትን ውብ ሊያደርግላት ስለሚችል ይህ በእውነቱ በቂ ነው። ሙሴ ማቼን በተመለከተ ግን እርሱ የራሱን የሕይወት ጉዳና በሚስማማው መልክ መርጧል። ያጋጠመውን የማዕረግ ዕድገት ዕድልም፣ አባቷ በእጁ ውስጥ ይዞባት ላለች አንዲት ወጣት ሴት ሲል ሊያባክንና ለድርድር ሊያቀርብ አይሻም። ይሁንና፣ በጣም አልፎ አልፎ፣ በርሱ በኩል የግድ መከናወን ያለበት ጉዳይ ሲኖር፣ ልዩ በሆነው ውበቷ፣ አቋሟና ወጣትነትዋ ሳቢያ ስትመጣበት ጥውልግልግ ይልላታል። እርሱ ከውስጡ ባይሆንም በጥልቀት ይመለከታታል። እርሷም ከውስጧ ባይሆንም ምላሹን በደስታ ትሰጠዋለች። እንዲህ ያለው ሁኔታ በአባቷ ዓይኖች ውስጥ ከወንጀል ያነሰ አይደለም።

«ከሙሴ ማቼ ጋር ለብቻችን የአፍታ ቆይታ እንዲኖረን ይፈቀድልናል?» ሲል ቆንሲሉ ጠጠር በሚል ድምፅ ጠየቀ።

«ማቼ! ስለባህሪህ ልናገራቸው የምችላቸው ብዙ ነገሮች አሉኝ። ነገር ግን አሁን ጊዜው አይደለም።»

ቆንሲሉ ንግግሩን በቀጣ ጀመረው። «ማቼ! ልብ ብለህ አስተውል። በችግር ጊዜ እንደሚነሣ እንጂ አንዳችም ችሎታህን በማሰብ እንዳልሆነ፣ እደግመዋለሁ፣ በችግር ምክንያት ስለሆነ እጅግ ከበድ ያለ የፖለቲካ ምስጢር ላካፍልህ ነው። ለዚህ ደግሞ ብቃት ያለህ መሆንህን ማሣየት ይጠበቅብሃል። ይህ ካልሆነ ደግሞ ከካድከው ሰው አስፈሪ ቁጣ የሚሸሽግህና የምትድንበት አንዳችም ጉድጓድ በምድር ላይ አይኖርህም።»

ይህን ተናግሮ፣ ቆንሲሉ፣ አመልካች ጣቱን ወደ ሉዊስ አሥራ አራተኛ ሥዕል ቀሰረ። ወጣቱ ማቼ፣ አፍንጫው ጉልበቶቹን እስኪነካ ድረስ በተቀመጠበት ሆኖ ዝቅ በማለት ታዛዥነቱን አረጋገጠ።

# 4

«አሁን በነፃነት ልገልፀው በማልችለው ምክንያት ንጉሡ ወደ ኢትዮጵያ አንድ ኤምባሲ ለመላክ ወስነዋል» ሲል ሙሴ ማይሌ፣ ዝቅ ባለና በጕረነነ ድምፅ ንግግሩን ጀመረ።

«ይህን በተመለከተ ክቡርነትዎ አምና አንድ ደብዳቤ ልከው ነበር» አለ ሙሴ ማቼ

«ትክክል ነሁ። ወደዚያ አገር ዘልቀን መግባት የምንችልባቸውን የተለያዩ ዘዴዎች ሚኒስትሩ ጠይቀውኝ ነበር። በእግርጥ ጉዳዩ አሁን በቤተመንግስቱ ተቀባይነትን አግኝቷል። ያን ጊዜ ደርሼበት የነበረውን የድምዳሜ ሃሳብ ለመሆን ታስታውሰዋለህ?»

«ሁለት መንገዶችን ጠቁመው ነበር። አንደኛው፣ በጂዳ በኩል ጠረፉን ተከትሎ በባህር ላይ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን በሲናር ንጉሣዊ ግዛትና በተራሮች ተጉዞ፣ በየብስ ላይ የሚል ነበር»

«ብዙ መረጃዎችን ደህና ታስታውሣለህ ማቼ። በነዚህ ሁለት አማራጭ መስመሮች ላይ የነበረኝን የወደፊት ምልከታስ ታስታውሣለህ በባህር ከተባለ፣ ወደ አገሪቱ የሚያስገባው መስመር ከቱርኮች ጋር ስምምነት ባለው የሙስሊም ገዥ የተያዘ ነው። የዚህ ገዥ አብይ ሥራው ወደዚያች አገር አንድም አውሮፖዊ ክርስቲያን በተለይም ካቶሊካዊ ዘልቆ እንዳይገባ ማገድ ነው። ባለፉት ሃምሣ አመቶች ይህን እንቅፋት ያስወገደው የለም። እንደሰማሁት፣ ሙከራ ያደረጉት የመጨረሻዎቹ ቀሣውስት እንዲገደሉ፣ አንገታቸው ተቆርጦና ራሣቸውም ተላጭቶ ለኢትዮጵያው ንጉሥ በአገልግል እንዲላክ ትዕዛዝ ሰጥቷል።»

ሙሴ ማቼ ፊቱን በጥላቻ አጨማድዶ ሲያበቃ፣ ከኪሱ ውስጥ መሃረቡን አውጥቶ አፍንጫውን ለአጭር ጊዜ ጫን አድርጐ ያዘ።

«የየብሱም መስመር እንደዚሁ ፍፁም መጥፎና የሚሰቀጥጥ መሆኑ ተረጋግጧል። በሙከራ አቋርጦ ወደዚያ አገር የገባው ከስንት አንድ አውሮፖዊ ግን፣ ሕዝቡ ንጉሥ እያለ የሚጠራውን ንገሠ ነገስት በቀጥታና ፊት ለፊት ለማግኘት ችሏል። ሆኖም ይህ የተሣካላቸው



ሰዎች ቀሪውን ዘመናቸውን በንጉሠ ነገስቱ ቤተመንግስት ውስጥ እስረኛ ሆነው ያሣልፋሉ። ከዚህ ሌላ፣ በጣም ብዙውን ጊዜ ካቶሊካውያን መሆናቸው ሲረጋገጥ በአመፅ በሚነሣው ሕዝብ በድንጋይ ተወግረው ይገደላሉ»

«ያለ ጄስዊቶች ይህ ሊሆን የሚችል አይደለም» በማለት ሙሴ ማቼ እያዘነ ተናገረ

«እሽሽሽ» አለ ቆንሲሉ ፊቱ ፍም እየመሰለ።

ማንም ሰው ስአዳራሹ ውስጥ የሚነገረውን እንደማይሰማ አይቶ ለማረጋገጥ፣ በዝግታ ተራምዶ በሩን ከፈተው።

«አሁን እዚህ ያሉን እንግዳ ከነርሱ አንዱ እንደሆኑ በሚገባ የምታውቅ ይመስለኛል። ከዚህም በላይ እኒህ ቄስ፣ ከንጉሡ የንስሃ አባት ጋር የቅርብ ዝምድና አላቸው»

«ይህም ቢሆን ያው ነው። እዚያ ምን እንደተፈፀመ ሁሉም ማወቅ ይገባቸዋል»። ሲል ሙሴ ማቼ ዝቅ ባለ ድምፅ ተቃወመ።

«ያ ከሃምሣ አመት በፊት ነው»

«ይህም ቢሆን ብልህነትና ግዴለሽነት የተቀያየጡበት ያልተለመደ አሠራር ነው። በርግጥ ንጉሡን አሣምነው፣ ሃይማኖቱን አስለውጠውትና አገሪቱንም በሙሉ አሸንፈው፣ እንዲገዟቸውም አድርገው ነበር። ነገር ግን በዚህ ሣቢያ ተሳድደው ወጥተው ለዘለአለሙ የደረሱበት ሳይታወቅ ቀርቷል። የሃይሉ ወይም የነገሩ ፍፃሜ የሆነው አንድም ካቶሊክ እንዳችም ዓይነት ሰበብ ሰጥቶ ወደ አቢሲኒያ እንዲገባ አለመፈቀዱ ነበር። አሁን በዚህ ቤት በጉብኝት ላይ የሚገኙት ካህን፣ ወደዚያ እንመለስና እንሞክር ይሆናል የሚል የጅል ሃሣብ ያቀርባሉ ብለው ክቡርነትዎ እንደማይነግሩኝ ተስፋ አለኝ»

«የለም፣ ማቼ፣ ካህኑ ብቻቸውን ወደዚያ ለመሄድ አላቀዱም፣ የርሣቸው ዕቅድ አንተ ልታስበው ከምትችለው በላይ እጅግ አስገራሚና አስደንጋጭም ነው»

የቆንሲሉ የታችኛው ከንፈር በትንሹ መንቀጥቀጥ ጀመረ። ቀደም ሲል ታጡክ የነበረው ጤንነቱ እንዳያገረሽበት በመፍራት እጁን በጠረጴዛው ላይ አሣረፈ።

«አሁን እኔን ሲልኩኝ አሰቡ።»

«እርስዎን፣ ክቡር ሆይ? ይህ ፍፁም ሊሆን የማይችል ነው።» ሲል ሙሴ ማቼ ከተቀመጠበት ሶሆ ዘልሎ ተነሣ።

ሁለቱ ሰዎች፣ ፊቶቻቸው ቀልተው፣ ለጥቂት ጊዜ እንቅስቃሴ አቋርጠው እርስ በርሣቸው ተፋጥጠው ቆሙ። ከማዳሞዜል ዴ ማይሴ ጋር በቡና ሰዓት ያለጥንቃቄና እንደልቡ የመሆኑ ጉዳይ ያስቆጣው ቆንሲል፣ አሁን ባልታሠበ አጋጣሚ ወደ ሰላማዊና የተረጋጋ መንፈስ ተለወጠ።

«የጤንነትዎ ጉዳይ . . . » በማለት እጆቹን አንዲት የቢራቢሮ ነፍሣትን በአየር ውስጥ ለመያዝ እንደሚሞክሩ አይነት እያወናጨፈ ተናገረ

«አዎን፣ አዎን ጤንነቴ ጉዞውን ፈፅሞ መቋቋም የሚችል አይደለም» ሲል ቆንሲሉ ፈጥኖ አረጋገጠ። «የአየር ጠባዩ ደግሞ ያባብሰዋል። በዚያም ላይ ማቋረጥ የሚገቡኝ እጅግ ብዙና ሠፋፊ በረሃዎች አሉ»

ፊቱ በቅፅበት ጠቆረ።

«ነገር ግን ይህን ፈፅሞ አያምኑልኝም። ከቬርሣይለስ አኳያ ሆኖ ሲተመለከተው በካይሮና በሱዳን የአሸዋ ምድር መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም»

«ሁሉም ተመሣሣይና አንድ . . . » አለ ሙሴ ማቼ። አዕምሮው አሁንም ያሰዕረፍት ይጋልባል።

«ቱርኮች!» ሲል ቆንሲሉ ከፍ ባለ ድምፅ ተናገረ። «የኦቶማን ባለሥልጣኖች እንዲህ ያለውን ተልዕኮ አይፈቅዱም። ስለክርስትና ሃይማኖት መስበክ እዚህ የተከለከለ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ የኦቶማን ቱርክ ፖሊሲ፣ አቢሲኒያ በሙስሊም ጎረቤቶች ምንጊዜም ተከብባ



እንድትቀር የሚል ነው። ካቶሊኮች ከጆርባቸው የሚያደርጉትን ስምምነት ያህል ቱርኮችን የሚያስፈራቸው ሌላ ነገር የለም»

«እርግጥ ነው። ኤምባሲ እንዲከፈት ካስፈለገ ፍፁም በምስጢር መጠበቅና በማይታወቅ ሰው የሚመራ መሆን ይገባዋል» አለ ሙሴ ማቼ

«ከዚህም በላይ አደጋውም ቀላል ነው። ክፍያ እስከተደረገ ድረስ ከኦቶማኖች ጋር ማንኛውም ነገር ማደራጀት ይቻላል። ይሁንና ፖሻው፣ የአስፈፃሚነት ደረጃ ያለው የቆንሲል ጽህፈት ቤትን ለመክፈትና ኤምባሲ ሆኖ ለሚጓዝ ሰው ለመፍቀድ ከፍተኛ ገንዘብ ይጠይቃል» በማለት ቀደም ሲል የገለፀውን የራሱን አስተሣሰብ እንደሚቃረን ሳያመዛዝን ተናገረ።

«በእያንዳንዱ የአቋም ለውጥ ላይ መደለያው ብዙ ገንዘብ የሚያስወጣ ሲሆን የግድ ነው»

ሁለቱ ሰዎች ስሜቶቻቸው በደስታ ጋሉ። ሙቀቱ ሳንቃውን በመክፈቱ መስኮቶች በከፊል ተከፍተዋል። ቆንሲሉ በቃል እየነገረው፣ አንድ አጠር ያለ ማስታወሻ ለመፃፍ ሙሴ ማቼ ብዕርና ወረቀት አነሣ። የማስታወሻው ይዘት በስርዓት የተቀነባበረ መከራከሪያ ነጥቦችን የያዘ ነው። ከነዚህ ሁሉ ዐብይ የሆነው ነጥብ ግን፣ ዲፕሎማቱ ወደ አቢሲኒያ የሚያደርጉት ጉዞ የወደፊቱን ሁኔታ የሚያሰናክልና አሁንም ለተፈፃሚነቱ እርግጠኛነት የማይኖርበት መሆኑን የሚገልጽ ነው። ማስታወሻውን ደግመው በደስታ አነበቡት። ሙሴ ማይሴ ሁለት ትናንሽ ብርጭቆዎች አምጥቶ፣ የደረቀ ወይንጠጅ ቀድቶ ስለጤንነታቸው ጠጡ።

ወይነጠጁ የመረረው ያህል ፊቱን ከሶ አስመስሎ፣ ብርጭቆውን ጠረጴዛው ላይ እያስቀመጠ «አልሸሹም ዞር አሉ። በዚያም አልን በዚህ ሁሉም ንጉሡን አስመታዘዝ ነው!» አለ ቆንሲሉ

«አስመታዘዝ አይደለም፣ ክቡር ሆይ! ንጉሡ፣ አቢሲኒያ ውስጥ ኤምባሲ እንዲከፈት ይፈልጋሉ። እርስዎ ይህን ተልዕኮ ሲመሩ አለመቻልዎን ብቻ ያሣያሉ»

«እንግዲያው አንድ ሌላ ተተኪ ማግኘት ይኖርብናላ?»

ቆንሲሉ፣ ምናልባት ምርጫውን በኔ ላይ ያሣርፍ ይሆናል በሚል ሃሣብ፣ ማቹ ሲቃ ያዘው። ሠላማዊ ርጋታ የተሞላበት ብሩህ የሕይወት መስመር እየጠበቀው፣ ወደ ሞቱ ለመሄድ የሚፈልግበት አንዳችም ምክንያት እንደሌለው ተሰማው።

ፈጥኖ አስተዋለውና «የምንፈልገው ሰው ጥሩ የስኬት ዕድል ሊኖረው የሚችል መሆን አለበት። ንጉሡ ኤምባሲ ለማቋቋም ብቻ የሚፈልጉ አይመስለኝም። ምላሹንም ይሻሉ። አንድ ዲፕሎማት ለዚህ ጉዳይ ቢመረጥ በጣም ትኩረት ስለሚስብ ከግብፃውያን ወሰን ከቶም ማለፍ አይችልም»

«ትክክል! በመጀመሪያው ደብዳቤያችን ላይ ለሚኒስትሩ የፃፍንላቸውም ይህንኑ ነው» ሲል ቆንሲሉ አረጋገጠ።

ሁለቱ ሰዎች በዝምታ ማሰባቸውን ቀጠሉ። በወንበሩ መደገፊያ ሥር ሲመለከቱት በላብ የወረዛው የሙሴ ማቹ የጥጥ ጃኬት ከብብቱ ሥር ጠቆሯል። ቆንሲሉ ይህን ስለተመለከተ ለአፍታ በጥላቻ ተሞላ። እንደ እውነቱ ከሆነ ልብሱን ወዲያውኑ ሊለውጥ ይገባዋል ሲልም አሰበ።

ቀደም ሲል ሲያውጠነጥነው በነበረው የሃሣብ ፈረስ ላይ ሲጋልብ ቢሞክርም፣ በመካከሉ ሃሣቡን በሠረቀበት ጉዳይ የአስተሣሰቡ አቅጣጫ ስለተቀየረበት፣ «በእውነቱ የምንፈልገው የተግባር ሰው ነው» ሲል በድንገት ጮኸ።

በራሱ ሃሣብ የተገረመው ሙሴ ማይሌ፣ ነገሩን ሣይጨርስ አቋረጠ። የዚህን ሃሣብ እውነተኛነት በመገንዘብ ሙሴ ማቼም እንደዚያው ግርም አለው።

«እርግጥ ነው። ክቡር ሆይ፣ በጣም ትክክል ነዎት። ንጉሡ የሚፈልጉትን ነገር ሊያቀርብላቸው የሚችል ሰው ይፈልጋሉ»

«ነጋዴ ነዋ!»

የሙሴ ማቼ ፊት በደስታ ፈካ። «ጌታዬ! እንደሚያስታውሱት አንድ የነጋዴ ቅፍለት ከኢትዮጵያ ተነስቶ ካይሮ እንደሚገባ መረጃ ደርሶን ነበር። ይሁንና ይህ ቅፍለት አሁን የት



እንደደረሰ ፋናው አልታወቀም። ምናልባት ከከተማው በስተደቡብ ሲል ተበታትኖ ይሆናል። የዚህ ቅፍለት መሪ ደግሞ በተደጋጋሚ ወደ አቢሲኒያ የተመላለሰ የሙስሊም ነጋዴ ነው»

«ታውቀዋለህ እንዴ?»

«አንድ ጊዜ ካይሮ ውስጥ ሰዎች ለይተው አሳይተውኛል። ቁመናውና አተያዩ ትህትና የተሞላው፣ ሲያዩት ለማኝ የሚመስል ነው። እንደነገሩኝ በመጨረሻው ካደረገው ጉዞው ሲመለስ፣ አምስት መቶ ሺህ ሊቱ ሊያወጣ የሚችል የወርቅ ዱቄት፣ የጥሪኝ ዝባድ፣ የአምበርግሪስ ማዕድን አምጥቷል። ይህን ያገኘው ንጉሡ ባዘዘው ሸቀጥ ልዋጭ ነው።»

ሙሴ ማይሌ ስሜቱ ተነሣስቶበት በክፍሉ ውስጥ ወደ ፊትና ወደ ኋላ መንጐራደድ ጀመረ።

«ለመሆኑ አሁን ካይሮ ውስጥ ይገኝ ይሆን?»

«ይህን አላውቅም። በአጠቃላይ እዚህ የሚገኝ አይመስልም። ነገር ግን እርግጡን ማን ይናገራል። ሰውዬው ንግዱን የሚያከናውነው በከፍተኛ ምስጢር ነው። አቢሲኒያን በተመለከተ መረጃ ሊሰጠን ቀርቶ ሊያነጋግረን እንኳ ፈቃደኛ መሆኑንም ርግጠኛ መሆን አልችልም።»

«ቀስ! ጉዳዮችን ተራ በተራ እናንሣቸው። መጀመሪያ ፈልገህ አግኘው፤ ከዚያ በኋላ እንዴት ሊተባበረን እንደሚገባ እናውቅበታለን?» ሲል ምላሽ የማይሻ ትዕዛዝ ሰጠ።

ቆንሲሉ ቁርጥ ያለ ውሣኔ ላይ ደርሷል። ሙሴ ማቹን ወደ በሩ ይዞት

«በል ወጥተህ ይህን ሰው አሁኑኑ ፈልገህ አግኘው»

በቆንሲሉ ድንገተኛ ጥድፊያ ሁለቱ ተደናገረ።

«ፈረሴ ያውልህ፤ ተከታይ ዘበኛ፣ ገንዘብና ሌላም የሚያስፈልግህን ያዝ። ሰውዬው በከተማው ውስጥ ካለ አይገቡ ገብተህ አምጣው። በነገራችን ላይ ስሙ ማን ይባላል?»

«አረቦች፣ ሃጂ አሊ ይሉታል»

«በል ወዳጄ፣ ሃጂ አሊን ለማግኘት እግዜር ይርዳህ፣ ይቅናህ»

በመጨረሻ ላይ የተነገረውን የቅርበት ቃል ሲሰማ ማቹ ልቡ በኩራት ተሞላ። በተልዕኮው ተስፋ ቢቆርጥም ወደ ቅጥር ግቢው ፈጥኖ ። ከአሥር ደቂቃዎች በኋላ ከተማው ውስጥ ገብቶ ሰመጠ፡

❦

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ዝግጅት በሌለው አቀራረብ ሃሣብ ገብቶት፣ ከሙሴ ማቹ ጋር በመሆን የፃፉትን ማስታወሻ አውጥቶ ያብራራለት ጀመር። የጀስዊቱ ቄስ፣ በንቃት ተቀምጠው ተረጋግተው ያዳምጣሉ።

ጥቂት ከተወያዩ በኋላ፣ ወደ አቢሲኒያ የሚሄደውን የኤምባሲ ቡድን፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ራሱ እንዳይመራው የሚለውን የቆንሲሉን ሃሣብ አባ ቬርሣው ደገፉ። ይህ አቋም ለቆንሲሉ እፎይታን ሰጠው።

«እውነቱን ለመናገር አንተ ወደዚያ እንዳለብህ ያሰበም አልነበረም» ሲሉ ቄሱ ንግግራቸውን ደመደሙ።

ይህን አስቸጋሪ ጉዳይ በተመለከተ ከቄሱ የቀረበው አስተያየት መልሶ በጠበጠው። ምናልባት ፈርቷል ብለው ጠርጥረውት ይሆን? አንዳንድ ጊዜ፣ እውነተኛ ጀግንነት ስድብን በፀጋ እስከመቀበል ይደርሣልና እርሱም እንደዚያ ታስቦ ከሆነ ለመቃወም ተዘጋጅቶ ነበር። ነገር ግን ጥርሱን ነክሶ ዝም አለ።

«ሌላ ምን አማራጭ ሃሣብ ትሰጠናለህ?» ሲሉ ቄሱ በጥሞና ጠየቁ።

«እንደሚታየኝ ከሆነ ከታላቁ ንጉሣችን ግርማዊ ሉዊስ 14ኛ፣ ይህ ከዚያው ከበቀለበት አገር ሌላ ለማያውቀው ባለዘውድ የኢትዮጵያ መሪ፣ ምንም ዓይነት የአቤቱታ አቀራረብ መልክ እንዳይኖር ነው። እንደነዚህ ካሉ ሰዎች ጋር ግንኙነት ሲጀመር ምን እንደሚጠብቁ የሚያውቅ



የለም። ባለፈው ምዕተ ዓመት የፖርቹጋልን ኤምባሲ እንዳጋጠመው ዓይነት የኛም ኤምባሲ ምርኮኛ ቢደረግ፣ በግርማዊነታቸው ላይ የሚደርሰውን ውርደት ያስቡት። የኤምባሲው መሪ የነበረው ፔድሮ ዴ ኮቪልሃም ተይዞ፣ ለአርባ ዓመት እዚያው ታሥሮ ቆየ። በመጨሻም እዚያው ሞተ። ይህን ሁሉ ሣስብ እኛ ከምንልከው መልዕክተኛ ይልቅ እኛን የላከን ባለሥልጣን ታላቅ ነው።»

«አስተሣሰብህ ጥልቅ ነው። እኛ ባሰብነው መንገድ ግን አሁን እውተኛውን ኤምባሲ መላክ ማለት የአቢሲኒያ ገዥም በተመሳሳይ ደረጃ እንደምንፈልገው ምላሽ እንዲሰጠን ያገፋፋል የሚል ነው። ይሁንና የምንሻው የመጨረሻ የውጤት ደረጃ ላይ ሊያደርሱን የሚችሉ ሌሎች ዘዴዎች ካሉህም . . . »

ውይይቱ እየተካሄደ ያለው ለአባ ቬርሣው በተመደበው በሁለተኛው ፎቅ ላይ በሚገኘው ሰፊ ክፍል ፊት ለፊት ባለው ሰገነት ላይ ነው። ከዚህ ከፍታ ላይ ሆነው ሁለቱ ሰዎች የፈረንሣይ ማህበረሰቦች መኖሪያዎች እጅብ ብለው የሚገኙበትን ዋና ጉዳና ይቃኛሉ።

«እኔ እንደሚታየኝ ኢትዮጵያ ከግብፅ ጋር ጠብቃቸው ያሉንት መደበኛ ግንኙቶች ለኛ በሚጠቅም መልክ መጠቀም ነው» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ በልበ ሙሉነት ተናገረ።

«እነዚህ የምትላቸው ግንኙቶች ምን አይነት ናቸው?»

«ሁለት ዓይነት ናቸው። በየጊዜው የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት፣ የአሌክሣንደሪያ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርክ አንድ አዲስ አቡን መርጠው እንዲልኩለት መልዕክተኛ ይልካል። ይህ ዓይነቱ ልማድ ዘመናት ያስቆጠረ ነው። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የበላይ መሪ፣ አቡን ይባላል። ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የበላይ አባት ሆኖ የሚላከው፣ ግብፃዊ ኮፕቲክ ነው። በርግጥ ይህ ዕድል በጣም አነስተኛና ልንተማመንበት የማንችልበት ነው።»

«ሌላው ዕድልስ?»

«ነጋዴዎች ናቸው። በአንዳንድ ዓመት ላይ ከአቢሲኒያ ተነስቶ ሸቀጦችን ካይሮ ውስጥና እግረመንገዱንም ባሉ ቦታዎች ለመለዋወጥ የሚመጣ ቅፍለት አለ»

«ንጉሡ ከሙስሊሞች ጋር በጦርነት ላይ የሚኖር ነበር የሚመስለን»

«እኛም ብንሆን ከቱርኮች ጋር በጦርነት ላይ ነው ያለነው። ያም ሆኖ ይኸው እርስዎና እኔ በዚህ ሰንጎት ላይ በሰላም ተቀምጠን እንጫወታለን። ግለሰቦች ሲያከናውኗቸው ለሚሞክሯቸው ጉዳዮች መንግሥታት ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። አንዳንድ ግንኙነቶች ደግሞ ጨርሶ የማይበጠሱ ናቸው አባቴ»

«ክቡር ሆይ» አሉ ቄሱ። በዲፕሎማቱ ላይ ያላቸውን ሙሉ እምነት በሚያረጋግጥ አስተዋይ ፈገግታ፣ «የንጉሡን እቅድ ወደፊት ሊያራምድ የሚችል መፍትሄ እንድትጠቀም ሁሉንም ነገር ባንተ ትከሻ ላይ ጥያለሁ።»

ቆንሲሉ ራሱን ዝቅ አድርጎ እጅ ነሣ። ውስጡ ግን በትህትና ኩራት ተሞላ።

ጹ

ሙሴ ማቼ ወደ አሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ተመለሰ። ከመጠን በላይ ስላላበው ፀጉሩ በራሱ ላይ ተጣብቆ፣ እርሱም በላብ ተጠምቆና የደረቀው የላብ ጨው በጉንጩ ላይ መስመር አበጅቶ፣ ይቅርታ በመጠየቅ ወደ ቆንሲሉ ጽህፈት ቤት ዘሎ ገባ።

«አገኘሁት» ሲል በደስታ ምስጢሩን ገለፀ

«ነጋዴያችንን?»

«አዎን፣ ሃጂ አሊን ራሱን?»

አንድ እጁን በልቡ ላይ ጫን አድርጎ፣ ቀስ በቀስ ትንፋሹ መለስ አለለት።

«ከተማዋን በሙሉ አሰስኳት። ሁሉም ሰው ሲለኝ ነበር። እንዲያው እንደዕድል ሆኖ አንዱ መረጃ አቀባዩ ትናንት አይቶት ኖሮ ነገረኝ»

«አሁን የት አለ? » ሲል ቆንሲሉ ከስተር ብሎ ጠየቀው።



«በእንግዳ መቀበያው ክፍል እየጠበቀ ነው። አስቀድሜ ግን ልገልፅዎ የምፈልገው ነገር አለኝ . . .» ማቼ ንግግሩን አረመና «ክቡር ሆይ! አለ» አለ። ትንፋሹ መለስ ሲልለት ወደሚታወቀው ሥነ-ሥርዓታዊ ባህርይውም ተመለሰ። በምንም ዓይነት ሁኔታ የበታቾች ነፃ እንዲሆኑ ሙሴ ዱ ማይሌ አይፈቅድም።

«ወስላታና ብልጣብልጥ ቀበሮ አይነት ነው።» ሲል ሙሴ ማቼ ቀጠለ። «ስለ አቢሲኒያ አንዳችም ቃል እንድተነፍስ አልፈቀደልኝምና ቃል ገብቼለታለሁ»

«እና ታዲያስ?»

«አንድ መቶ ኤኩስ»

«እውነት?» ቆንሲሉ እንዲቀጥል አደረገው።

«ይህን ያህል ካገኘ ይናገራል»

«አንድ መቶ ኤኩስ ሊያወጣ የሚችል ምን ሊነግረን ይችላል?»

«ክቡር ሆይ፣ የተስማማሁበትን ጉዳይ እንዲያከብሩልኝ እማፀናለሁ። ይህ ካልሆነ ክምት የከፋ ውርደት ይገጥመኛል»

«እሺ ይሁን፣ እከፍላለሁ፣ ግን ምን አለ?»

«እስከ አሁን አልተነፈሰም»

«እየቀለድክ ነው!» አለ ሙሴ ዱ ማይሌ ክፍሉን ለቅቆ የሚወጣ እየመሰለ።

«ክቡር ሆይ! እባክዎን ይናገራል። ንጉሡ ምን እንደሚፈልግ ይነግረናል» ሙሴ ማይሌ ለአፍታ አመነታ።

«እሺ እንግዲያው ምን ትጠብቃለህ? አስገባው!» አለ በቁጣ

ሃጂ አሊ፣ የጉማ ምንጫቸው ይህ ነው ተብሎ ሊነገርባቸው ከማይችሉት ሰዎች አንዱ ነው። ማንም ሊገምተው ከሚችለው በላይ ቀጭን ነው። አጥንትና ቆዳ ከሆኑ እጆቹ፣ ጉድጓድ ከመሰሉት ጉንጮቹ ጋር ሲመለከቱት የሚሰበር ነገር ይመስላል። አፍንጫው መንጠቆ ሲመስል፣ የአይኖቹ ቆቦች ትላልቅ ናቸው። የሰውነቱም ቀለም መዳብ መሰል በመሆኑ የመን ውስጥ የመናዊ፣ ግብፅ ውስጥ አረባዊ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አበሻና ሌላው ቀርቶ ህንድ ውስጥ ህንዳዊ ያስመስለዋል። ከዚህም ባሻገር፣ በሐሩር ፀሃይ ቆዳው የጠቆረበት ሰው ነው ተብሎ፣ አውሮፓዊም መባል የሚችል ነው። አረቦች የሚለብሱትን የተለየና ሰማያዊ የወታደር ጃኬት ለብሷል። አረንጓዴ ገምባሌ ያለው ጫማ ተጫምቷል። የቀኝ ጆሮው ተበስቶ የወርቅ ቀለበት ጉትቻ አለበት። የቆንሲሉን እጅ በሁለት እጆቹ መሃል ተቀብሎ ዘርግቶ ያዛቸውና ሦስት እጥፍ የሚሆን የታዛዥነትና የአክብሮት ሁኔታ ካሣየ በኋላ፣ የቀኝ እጁን በራሱ ልብ ሳይ አሣርፎ ሲያበቃ ባቶቹን በመሣም ሠላምታውን ፈፀመ።

ሙሴ ማይሌ፣ እንዲህ ያሉትን የተለያዩ የሰላምታ አቀራረቦች የመቀበል ልምድ ቢኖረውም፣ ሁልጊዜም አስልቺ የሆኑትን የሰላምታ አቀራረቦች ሳለመቀበል ሳይገልፅ አያልፍም።

ሙሴ ማቼ፣ ለሁለቱም እያስተረጎመላቸው ውይይቱ በዝግታ ጀመረ። ሃጂ አሊ፣ የቆንስላውን ጽሕፈት ቤት ማሸብረቅ ከሥዕሉ በመነሣት ሲፈርጀው፣ የንጉሡን ውብ ቁመናና የተጋበዘውን ከቆንጥር አበባ የተቀመመ ጣፋጭ መጠጥ አደነቀ። ምንም ያህል የበዛ ሃብት ቢኖረውም፣ ተቀምጦ የሚውል ሰው፣ በሚተኛበት ጊዜ ከበላዩ ሆነው በጓደኝነት ለሚጠብቁት ከዋክብት ካሣ መክፈል አለበት በማለት አስተያየቱን ቋጨ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ አስተያየቱን በትህትና ተቀበለው። ይህም ሆኖ ውይይቱ ሊሣካ አልቻለም።

ከሙሴ ማቼ በተሰጠው ምልክት ቆንሲሉ በጥግ በኩል ካለው ባለግጣም ሣጥን አንድ የቆዳ ቦርሣ አወጣ። ቦርሣው ቃል የገባውን ገንዘብ መጠን ይዟል። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ለግመል ነጂው ሰጠው። ተቀባዩም ወዲያውኑ ሰወረው። ከዚህ በኋላ፣ ሃጂ አሊ ስለንጉሡ ማውራት ጀመረ። በአሁኑ ጊዜ ዘውድ ጭኖ ያለው ንጉሠ ነገስት፣ እያሱ ይባላል። ይህ



የርሱ መጠሪያው ነው። ዕድሜው አርባ ዓመት ይሆናል። ሃይለኛ ጦረኛ ነው። ብዙ ታላላቅ ጦርነቶችን ተዋግቷል። አሁን ግዛቱ ሰላም ነው።

«ኢትዮጵያውያን የሚፈልጉት እንዳችም ነገር የለም። አገራቸው የሚፈልጉትን ሁሉ ታቀርብላቸዋለች» ሲል ቀደም ብሎ ሙሴ ማቼ ላቀረበው ጥያቄ ሃጂ አሊ መለሰ።

«ይሁን እንጂ ተመልሰህ የሆኑ ነገሮችን እንድታመጣለት ንጉሡ ሳይዋዋልህ እንዳልቀረ ይገባኛል» አለ ቆንሲሉ ሆን ብሎ

የሃጂ አሊ መልሱ አጭር ነበር።

«እንደሚለው፣ እቃዎች አይደሉም» ሲል ሙሴ ማይሌ አስተረጎመ።

«ምን ማለቱ ነው ዕቃዎች አይደሉም ሲል? ታድያ ምንድነው?»

«ይህን እኔ አላውቅም ክቡር ሆይ፣ ምናልባት እንስሳት ይሆኑ?»

«እርሱኑ ጠይቀው»

ሙሴ ማቼ ጥያቄውን ተርጉሞ ነገረው። በዚህን ጊዜ ነጋዴው ጭንቅላቱን ወደ ኋላ ወርዋሮ ተንከተከተ።

«የዚህን ደስታ ምክንያት ማወቅ እንችላለን?»

«በግልፅ ለመናገር ምንጩ ጥያቄህ ነው» አለ ሙሴ ማቼ

«ንጉሡም ምንም እንደማይፈልግ ነገርኳችሁ። እናንተ ግን እንስሳት ይሆኑ? ትላላችሁ። ይህ በርግጥ አስቂኝ ነው» አለና ስርቅ እያለው ሃጂ አሊ መሳቁን ቀጠለ።

«ጌታዬ» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ተበሣጭቶ። «የጨዋታ ስሜትህን ሙሉ በሙሉ እጋራለሁ። ይሁን እንጂ ማወቅ የምፈልገው፣ ወደ ኢትዮጵያ ስትመለስ ዕቃዎች ወይም

እንስሳት ካልሆኑ ምን ልትወስድ እንዳሰብክ እንድትነግረን ነው። ይህን ልትነግረን ተዋውለናል?»

ሃጂ አሊ ተመልሶ ፍርጥም አለ። «ሰው እየፈለግሁ ነው»

ሙሴ ዴ ማይሌና ሙሴ ማቼ ፈጣን የአይን እይታ ተለዋወጡ። «ደህና! ምን ዓይነት ሰው ነው?»

«ይህማ የመንግስት ምስጢር ነው። በነፍሴም ቢመጣ የማልናገረው ነው» ሲል ነጋዴው አንዳችም ክርክር በማያሻው ቅላጼ ተናገረ።

ረዘም ያለ ዝምታ ሠፈነ። ከዚህ በኋላ ቆንሲሉ ሌላ ቡና ለማምጣት ወደ ማጦኑ እንዲሄድ፣ ሙሴ ማቼ ምልክት ሰጡ። ሆኖም ግን፣ ሙሴ ዴ ማይሌ በዝምታና በንዴት ሳይቀበለው ቀረ። በመጨረሻም ፉክክሩ አድክሞትና ግቡም

ሩቅ እንደሆነ በማመዛዘን ቆንሲሉ ተሸነፈ። እንደመጀመሪያው ሁሉ ይህኛውም ቡና በነጋዴው ጓሌት ውስጥ ለምጦ ጠፋ።

ሃጂ አሊም ቡናውን ከተቀበለ በኋላ ለተግባር ተነሣሣ። «ባለፈው ዓመት ታምሜ ነበረ»

የአጀማመሩ ሁኔታ ቆንሲሉን ተስፋ አስቆረጠው «በቀጥታ ወደ ፍሬ ነገሩ ግባ»

የግመል ነጂው በራሱ ስልት ርዕሰ ጉዳዩን እንዲቀጥል በማሰብ፣ ይህን የቃለአጋኖ ንግግር ሙሴ ማቼ ሳለመተርጎም ብልህ ውሣኔ አደረገ።

«ታምሜ ስለነበረ ወደ ካይሮ ለሕክምና መጣሁ። የአረብ ሃኪሞች መድሃኒት ሊያገኙልኝ አልቻሉም። እነርሱን በምንም መልኩ አላምናቸውም። ሁልጊዜም ማስበው ፈረንሣውያን ሃኪሞች የበለጡ አዋቂዎች ናቸው። በናንተ ማህበረሰብ ውስጥ ሣፈላልግ የሆነ ሰው የአንድ መነኩሴ ስም ሰጠኝ። የተባለውን ሰው ሳገኘው ሄድኩ። የለበሰው የኔ አገር ሰዎች የሚለብሱትን ዓይነት ቢሆንም፣ ካባው ግን ቡኒ ሆኖ ወገቡን በገመድ ታጥቋል።»



«ካፑቺን ነው?» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ ትዕግስት አጥቶ ጣልቃ በመግባት

«ሊሆን ይችላል። እዚህ አገር እነርሱ ብዙ ናቸው። እኔ የምለው ሰው ግን ሽማግሌና ዐይኑ-ሥውር ሊሆን የተቃረበ ነበር። በሙሃመድ የሚያምኑትን ለማከም ይፈቅድ እንደሆነ ጠየቅሁት። አዎን አለ። በርግጥም አከሞ አዳነኝ»

«ይህን ሁሉ በማወቁ በጣም ደስ ብሎኛል። የርስ የጤንነት ጉዳይ እኛን የሚመለከተን አለመሆኑን ንገረውና ደህ የሚነግረን ታሪክ ከኛ ጉዳይ ጋር ምን አግባብነት እንዳለው ጠይቀው»

«በመስከረሙ ቅናሉት ወደ አቢሲኒያ ተመለስኩ። ደርሼ ሳልሰነብት ንጉሡ ጠራኝ። ባልተለመደ አኳኋን ለብቻ እንዳነጋግረው ጠየቀኝ። በጭውውታችን ጊዜ እርሱ ራሱ መታመሙን ነገረኝ። ሕመሙ እኔ የታመምኩትንና በፈረንሣዊው መነኩሴ ታክሜ የዳንኩት ዓይነት ነበር»

«እና አንድ ዶክተር ለመውሰድ ወደ ካይሮ ተመለስክ?» አለ ሙሴ ማይሌ፣ ፊቱ ሣምባ መስሎ።

ሃጂ አሊ ጥያቄውን በአዎንታ መመለሱን ለመግለፅ በአክብሮት ዝቅ አለ።

«አግኝተኸው ወይም አላገኘኸውም እንደሆነ ብትነግረን?» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀ።

«እንዳለመታደል ሆኖ» ሲል ሃጂ አለ ሃዘኑን አጉልቶ ሊገልፅለት በሚችል የድምፅ ቃና ተናገረ። «እኔን ያዳነኝ ሽማግሌ ከመሆኑም በላይ ልፁ . . . »

«ታድያ ምን ለማድረግ ወሰንክ?» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀ

«እጠብቃለኋ! ማንም ሰው እምነት ካለው አላህ የሚያስፈልገውን ይሰጠዋል»

«እምነትህ የሚመሰገን ነው። አሁን የምንነጋገረው ግን ደህ ስራችን በዓለማዊው አኳኋን እንዴት ሊሆን ይችላል የሚል ነው»

«እኔን ያዳነኝን የሚመስል ሌላ ዶክተር በቅርቡ እንደሚመጣ ሌሎች ፈረንሣውያን መነኩሴዎች ቃል ገብተውልኛል። ይህ የነርሱ እምነት አባል የሆነ ሰው ከእየሩሳሌም ስለሚመጣ እየጠበቅሁት ነው። ስውዬው በማዳን ችሎታው ስሙ የገነነ ነው። እስከአሁን አሌክሣንድሪያ አካባቢ መጠጋት ይችላል። ቢበዛ በአሥር ቀናት ውስጥ እዚህ ይደርሣል።»

«ምን ዓይነት መታደል ነው» አለ ሙሴ ዴ ማይሴ።

«ይህ ሰው በመምጣቱ በጣም ደስተኛ ነኝ። ምክንያቱም የበፊቱ ዶክተር የሰጠኝ መከላከያ እያለቀ ስለሆነ አዲስ እፈልጋለሁ።»

«ይህ የምትለው ህመም ምን እንደሆነ ማወቅ ይቻላል?» ሲል ቆንሲሉ ሙሴ ማቼን ጠየቀው። ጥያቄው ለነጋዴው በዙሪያ ጥምጥም እየተነገረው ቢሆንም በተቻለ መጠን ተተርጉሞ ተነገረው።

«ሕመሜ ምስጢር አይደለም። እንደምታውቁት ንጉሡም የሚሰቃየው በዚሁ በሽታ ነው። ንጉሡን ካልካድኩ በስተቀር የበሽታውን ባህርይ መግለፅ አይገባኝም። ልትገነዘቡት የሚገባችሁ በሽታው ገዳይ በሽታ አይደለም። ግን የአዕምሮ ሰላምና ምቾትን ይነሣል። ፀባይንም ብስጩ ያደርጋል። እንዲህ ያለው ህመም በአገር መሪ ላይ ሲሆን አለመታደል ነው»

በሚቀጥለው ዕለት እንደገና ለመገናኘት በመወሰን፣ በአሥራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ሙሴ ማቼ፣ ነጋዴውን ወደ ማረፊያው ወሰደው።

ሙሴ ዴ ማይሴ፣ ሲገመት ከሚችለው በላይ ተደሰተ። እንኳን ደስ አለህ በማለት ሲያሞቀው፣ ፀሐፊውም ከጀርባው ዝቅ በማለት ተቀበለው። አንዳችም የማጥላላት ነገር ሳይጨመርበት የሙሴ ዴ ማይሴን ሕይወት ለማዳን የኢምባሲውን እቅድ መልሰው ለማሻሻል ቻሉ። የንጉሡን ችግርና ከዚሁ ጋር ተያይዞ አንድ መልዕክተኛ እንዴት ሲደርሰው እንደሚችልም አውቀዋል። ከዚህም በላይ መልዕክተኛው የካቶሊክ መነኩሴ መሆን አለበት። ይህ ሉዊስ 14ኛን ያስደስተዋል። ሁለቱም ሰዎች ለዲፕሎማቲክ ችሎታው በጣም ከፍተኛ ነጥብ ሰጡ። ከዚህ በኋላ የሚፈልጉት ቢኖር ይህን መልካም ዜና ለጄስዊቱ ቄስ ሽፋፍነው ማቅረብ ብቻ ነው።



«በነገራችን ላይ፣ ህመሙ ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ?» ሲል ሙሴ ዴ ማይሴ ጠየቀው

«በኔ አስተሣሰብ ሃጂ አሊ የቆዳ ሕመም ችግር አለበት። ያለጥርጥር እንዳስተዋልከት፣ ባለማቋረጥ የቀኝ ጉንጉን ያከክ ነበር። ሻዩን ለማንሣት እጁን ሲዘረጋ፣ በክርኑ አካባቢ በአገራችን ደኖች ውስጥ በዛፎች ቅርፊት ላይ ያለውን የእንጨት ሽበት የመሰለ ሽፍታ ያስተዋልኩ ይመስለኛል።»

«ይሁና! ለማንኛውም የሰውነት ቆዳውም ይሁን ሌላ የሰውነቱ ክፍል ብዙም ልዩነት አያመጣም» አለ ቆንሲሉ

ወዲያውኑ ተነስተው ለአባ ቬርሣው ለመንገር ወደ ፎቅ ወጡ። ቄሱ፣ እጆቻቸውን በሆዳቸው ላይ አጣጥፈው የሚነግሯቸውን መግለጫ በትህትና አዳመጡ። ሙሴ ዴ ማይሴ፣ የፈረንሣዩን ሃኪም ጉዳይ የሚገልጹበት ደረጃ ሲደርስ ደቃቃው ሽማግሌ የሚጥል በሽታ እንዳለበት ሰው ፈርተው ዘለሉ። በመጀመሪያ ላይ በጣም ያስደነቃቸው ነገር እንዲያ ያለ ደካማ ሰውነት ያንን የመሰለ ማዕከላዊ ቁጣ ከውስጡ ማመንጨት መቻሉ ነበር። በኋላ ላይ ግን እንዲህ ያለ ቁጣ የሚያደርግ ምላሽ የሚፈጥር ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ማውጠንጠን ቀጠሉ። ይህ ሁሉ የጀመረው ሙሴ ማይሴ ከአፉ «ካፑቺን» የሚለው ቃል እንደወጣ መሆኑን አስታወሱ።

# 5

ካፑቺኖዎች በራሣቸውና በትክሻቸው ላይ ጣል በሚያደርጉት የአንገት ልብስ ተለይተው ይታወቃሉ። በኢጣሊያንኛ ካፑቹዮ ሲባሉ፣ ከፍራንሲስካውያን ተከታይነት በተሃድሶ ተለይተው የተመሰረቱ መነኩሣት ናቸው። በቅድስት አገር በተፈፀመ ችግር ተተብትበው በመያዛቸው፣ በግብፅ አገር የሚገኙ ካፑቺኖዎች በቁጥርም፣ በፖለቲካ አቅማቸውም በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ በጣም ቀንሰዋል። ይህ ጉዳይ በሙሴ ማይሌ ዘንድ ይታወቃል። ከአገሪቱ ፍፁም ተጠርገው እንዳይጠፉ በመስጋት፣ ካፑቺኖዎች ጥሩ ያልሆነ የማምለጫ ብልሃት መፍጠራቸውንም ያውቃል። ሮም ድረስ በመጓዝ ጳጳሱ በግል እንዲያማልዷቸውም ጠይቀዋል። በሺህዎች የሚቆጠሩ አቢሲኒያውያን ካቶሊኮች፣ ከሃምሣ ዓመት በፊት የጀስዊት ተከታይ ሆነው ነበር። ነገር ግን፣ የኢየሱስ ማህበረሰቦችን ንጉሡ ከአገር ካስወጣ በኋላ አማንያኑንም እያስቃያቸው ስለሆነ ከሃገራቸው እየተሰደዱ ናቸው በማለት እነዚሁ ወገኖች ጳጳሱን ለማሣመን ችለው ነበር። እንደ ካፑቺኖዎች አገላለጽ፣ እነዚህ በጀስዊት እምነት ሳቢያ ሰለባ ሆንን የሚሉ ሰዎችና የኢትዮጵያ መናፍቃን የጭካኔ ሥራ፣ ለመኖር ሲባል የተደረገ ስልት ነው። በዚህ ሣቢያ ለኑሮ አመችነት በሌለው ከግብፅ በስተደቡብ በሲናር ምድርና በአቢሲኒያ ድንበር አካባቢ ተበትነዋል። እነዚህን ሰዎች ሌላ ማንንም ያያቸው ባይኖርም፣ መነኩሣቱ ግን መኖራቸውን ስላረጋገጡ፣ ካፑቺኖዎች እነዚህን የተበተኑ ካቶሊካውያን ለመታደግ ጥያቄ አነሱ። ለዚህ ተልዕኮአቸው፣ ጳጳሱ በአፋሴል ሥልጣን እንዲሰጧቸውም አቤቱታ አቀረቡ። የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ጳጳስ አቡነ ኢኖሴንት 12ኛ፣ እነዚህን በትምህርታቸው ያልገፉ መነኩሣት በጥሩ መንፈስ ሰላዩዋቸውና ብዙዎችም ማስተዋል ያለባቸው ኢጣሊያውያን ስለሆኑ፣ አቤቱታቸውን ተቀብለው ፈቀዱላቸው። ከዚያም ወደ ደቡብ በማቅናት በላይኛው ግብፅ አካባቢ አንድ የእንግዳ ማረፊያ ቤት ይከፍታሉ። በአንድ ወቅት በአገሪቷ ውስጥ ፍፁም እንዳልነበሩ ሁሉ፣ ዛሬ ደግሞ ከመቸውም በበለጠ ሃይል ተጠናክረው ተመልሰዋል።



እምብዛም ክብደት አይሰጠው እንጂ፣ የካፑቺኖዎች እቅድ እዚያ ላይ እንደሚያበቃም ሙሴ ዱ ማይሌ ያውቃል። ዋናው ግባቸው በስደት ላይ የሚገኙትን አቢሲኒያውያን ለመርዳትና ለመታደግ ሣይሆን፣ አቢሲኒያን ራሷን ወደ ካቶሊክነት ለመለወጥ ነው። ጳጳሱም፣ ይህን እቅዳቸውን በመደገፍ ስላበረታቷቸው፣ ወደ አቢሲኒያ ለሚጓዙ የካፑቺኖ ሚሲዮናውያን ፍላጐት የሚያግዝ፣ ያልተቋረጠ የገንዘብ ድጋፍ እንዲደረግለት መላ ፈጥረዋል። ይህ እንቅስቃሴያቸው ደግሞ ከጀስዊቶች ጋር ቀጥታ ፉክክር ውስጥ ያስገባቸዋል። ጀስዊቶች በበኩላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የገጠማቸውን ሽንፈት ፈፅሞ ባለመቀበል አንድ ቀን እንመለሣለን ብለው የሚያምኑ ናቸው።

በግብፅ ውስጥ የሚኖሩ ጀስዊቶች ጥቂቶች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች በኑሪያቸው ካሉት ሁሉ ጋር በሰላምና በግልፅ በሚታወቅ ወዳጅነት ይኖራሉ። ከሌሎች የሃይማኖቱ ቅርንጫፎች ጋር ይህን ያህል የጠነከረ ፉክክር፣ ቢያንስ በከፍተኞቹ የሥልጣን አካላት መካከል ይኖራል ብሎ ቆንሲሉ ገምቶ አያውቅም። «ካፑቺን» የሚለው ቃል ሲጠቀስ፣ በአባ ቬርሣው ላይ የታየው የቁጣ ስሜት ግን፣ ሙሴ ማይሌ ስለ ፉክክሩ የነበረው ግንዛቤ ምን ያህል የተሣሣተ እንደነበረ በግልፅ የሚያሣውቀው ሆነ።

«የፈረንሣይ ንጉሥ መልዕክት፣ በኢጣሊያውያን በኩል ይተላለፋል የሚለው ጉዳይ ከጥያቄ ውጭ ነው። ከዚህም በላይ ተልዕኮው የኛና የኛ ሃይማኖት ቅርንጫፍ ሃላፊነት ብቻ ነው። በዚህ ነጥብ ላይ የንጉሡ መመሪያ እንዳችም ስህተት የለበትም። የተፈጥሮ ጉዳይ ሆኖ ስለራሴና ስለተግባሬ ያስመግለፅ ሁኔታ ስላለብኝ እንጂ፣ በሮም በኩል አቋርጬ ወደዚህ ስመጣ ብፁዕ ወቅዱስ የሮማን ጳጳስ በአካል አግኝቻቸው ነበር» ሲሉ ቁጡ ሃይል በተቀላቀለበት አነጋገር አስገነዘቡ።

አስቀድሞ ሲታሰብ ይሆናል ለማለት ቢያስቸግርም፣ አሁን የተገለፀው እውነታ የጀስዊቶች ክብር ከፍ ያለ መሆኑን በሙሴ ዱ ማይሌ ዓይን እንዲታይ አደረገው። ቆንሲሉ፣ መላ አካሉን አድናቆት ቢሞላውም፣ የልምድ ማነስ የፈጠረበት ሃፍረትም ስሜቱን አሣመመው። ከዚህ በኋላ የኒህን የጀስዊት ቄስ ቃላት፣ በሙሉ መንፈሣዊ ምርኮኛነት ለመስማት ተዘጋጀ።

«የፈረንሣይን ንጉሥ በመጠከል በመቅረቤ፣ ጳጳሱ መስማማታቸውን አረጋግጠዋል። ከዚህም ባሻገር፣ አቢሲኒያ፣ ባለመታደል ከሰመጠችበት የመናፍቅነት መከራ ሊያድናት፣ የኢየሱስ ማህበረሰቦች ለሚወስዱት እርምጃ ቡራኬአቸውን ሰጥተዋል»

በሐሩር አውራጃ አገሮች ምሽት ፈጥኖ ይደርሣል። ክፍሉን የሞላው ድንግዝግዝ ያለ ብርሃን፣ ለቄሱ ቃላት ይበልጥ ክብደት አከለበት።

የዚህ ሁሉ እውነታ ማጠንጠኛው፣ ሕዝብን በመንፈሣዊ ሥርዓት ውስጥ ለማምጣት የሚደረግ ዳግም ጥረት፣ እንደ ሃቀኛ እምነት እንዲቀጥል ማድረግ የሚቻለው፣ ከምድራዊው ፍላጐት በላይ በሆነውና ተፎካካሪ በሌለው ሃይል ፈቃድ ሲሆን ነው። ይህ ዓይነቱ ሃይልና አቅም ያላቸው ሳያዳሉ ዕቅዱን ማሣካት የሚችሉት በዘመናችን ታላቁ የካቶሊክ ንጉሡ ነገሥት የሆኑት የፈረንሣዩ ንጉሥ ብቻ ናቸው። ሌላው ነገር ሁሉ የሚመነጨው ከዚህ ታላቅ እምነት ነው። በፁዕነታቸው ይህን የተቀደሰ ነው ብለው ተቀብለውታል። የኛ ቅርንጫፍ ደግሞ በታላቅ ትህትና ይተገብረዋል፣ ሲሉ ጠንካራ ሃይማኖተኛነታቸውን በሚያሣይ መልክ ገለፁ።

ቄሱ፣ ለአፍታ ያህል ንግግራቸውን ገታ ካደረጉ በኋላ፣ በድምፃቸው ውስጥ እለመደሰታቸውን ሊያመለክት በሚችል ቅላፄ «ከታች በማይማን ቀሣውስትና በደካማ መንግስት ዜጐች እየተመራ እንዲንቀሣቀስ የሚደረግ አዲስና ልዩ ዕቅድ፣ ሲበዛ ሰብዓዊ በሆኑ ምክንያቶች የሚሰራ ስለሆነ ምንም ልትረዳው አትችልም»

የመጨረሻውን ዓረፍተ ነገር ሲደመድሙ ቄሱ ቁና ተነፈሱ። ሙሴ ዱ ማይሴ ትንፋሹን ውጦ ፍፁም ተረበሸ።

«ሥራህ ተስፋ በሚሰጥ መልክ ቀጥሏል» ሲሉ የጀስዊቱ ቄስ ከፍ ባለና ተመልሶ ወዳጃዊ በሆነ ቃና ንግግራቸውን ቀጠሉ። «ከዚህ ነጋዴ ጋር ተጐዳኝቶ በሚሄድ ሃኪም ትክሻ ኤምባሲያችንን ማድረጉ እጅግ ድንቅ ሃሣብ ነው። ይሁንና ሃኪሙ ፈረንሣዊ መሆን ሲኖርበት የኛ እምነት ተከታይም አብሮት ሲሄድ ይገባል።»

አገልጋዮች የፋና መብራት ይዘው በመግባታቸው የሁለቱ ሰዎች ውይይት ተደናቀፈ። ንግግራቸው እዚህ ላይ ሲቋረጥ ርዕስ ጉዳዩም ተዘጋ።



እራት በታላቅ ክብር ቀረበ። ቄሱ ስላደረጓቸው ጉዞዎች ብዙ ታሪኮችን አወጉ። ሴት ወይዛዝሮች ስለ ቬርሣይለስና ስለ ሮም ይጠይቃሉ። ቄሱ፣ ትኩረታቸውን ይበልጥ ወደ ማዳሞዜል ዱ ማይሴ በማድረግ ብልህነታቸውን አስመሰከሩ። የልጃገረዲቱ አባት፣ በቄሱ ላይ የአገራዊ ስሜት ዝንባሌ እንዳለ ስለተረዳና በዚህ ነፃ የሃይማኖት ሥርዓት ገለፃ፣ የወጣቶችን ነፍስ ለመምራት በመቻላቸው ስሜቱ ተደሰተ።

ቬርሣው፣ በዚያን ጊዜ ካይሮ ውስጥ ሊገኙ እንደሚችሉ የሚያውቋቸውን ሁለት ጀስዊቶች ለማየት መጓጓታቸውን አባ ገለፁ። ምናልባት በማግስቱ ያኟቸው ይሆን? ሙሴ ማቹ፣ የቄሱን መልዕክት ለነዚህ ለሚጠበቁ ጀስዊቶች ለማድረስ ቃል ገባ። ግብዣው በጊዜ ተጠናቀቀ። ቆንሲሉም በቢሮው ውስጥ ብቻውን ቀረ። በአዕምሮውም ውስጥ አስፈሪ የሆነውን እውነታ ለረዥምም ጊዜ አውጠነጠነ። ይህን እውነታ ከዚህ በፊት እምኖ ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም። ጀስዊቶች ወደ አቢሲኒያ ኤምባሲ ሲላክ የሚያጋጥመውን የሚታወቅ አደጋ ቸለል የሚሉ ብቻ ሣይሆን፣ አገር ሁሉ ጠልቷቸው እያለም ራሣቸው ወደዚያው ለመሄድ ይፈልጋሉ። ይህ ሁሉ ይቅርና፣ ሙሴ ዱ ማይሴን አሁን የገጠመው መጥፎ ጣጣ፣ በፈረንሣውያን ማህበረሰብ ውስጥ አንድ ፈረንሣዊ ዶክተር የማግኘት ጉዳይ ነው። በርግጥ ደግሞ አንድም የለም።

ከማለዳው አንድ ሰዓት ሲሆን የለሊቱ ቅዝቃዜ ቀስ እያለ ሲወገድ፣ ከተማዋ በሞቃት ብርሃን ተሞላች። በፈረንሣውያን መኖሪያ አካባቢ በሚገኙ ትላልቅ ዛፎች ላይ የሰፈሩ ወፎች፣ በመገፈፍ ላይ ባሉ ጥላዎች ሥር ባለማቋረጥ ይዘምራሉ። ምንም እንኳ የእግር እርምጃ ያንቀሣቀሰው በአየር ውስጥ ተንሣፍፎ ቢቀርም፣ ገና ከመሬት ላይ አልተነሣም።

ሜትር ፑረሚ፣ በአሸዋማው የመንገዱ ጠርዝ አጠገብ በሚገኙና ዝርግት ባሉ ዛፎች ጥላ ሥር አቋርጦ፣ የፀሃይ ብርሃን በዛፎች ቅርንጫፎችና ቅጠሎች ተቆራርጦ በሚታይባቸው ቦታዎች ላይ ወዲያና ወዲህ ይራመዳል። በቀዝቃዛ የውቅያኖስ ውሃና በሞቃት አየር መካከል እንደሚቦርቅ ዶልፊን ደስተኛ ነው። ምንም ዜማዊ ቃና የሌለው ፉጨት ይፏጫል። አንዲት

ትንሽ የልብስ ክረጢት ይዟል፡፡ የቆንሲሉ አሽቃባጮች እንደተተነበየው ቆንስላው ጽሕፈት ቤት እንዲገኝ የሚያገዘውን መጥሪያ ይዘው ትናንት ማታ መጥተው ነበር፡፡

በመጨረሻው ሰዓት ላይ ሜትር ዠረሚ የጓደኛውን የጆን ባፕቲስትን ብልሀ ምክር ተቀብሏል፡፡ በአንድ አነስተኛ ከረጢት ውስጥ የንፅህና ዕቃዎችን፣ ንፁህ ሸሚዝና የኪስ መፅሃፍ ቅዱስ በመያዝ ከሰዓት በኋላ በግዴለሽነት አሣ ለማጥመድ እንደሚሄድ ሰው፣ እርሱም ወደ እሥሩ ተዘጋጀ፡፡

በቆንስላው መግቢያ ላይ አንድ አገልጋይ መጥቶ በክብር ወሰደው፡፡ አስቀድሞ ወደ ሁለተኛው ፎቅ መራው፡፡ ከዚያም በላይኛው አዳራሽ ውስጥ ባለ አጭርና ስውር በር አልፈው አንዲት ትንሽ ክፍል ውስጥ ገቡ፡፡ ክፍሉ ቅዝቃዜ ያለው ነው፡፡ በክፍሉ መሃል ላይ ስፊውን ቦታ ይዞ የሚገኝ የምግብ ገበታ የሚሆን ጠረጴዛ አለ፡፡ ዙሪያውን፣ ማይሴ በሚል ጉትያ ጥልፍ ያጌጠ ነጭ የጠረጴዛ ልብስ ለብሷል፡፡ የሚያብረቀርቁ የመስተዋት ብርጭቆዎች፣ የፍራፍሬ ጭማቂ የያዘ ብሩህ የመስታወት ጆግ፣ ሁለት የሸክላ ስኒዎችና ትኩስ ዳቦ ተቀምጧል፡፡ የታዘዘውን ለመፈፀም ዝግጁ የሆነው አገልጋይ ወንበር ስቦ ሜትር ዠረሚ እንዲቀመጥ ጋበዘው፡፡ ነገር ግን መድሃኒት ቀማሚው እምቢ አለ፡፡ አንዳች የተፈጠረ ስሀተት ስላለ በአስቸኳይ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ክፍሉና የሚታየው ዝግጅት ስሀተት እንደሆነና እርሱ ወደመታሠሪያው መሄድ እንደሚፈልግ መናገር ሲጀምር አገልጋዩ ልጅ ከአጠገቡ ፈጥኖ ሄደ፡፡

ቆንሲሉ ብዙም ሣይቆይ ደረሰ፡፡ ሲያዩት ጤናው ጥሩ አይመስልም፡፡ ዓይኖቹ ቀልተዋል፡፡ መሆን ከሚገባው በላይ ፊቱ ተኳኩሷል፡፡ ስሜቱ በተለየ ደስተኛ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡

«ሜትር ዠረሚ! ስላገኘሁህ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ታዲያ ምነው መቀመጫ አልተሰጠህ? እባክህ ቁጭ በል!»

ደነገጠ፡፡ አለማመኑን ሙሉ በሙሉ ሣይተው፣ ባለመድሃኒቱ ረዥም አካሉን በሚያስደስት አኳኋን እጣጥፎ ወንበር ላይ ተቀመጠ፡፡ ቆንሲሉ፣ መዓዛው ውብ የሆነ የሚንት



ሻይ አዘዘ፣ እንግዳውን ከመጠን በላይ መንከባከብ ሞከረ፡፡ ወተት፣ ስኳርና የማማሰያ ማንኪያ ሰጠው፡ የፍራፍሬ ጭማቂውንም በሁለቱም ብርጭቆዎች ውስጥ በራሱ እጅ ቀዳ፡፡ ያችን ቀጭን ሹል ጉራዴውን ባለመያዙ ሜትር ዠረሚ አዘነ፡፡ እርሷን ይዞ ቢሆን ኖሮ ይህን ሁሉ ቧልት በአንድ ውግ ከፍፃሜ ያደርሰው ነበር፡፡

«እኔ በሌለሁበት የተሰራ ቢሆንም ያከናወንከው ተግባር እጅግ በጣም ድንቅ ነው» አለ ሙሴ ዴ ማይሴ ቅንድቡን ከፍ አድርጎ፡፡

ሜትር ዠረሚ የሚሰጠውን መልስ አላወቀም፡፡ ለራሱ እርጋታ እንዲሰጠው በማሰብ የቀረበለትን ብስኩት በአፉ ሙሉ ጉረሰና ጠበቀ፡፡ ምን ይከተል ይሆን በሚል ስጋት አፉን ዘጋ፡፡

«ሥራህ ትልቅ ችሎታ የሚጠይቅ ነበር፡፡ የተለያዩ ዕፅዋትን አዋህዶ የተለያዩ ማባበቂያዎች /ሙጫዎች/ እንዲሆኑ ማድረግ፣ መቀባትና መወልወል በእውነቱ ትልቅ ክህሎትን የሚጠይቅ ነው»

ሜትር ዠረሚ ጭንቅላቱን አንዴ ወደ ቀኝ፣ አንዴ ወደ ግራ እያጋደለና ትክሻውን እየነቀነቀ ማላመጡን ቀጠለ፡፡

ምን እንደሆነ እንጃ እንጂ፣ በቆንሲሉ አዕምሮ ውስጥ አንድ ነገር አለ፡፡ ዲፕሎማቱ፣ በአንድ ትልቅ ስኒ ውስጥ የተቀዳውን ቡና በአንድ ትንፋሽ ሲጨልጠው፣ መድሃኒት ቀማሚው በበኩሉ የተጠራበት ጉዳይ ከዚህ በኋላ እንደሚቀጥል በልቡ አሰበ፡፡

«እነዚህን ቅይጦች ለብዙ ጉዳዮች እንዲጠቅሙ ማድረግ ይቻላል፡፡ በዚህም ላይ ሌላው ቀርቶ መድሃኒት እንደምትቀምምም ስትናገር ጆሮዬ ውስጥ ጥልቅ ብሎ ነበር፡፡ ተሣሣትኩ?»

እንግዲህ ጀመርን ማለት ነው፣ ሲል ሜትር ዠረሚ አሰበ፡፡

ከኋላዋ የሚገኝ ቁጥቋጦ ድንገት የተተረማመሰባት መስሏት የበረገገች ድኩላ ይመስል፣ ቁና ቁና መተንፈስ ጀመረ፡፡

በአገልግሎት ብዛት የወየበች አንዲት ትንሽ መሃረብ ከኪሱ አውጥቶ አፉን እየጠረገባት «አይዞህ አትፍራ!» አለው ቆንሲሉ። «ከኔ በፊት የነበሩት ሃላፊዎች፣ ተገቢው ቅድመ ፈቃድ ሳይኖራቸው በመድሃኒት ቅመማና ንግድ ወይም በሕክምና ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩትን አንዳንድ ባልደረቦችን በተመለከተ በጣም ይቆጣጠሩ ነበር። እኔ ራሴም ብሆን ጠንቃቃ ልሁን እንጂ በዚህ ሁኔታ ላይ በዙሪያችን ብዙ አስመሣዮች ስላሉ ሃላፊነታችንን በትክክል መረዳት ይኖራል ብዬ አስባለሁ። አንተስ ምን ትላለህ?»

ሜትር ዠረሚ ቅንድቦቹን ሁለት ጊዜ አርገበገባቸው። ይህ ማለት በሃሣቡ መስማማቱ ነው ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ አሰበ።

«አንተን በሥራ ላይ ነው ያየሁህ። ያውም በሥዕል ቅብ ሥራ ላይ። ይህ እውነት ነው። ከዚያ ወዲህ አዕምሮዬ ወሰነ። ስላንተ ያገኘሁት መረጃም በጣም ትክክል ነበር። ከዕፅዋት የፈውስ መድሃኒቶችን መቀመምህን ብታረጋግጥልኝ ሙሉ ድጋፌ እንደማይለይህ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ። ቃሌንም የማከብር ሰው ነኝ። ይህንንስ ታውቃለህ?»

«አዎን፣ ክቡር ሆይ» አለ ሜትር ዠረሚ በብዙ ጥረት።

«እንግዲያው በግልፅ አነጋግረኝ። በስፋት እንደሚነገረው በርግጥ እፅዋትን ለመድሃኒትነት በማዘጋጀትና የነዚሁኑ መድሃኒቶች አዘገጃጀትና ጠቀሜታ ልምዱ አለህ?»

«እንደዚያ ብዬ አምናለሁ» አለ ቀማሚው

«እንደዚያ ያምናል! ምን ዓይነት ትህትና ነው። ከሚታየው በበለጠ እንደሆንክም ሰምቻለሁ። ማህበረሰቡ ከሚኖርባቸው ከተለያዩ ቦታዎች እየመጡ የሚጎበኙህ ሰዎች፣ ሌላው ቀርቶ ፖሻው ምክር እንደሚጠይቅህ ሰምቻለሁ።»

ሜትር ዠረሚ መሬት መሬት ማየት ጀመረ።

«በዚህ ቅር አትሰኝ። ይህ ድንቅ ነው። በጣም ድንቅ ነው። እንዲህ ያለ ችሎታ አለህ ብዬ ጨርሶ አልጠረጠርኩም ነበር። ትህትናህ የሚደነቅ ነው። ትናንትና ማታ መጠነኛ



የጤና መታወክ ደርሶብኝ ነበር። ስለመድሃኒት ስንነጋገር ባለቤቴ ማዳም ዴ ማይሌ፣ እኔ ሣላውቀው ከስድስት ወራት በፊት ጠርታህ አድነሃት እንደነበረ ነገረችኝ»

በእንግዳው ፊት ላይ የሥጋት ሁኔታ ስላየበት ቆንሲሉ በጣም በተረጋጋ ቅላፄ መናገር ጀመረ።

«እውነቱን ነው። አትፍራ! እንዴት ላግምንህ እንደምችል ግራ ይገባኛል። የምሥራች ብዬ መልካም ምኞቱን አቀርባለሁ። ከዚህ በተረፈ በዚሁ እንድትቀጥልበት አደፋፍርሃለሁ።»

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ከመቀመጫው ብድግ በማለት ወደ መስኮቱ ከተራመደ በኋላ ዞር ብሎ፣ «ለምሣሌ ጥቁር ሰዎችን የሚያጠቃውን እንደቁምጥና ዓይነት ያለውን የቆዳ በሽታ የማዳን ችሎታ አለህ?»

«እንዴት ልገልፅም እችላለሁ? ይህን ነገር የምንሰራው ሁለት ሆነን ነው፣ ክቡር ሆይ።» ሲል ሜትር ዠረሚ በመጨረሻ አጉተመተመ።

«ምን ማለትህ ነው?»

«ሽሪክ ጓደኛ አለኝ።»

«ጥሩ። ገባኝ፣ጥያቄዬን በትዕግስት መልስልኝ»

«ነጥቡ ክቡር ሆይ! የመድሃኒት ዕውቀቱ ያለው ጓደኛዬ ነው። እርሱ ለህመምተኞች መድሃኒት ያገዛል። እኔ መድሃኒቱን እቀምማለሁ። ለምሣሌ ማዳም ማይሌን በተመለከተ ችግሩን ገለፅኩለት። እርሱ የሚያስፈልጋቸውን ነገረኝ። ቅባቱን አዘጋጅቼ አመጣሁላቸው። የኔ የተሣትፎ መጠን ይህን ያህል ነው።»

ቆንሲሉ ወደ ጠረጴዛው ተመልሶ ወንበሩ ላይ ተቀመጠ።

«ገባኝ። እንዲህ ከሆነ ይህን ሽሪክህን ማነጋገር ይኖርብኛል ማለት ነው?»

«ልገልፅም እሞክር የነበረውም ይህንኑ ነው፣ ክቡር ሆይ» ሙሴ ዴ ማይሌ ከውይይቱ ያተረፈው የጋለ ስሜት በአንድ ጊዜ ቀዘቀዘ።

«ስሙ ማን ይባላል?»

«ፖንሴ ይባላል፣ ክቡር ሆይ። ጆን ባፕቲስት ፖንሴ»

«ታዲያ የት ነው ላገኘው የምችለው?»

«ደባሎች ነን። እርሱ በላይኛው ፎቅ ላይ ሲኖር፣ እኔ በታችኛው ወለል ላይ እኖራለሁ።»

«ቤተ-መኩራችሁስ?»

«አ! ክቡር ሆይ! በሕይወታችንና በሥራችን ላይ ያለውን ለያይቼ ለመግለፅ እጅግ ይከብደኛል። ይህን ልገልፅዎ ይከብደኛል . . . »

ቆንሲሉ ለረዥም ጊዜ በሃሣብ ውስጥ ሰመጠ።

«ለመሆኑ ይህ ጓደኛህ፣ ረዥም ጉዞ ለማድረግ ፈቃደኛ የሚሆን ይመስልሃል?»

«ክቡር ሆይ፣ ይህንንማ እርሱን መጠየቅ ይገባል። እርሱ . . . የተለየ ዓይነት ሰው ነው። ሽሪሉ ባልሆን ኖሮ . . . ብቻ የተለየ ተሰጥኦ ያለው ሰው ነው።»

«የተለየ ተሰጥኦ! አትለኝም!»

እነዚህ የጀብድ ሰዎች እኮ ስለምንም ነገር አይጨነቁም ሲል ሙሴ ማይሌ አሰበ።

«ልታመጣው ትችላለህ?»

«እርስዎ ከጠየቁ ይቻላል። እኛ እኮ የንጉሠ ነገስታችን ተገዥዎች ነን። እርስዎ ደግሞ የንጉሠ ነገስታችን ሹመኛ እንደራሴ ነዎት»

እንዳችም የሚያስከትለው ውጤት ከሌለውና የራሱን ልብ ሳያሞቅ፣ ይህን የመሰለ የሙያ ታማኝነት ሊሰማ አይችልም። ታዲያም ይህን የመሰለ ታማኝነቱን በግልፅ ላቀረበ ሰው ፈፅሞ ውሸታ ቢስ መሆን አይገባም። እንግዲህ ንጉሣዊ አገዛዙን አፅንቶና አስማምቶ ማኖር



የሚቻለው፣ አስደሳች ባለሥልጣን በአመስጋኝ ሕዝብ ላይ ሲኖር ነው፣ ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ አሰበ።

«እንዲህ ከሆነ ሽሪክህን እዚህ በአምስት ሰዓት ላይ እንደምጠብቀው ንገረው» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ።

«እንደክቡርነትዎ ፈቃድ እሺ። እና ግን . . . »

ሚትር ዠረሚ አቅማማ። ቆንሲሉ ተንኮል ያሰበ አይመስልም። የጆን ባፕቲስትን እውነተኛ የሙያ ምስጢር ማዋየቱ እንዳችም እሱታዊ ገፅታ የለውም። ችግሮችን የመቀስቀስ ሁኔታ የሚፈጠረው በተለይ በጓደኛው ባህርይ ማቢያ ነው። «እኔን ቢጠራኝ ኖሮ አልሄድም ነበር» በማለት ጆን ባፕቲስት ከትናንት በስቲያ ማታ ባይናገር ኖሮ ጥሩ ነበር።

«እና ግን?» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ ትዕግስት በማጣት

«እና ግን ጓደኛዬን ፖንሴን ደህና አድርጌ ስለማውቀው ሌላ ዘዴ ባቀርብስ?»

«ምን ዓይነት?»

«ክቡርነትዎ፣ ወደ ቤታችን፣ ማለቴ ሁለታችን ወደምንኖርበት ቤት፣ እርስዎ በሚፈልጉት ጊዜ እንዲገኝ ካዘዙት አለቅጥ ባለውለታዎ ስለሚሆን እንዳችም ነገር እምቢ አይልዎትም»

«እንግዲያው አዝዣለሁ። ሲፈልግ ተመልካችና አድማጭ ተፈቅዶለታል»

እንዳችም አለማለት እርቆ አለማሰብ ነው፣ ሲል ዠረሚ ገመተ።

ይህ ድንቅ ነው። የማይመስልና እንዲያውም የሚያምፅ ዓይነት ነው። ነገር ግን ይህ ጉዳይ ድንገተኛ ስለሆነና ሰውዬውም የአሽናፊነት ሚና ስላለው፣ እርሱ በመረጠውና ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሚንቁትን መቀበል ግዴታ የሚሆንበት ጊዜም አለ። ሲል ቆንሲሉ አሰበ።

«በአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሊደርስ ይችል ይሆን?» ሲል በጣውን አጠንክሮ ሙሴ ዴ ማይሌ ጠየቀ።

# 6

ሰረገላው፣ በግቢው ውስጥ በተነጠፈው የጣውላ ሣንቃ ላይ ቆሞ ይጠብቃል። በጣም ግሩም ሠረገላ ነው። ቆንሲሉ፣ ሠረገላውን የሚጠቀመው በከተማው ውስጥ ይፋዊ ጉብኝት ሲያደርግ ነው። በዚህ በመጠቀሙ በቱርኮች መካከል ከፍተኛ ባለስልጣን ያስመስለዋል። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ እርሱ ለራሱ ሆን ብሎ የወሰነው ሰዓት ሲያበቃ፣ ወደ ዶክተሩ ቤት በሠረገላው ለመሄድ ወሰነ። የብዙ ሰዎችን አትኩረት ለማስቀረት፣ ቆንሲሉ በሠረገላው ላይ ሆኖ መጡጣትና አንዳንድ ጊዜ ከሚጐበኛቸው ታዋቂ ነጋዴዎች ሱቅ አጠገብ ቆም ማለት፣ ከዚያም ጉብኝት ለማድረግ እንደወጣ በማስመሰል መድሃኒት ቀማሚውና ሽርኩ ወደሚኖሩበት አቅጣጫ መንገዱን ይዞ በመጓዝ ሌላ ምንም ፍላጐት እንደሌለው ማዘናጋት የተሻለ ነው። ቆንሲሉ፣ ስለዚህ ሃሣቡ ሙሴ ማቹን አስተያየት እንዲሰጠው ጠየቀው። ሃሣቡና እምነቱ በሙሴ ማቹ ሲረጋገጥለት ሁለቱም ተያይዘው ከጠዋቱ አራት ሰዓት ሲሆን ጉዞ ጀመሩ።

አወጣጡ ሠላማዊና የተረጋጋ እንዲመስል፣ ሠረገላ ነጂው፣ በየት በየት እያደረገ እንደሚሄድ ቆንሲሉ ትዕዛዝ ሰጠው። «ከፈረንሣውያን ማህበረሰቦች መኖሪያ አካባቢ ውጭ፣ በከተማው ዙሪያ ተጉዘህ ትመለስና በከተማው ውስጥ በሚገኘው በሙሴ ቢ ቤት ፊት ለፊት ስትደርስ ትቆማለህ»

«አይደለም እንዴ ማቼ። ለመሆኑ ልንጐበኛቸው የምንሄድባቸውን ታላላቅ ሰዎች በተመለከተ በማህደሮቻቸው ውስጥ ምን አገኘህ?»

«ምንም አላገኘሁም ማለት ይቻላል፣ ክቡር ሆይ። ሰውዬው ሰላማዊ ነዋሪ ነው። ሌላው ቀርቶ፣ ፖንሴ እውነተኛ ስሙ መሆኑንም አናውቅም። እዚህ የመጣው ከሦስት አመት በፊት ነው። ከቬነስ ለቅቆ ከመጣ በኋላ አሌክሣንደሪያ ውስጥ ለስድስት ወሮች ተቀምጧል። ብዙ ጊዜ ማርሴይ፣ ቢዩካሬና ከዚያም በፊት ኢጣሊያ ውስጥ የመድሃኒት ቅመማ ሥራ ማከናወኑን በጉራ ይናገራል። የያዘው የሙያ ማስረጃ የተጭበረበረ ነው ለማለት በቂ ምክንያት አለን። የልደት ሠርተፊኬቱ የወጣለት ከግሬኖብል ነው። ይህ ማለት ያ በጣም የተለየ ችሎታ ኖሮት፣ የሃሰት ሰነድ እያዘጋጀ ሲሰጥ ተደርሶበት ተይዞ፣ አምና የታሠረው



ያፈረሰ መነኩሴ ከነበረበት ቦታ ማለት ነው። በወቅቱ ይህን እውነታ አውቀው ጉዳዩን እንዲጠነቀቁበት ቢቀርብልዎ ምንም እንኳ ስለትውልድ ቦታው ዕለትና ሁኔታ ማወቅ ባንችልም፣ ክቡርነትዎ በቸርነትዎ፣ ሙሴ ፖንሴ፣ የፈረንሣይ ጥበቃ እንዳይቋረጥበት አዘዙ»

«ትውልዱ ምን የሚፈይደው ነገር አለ?» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ ሃሳቡን አለመውደዱን በሚገልፅ መልክ ተናገረ።

በቆንሲሉ እምነት የትውልድ ቦታ ያለው ሰው፣ በስሙ የሚጠራበት ቦታ ያለው፣ ሰዎችንና ነፍሣቸውን የሚያኖርበት ሥፍራም ያለው መኳንንት ብቻ ነው። ሌሎቹ ሰዎች ባሻቸው ሥፍራ የተወለዱ ናቸው። አሁን የተገለፀው ግን ተረት ተረት ነው ሲል አሰበ።

«ሰውዬው ከአገር አገር የሚንከራተትበትን ምክንያት ለመሆኑ በትክክል እናውቃለን። ምናልባት ይህ ፖንሴ የሚባለው እንደ ሽሪኩ ጓደኛው ፕሮቴስታንት ይሆን ይሆን?» ሲል ጠየቀ።

«ከቦታ ቦታ መዘዋወሩ በስም ማጥፋት ሰበብ ይመስለኛል። የመድሃኒት ቅመማና ሽያጭ ስራ የሚያከናወነው ምንም ዓይነት ፈቃድ ሳይኖረው ነው። ሃይማኖቱን በተመለከተ ግን የተጠመቀ የሮማ ካቶሊካዊ ክርስቲያን እንደሆነ ፍፁም ርግጠኞች ነን»

«ቢሆንም በፀሎት ቤት ጨርሶ አይቼው አላውቅም»

ይህን የጠቀሰው ከቆንስላው ግቢ ጋር ተያይዛ ያለችውንና የፈረንሣይ ማህበረሰብ በየእሁዱ የሚሰበሰብባትን አነስተኛ ቤተክርስቲያን ለመግለፅ ሲል ነው።

«መቼም ከማህበረሰባችን ሩብ ያህሉ ከርሱ የበለጡ አክባሪዎች

አይደሉም።»

«ይገባኛል፣ ግን አንድ ቀን አንድ መፍትሔ ማግኘት ይገባናል»

«ቄሱ እንደተናገሩት ሰውዬው እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ከደረሰበት ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ ከቤተክርስቲያን ሥነ - ስርዓት በኋላ ሁልጊዜም ወጥቶ ይሄድ ነበር። በግልፅ እንደሚታወቀው አበባዎችንም ወደ ቤተክርስቲያን አምጥቶ ያውቃል።»

«ለመሆኑ የንስሃ ቃል ወጥቶት ያውቃል?»

«በጭራሽ»

ቆንሲሉ፣ ትከሻውን ነቀነቀና ትዕግስት በማጣት በመስኮት ወደ ውጭ ተመለከተ።

ሙሴ ማቼ፣ ጭኑ ላይ ያስቀመጣቸውን የወየቡ ወረቀቶች ያገላብጣል። በተከፈተው መስኮት በኩል ከአረብ ከተማ የሚነፍሰው ሞቃት አየር በሠረገላው ውስጥ ሲያልፍ፣ የቡናና የደረቅ ቅመማ ቅመም መዓዛ ይዞ ይገባል። በጠባቡ ጎዳና ላይ ያለው ሕዝብ ለመተላለፍ ሲል አልፎ አልፎ ከሠረገላው ጋር ይጋፋል። ሕፃናት የቀልድ ማበሻሻጫ ቃል ይናገሩና ይሮጣሉ። ሁልጊዜም በቡድን ተሰብስበው የሚጓዙት ሴቶች፣ በሠረገላው ውስጥ ያለውን ለማወቅ በዓይነ ርግባቸው ሥር አሾልቀው ይመለከታሉ።

«በዚም የሚጠቀስ የለም» ሲል ፀሐፊው ቀጠለ። «እሱና ጓደኛው ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ነገር ለማክበር ብለው ይወጣሉ። በሁለቱ ሰዎች መካከል የከረረ ፀብ ተፈጥሮ ሰላም አደፍርሰዋል የሚል መረጃ ቀርቧል። ነገር ግን ሲጣራ ለቀልድ ብለው ሽምላዎቻቸውን ስላፏጯቸው መሆኑ ይታወቃል። ፖንሴ፣ ቱርኮች ዘንድ በብዛት ይመላለሳል። የካይሮ ዋናው ቃዲ ዘንድም ገባ ወጣ ይላል። ብዙ ነጋዴዎች ዘንድም ይመላለሣል . . »

ጉዳዩ ለቆንሲሉ እንዲህ እየተንሸራተተ የሚያስቸግረውም ለዚሁ ነው። ይህ መድሃኒት ቀማሚ፣ ከቱርክ ባለሥልጣናት ዘንድ ያገኘው ድጋፍ ከፍተኛ ነፃነት ሰጥቶታል። በማይረባ ግጭት ሰዎችን ማስቆጣት የአገሬውን ሕዝብ የጥላቻ ስሜት ሊቀሰቅሱና የዲፕሎማሲያዊ አተካሮ ሊፈጥሩ የሚችሉ አደጋዎች እንደሚሆኑ ቆንሲሉ ከተሞክሮው ያውቃል። ፖንሴም ይህንን ያለጥርጥር ያውቃል። በዚህ ሣቢያ ሰውዬው መርዛም ባህርይውን በከፍተኛ ብልግና ቆንሲሉ ላይ ሲያሣይ ሣይሞክር አይቀርም።



ምንም እንኳ በአዘቦቱ ጊዜ በውጭ አገር ማህበረሰቦች ላይ ሰፋ ያለ መረጃ ስለመያዝ ክዛደት ባይሰጥም «ማሀደር ሲበዛ ባዶ ነው፣ ለዚህ ደግሞ የምሥራች አትባልበትም» አለ ቆንሲሉ በአብሬት።

ሰረገላው የሚዞርበትን መስመር አጠናቅቆ በአንድ የግል ቤት ፊት ለፊት ሲደርስ ቆመ። ሁብታሙ ባለቤት፣ በአድናቆትና በደስታ እንግዳውን ለመቀበል ሽርጉድ እያለ ወጣ። እንዲህ ያለው ሁኔታ ጥንቃቄውን ሲጉዳበት ስለሚችል ጭንቅላታሙን ነጋዴ ሲመለከት ዲፕሎማቱም የደስታውን አፀፋ ሲመልስ አለመቻሉን ጠቅሶ መንገዱን እንደሚያቋርጥ ነገረው። ከዚህ በኋላ የሙሴ ማቼን ክንድ ይዞ፣ ጉዳናውን በመጀነንና በክብር አቋረጠ።

ፖንሴና ሜትር ዠረሚ ተዳብለውበት የሚኖሩበት ቤት ከፊት ለፊት ከሚታየው ይልቅ የባሰ ደካማ ነው። እርስ በርሣቸው እንዲያያዙ ከተደረጉት ባለሁለት ፎቅ ሕንፃዎች በስተቀር ሌላ የለውም። ሙሉ በሙሉ የጣውላ እንጨት ባይለበጥበት ኖሮ፣ ወደ መንገዱ ሲል ያለው የሕንፃው ግድግዳ አጥር ይሆን ነበር። በጉዳናው የውሃ ልክ እኩል በተሠራው ባለጉበን የስገነት መወጣጫ ስር አድርጎ አንድ ሰው በጥላ ውስጥ ሊጓዝ ይችላል። ከበላይ ያለው ፎቅ ከበስተኋላ የሚገኙትን ክፍሎች ቀዝቃዛ እንዲያደርጋቸው ሲባል እንደ ፀሐይ መከላከያ ያገለግላል። የሁለቱ መድሃኒት ቀማሚዎች መኖሪያ፣ በዙሪያቸው ካሉት አጠቃላይ ወጥ ሕንፃዎች አንድ አካል እንጂ ተለይቶ የሚገኝ አይደለም። በውጫዊው መልኩ ከሌሎች ጋር አንድ ነው። ይህ ጥቂት ጉረቤታሞች ያሉበት ሕንፃ ከማህበረሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ኑሮ ያላቸው፣ አዲስ እንግዳ ደራሾች፣ የከሰሩ ሰዎች፣ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች፣ የታወቀ ሥልጣን የሌላቸው የቅይጥ ዘር ልጆች፣ አንዳንድ ጊዜ ቆንሲሉ ባለው ርህራሄ በማህበረሰቡ ውስጥ ታግሷቸው የሚኖሩ አባላት ተፋፍገውና ንፅህናው ባልተጠበቀ ቅርርብ የሚኖሩበት ነው።

ወደ መድሃኒት ቀማሚው ቤት የሚያስገባው በር ወለል ብሎ እንደተከፈተ ነው። በመንገዱ ላይ መቆም ጥርጣሬን እንዳያስከትል በማሰብ፣ ዲፕሎማቱ፣ ይግቡ የሚል ግብዣ ወይም ፈቃድ ሳይጠብቅ ዘው አለ። ሜትር ዠረሚ ሲያስተናግዳቸው ሲል ፈጠን ብሎ ወደ ቤቱ በሚያደርሰው ጠባብ መተላለፊያ ላይ ቀደማቸው። ክፍሉ፣ የምድር ቤቱን ወለል ሙሉ በሙሉ የሚይዝ፣ ሰፊና ጨለማ የዋጠው ነው። የሥፍራውን ምስቅልቅልነት ለመግለፅ የሚያስቸግር ነው። ለዕይታ ስሜት የሚሰጥ እንዳይሆን፣ ሲበዛ የተለያዩ ነገሮች የተከማቹበት

ነው። በመጀመሪያ ዕይታ፣ በቢጫ ነፀብራቁ ጭላንጭል እየፈጠረ ዐይንን የሚስበው የነሃስ መቀጫ ይስተዋላል። አንገተ ረዣዥም የሸክላ እንስራዎች በጋስ የከሰል ምድጃ ላይ ተጥደው፣ እንደምስሶ የተገተረ ጭስ ከውስጣቸው ወደውጭ ይተፋሉ። ጭሱ ግን፣ በአንዳች ምስጢራዊና ከባድ ነገር ጫና እንደተደረገበት ያህል ተመልሶ አግድም በግድግዳዎች መሃል ይሰምጣል። በአንድ ጥግ በኩል፣ በአንድ የገለባ ፍራሽ ላይ ያለቀ አንሶላ ተነጥፏል። ኮርኒሱ ዝቅ ያለ ሲሆን በጥቀርሻ ብዛት ጠቁሯል። በዚያ ላይ መቶ ወይም ሁለት መቶ የሚሆኑ የቀርቀሃ ቅርጫቶች በውስጣቸው የደረቁ ዕፅዋትን፣ የጠወላለጉ ፍራፍሬዎችን፣ በአይጦች የተተፈተፉ የዳቦ ቅራፊዎችን ይዘው ተንጠልጥለዋል።

በረኸኛመና ሰፊው ቁመናው የኮርኒሱን አውታር እየበረሸ «ወደ ቤተሙከራችን እንኳን ደህና መጡ ስል ታላቅ ክብር ይሰማኛል፣ ክቡር ሆይ»

«ሸሪክህስ እውስጥ አለ እንዴ?»

«ፎቅ ላይ ነው»

በደብዛዛው ክፍል ውስጥ ቀጭን ብርሃን ከፎቁ ወደ ምድር ቤቱ ይወርዳል። በዚያ ክፍተት በኩል የሚያስወጣ የጣውላ ደረጃ አለ። ቆንሲሉና ሙሴ ማቼ እየተንተቱ ደረጃውን ወጡ።

ከላይ ያለው ክፍል እንደታችኛው የጨለመ ሣይሆን ብርሃን የሞላበት ነው። ዙሪያውን ባሉት አራት መስኮቶች የሚገባው ብርሃን ክፍሉን ወለል አድርጎታል። መስኮቶቹ ወደ ጉዳናው ሲል ወደ ሚገኘው በረንዳና በጐን ወደ ሚገኘው ሰገነት ይከፈታሉ። የዚህ ክፍል ኮርኒስ አንድም ተነስቷል ወይም ጨርሶም አልነበረውም። በዚህም የተነሣ የጣሪያው ወራጅና ግራጫ የሆነው የጣሪያው ክዳን ጡብ፣ ወለል ብለው ይታያሉ።

ቦታው ሙሉ በሙሉ በቅጠሎች የተሞላ ነው። ሙሉ እድገታቸው ላይ የሚገኙና ከነሥራቸው በትልቅ የእንጨት ገንዳ ውስጥ ተተክለው ብርሃንና የርጥበት ሙቀት ለማግኘት ሽቅብ አድገው የተመዘዙ ዛፎች ይታያሉ። አንድ እጅግ ግዙፍ የቁልቋል ዛፍ በፎቁ ጣሪያ ላይ ከተተከሉት ዕፅዋት ጋር በቁመት ተስተካክሏል። በድምቀት የሚያብረቀርቁ፣ ግንዶቸው በፀጉር የተሸፈነ የሚመስሉ ሌሎቹ በእሾህ የተከበቡና ቅርንጫፎቻቸው የተንዘረፈፉባቸው ትላልቅ



ተክሎች አሉ። በግዙፎቹ ተክሎች መካከል በሚገኙት ባዶ ቦታዎች ላይ ብዛት ያላቸው የተለያዩ ትናንሽ ዕፅዋት አሉ። የዚህ ክፍል ወለል ወደ አትክልቱ ስፍራ በሚወስደው በረንዳና ሌላው ጉዳናውን ሲያሳይ ወደሚችለው ሰገነት የሚወስዱ ቀጫጭን መተላለፊያዎች በስተቀር ሙሉ በሙሉ በትናንሽ ማሰሮዎች የተሞላ ነው። መፃህፍት የተከመሩበት አንድ ጠረጴዛና ጨለም ከሚለው ጥግ በኩል አንድ አነስተኛ ቁም ሣጥንም አለ። በመካከለኛ ቁመት ከፍታ፣ በግድግዳው ላይ ካሉ የነሃስ ወይም የቆርቆሮ ማንጠልጠያዎች ላይ የተሰቀሉ ወይም ከጣሪያው ርብራብ ላይ በተቋጠሩ ሲባጎዎች ታስረው የተንጠለጠሉ በደርዘኖች የሚቆጠሩ ግንዶቻቸውና ቅጠሎቻቸው ወፍራም ሆነው በተፈጥሯቸው ብዙ ውሃ የሚይዙ ተክሎች፣ የእንጨት ወይም የድንጋይ ሽበት የሚታዩባቸው፣ ውብ መዓዛ ያላቸው ትላልቅ አበቦችና ሌሎችም ፋፍተውና ዳብረው ይታያሉ።

ቆንሲሉና ፀሐፊው ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ተዋጡ። እንዲህ ፍፁም ልዩ በሆነ የአረንጓዴ ዕፅዋት ማሣደጊያና ማራቢያ ቤት ውስጥ፣ ማንም ሰው የትናንሽ ወፎችን ክንፎች መርገብገብና ጫጫታቸውንም መስማት ይችላል። ሜትር ዠረሚ ወደ ፎቁ አልወጣም። ሁለቱም ጉብኚዎች በዚህ ምድራዊ ገነት በሆነ ቦታ ሌላ የሰው ፍጡር ይኖራል ብለው አላሰቡም።

«ግቡ፣ ግቡ ጌቶቼ» ሲል ከላይኛው የክፍሉ አካል ከአንድ ቦታ የተላከ ድምፅ ጋበዛቸው።

ዲፕሎማቶቹ እንደ ሁለቱ ወደፊት ራመድ አሉ። የወለሉ ንጣፍ ጣውላ ባልተቋረጠ ሁኔታ ውሃ ስለሚፈስበት ሲረግጡት ይንሳጠጣል። በክፍሉ በስተጀርባ በሰው ቁመት ልክ በማይሆን ከፍታ ላይ፣ ከመረብ የተሰራ ባዶ ተወዛዋዥ አልጋ ይታያል።

«ይህን አስቸጋሪ የማዳቀል ሥራ እንደጨረስኩ እመጣለሁ። እስከዚያው ድረስ እባካችሁ ተቀመጡ። ጠረጴዛው አጠገብ ሁለት በርጯማዎች አሉላችሁ።» አለ ድምፁ።

ዐይኖቹ አጥርተው የማያዩለት ሙሴ ማቼ፣ በረኸኛሙ ዛፍ ላይ የተደገፈውን መሰላል ቆንሲሉ እንዲመለከት አቅጣጫውን በእንቅስቃሴ መራው። በመሰላሉ የመጨረሻው የመርገጫ ማገር ላይ የሚተጣጠፍ የቆዳ ቦት ጫማ የተጫሙ ሁለት እግሮች ይታያሉ።

«ደህና፣ ደህና፣ ሥራህን ስትጨርስ ትደርሳለህ» አለ ቆንሲሉ ንጹቱን በትንሹ በሚገልፅ ቃና ሙክ ብሎ።

ቆንሲሉ፣ በእንቅስቃሴ ሙሴ ማቼን አመለከተው። ሁለቱም ድምፁ ወዳዘዛቸው ቦታ ለመድረስ በየማሰሮው ላይ እየተራመዱ፣ የማይስተዋሉ የቆንጥር እሾሆች የእግር ሹራቦቻቸውን እየያዙባቸው በዝግታ ወደ ጠረጴዛው አምርተው ተቀመጡ።

«እነዚህ ቁርጥራጮች ሊፀድቁበት የሚችሉበት ወቅት ከእንግዲህ አጭር ነው። የኛ ሙያ ተስፋ የሚያደርገው በማዳቀል ሥራ ላይ ነው። በተፈጥሮ የምናገኘው ዕፅ ጥሬ ሃብታችን ነው። ወይኔ! ወይኔ! ወይኔ፣ ይህች ትንሽ ሽቦ ድጋሚ ተሰብራ ወደቀች። እባካችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ» ሲል ከመሰላሉ በላይ ያለው ድምፅ ተናገረ።

ቆንሲሉ፣ ቁጣውን ሊደብቅ የሚችልበት ትዕግስት ከዚህ በኋላ አይኖርም ከሚል ፍርሃት «ይገባናል» ሲል ሙሴ ማቼ መሰሰለት

«እንዳልኩት የተፈጥሮው ተክል ጥሬ ሃብት ነው። ይህን በማዳቀል አንዱ ሌላውን እንዲደግፍ ማድረግ ያስፈልገናል። ለኛ የነገሮች መነሻ ምንጊዜም ተፈጥሮ ነች። ቅመሞቹ ሁሉ በእጃችን ውስጥ ናቸው። የምንመረምረው እነዚህን ቅመሞች እንዴት እናስተባብራቸዋለን የሚለው ነው»

በጠረጴዛው ላይ መጠናቸው የተለያዩ ወረቀቶች ተቆልለዋል። ቆንሲሉ፣ በድንጋጤ ያገላብጣቸው ጀመር። በአዝዕርትና ዕፅዋት ጣይንስ ላይ የተፃፉ የሆራስ ግጥሞችና ትልልቅ መጠን ባላቸው ብዙ ወረቀቶች ላይ በአረቢኛ የተፃፉ ቅፆች ናቸው።

ለሻበላ ግጥሚያ የሚያስፈልጉ ሁለት ሻምላዎች በመጠቅለያ ተደርገው በአንድ ወፍራምና ጠንካራ ግንድ ላይ ተንጠልጥለዋል። ወለሉ ላይ የእጅ ጓንቶች፣ የደረት መከላከያዎችና የፊት ጭምብሎች ወድቀዋል።

«የሥራችንን ሁኔታ በተመለከተ ውይይታችንን ለመጀመር እንድንችል እንኳን ደህና መጣችሁ እላለሁ። ጆን ባፕቲስት ፖንሴ እባላለሁ። አንድ ነገር ልትነግሩኝ እንደመጣችሁ አስባለሁ።»



«ጌታው» አለ ቆንሲሉ ከመቀመጫው ላይ እየተነሣ።

«የመጣሁበት ጉዳይ እጅግ በጣም አስቸኳይ እንደሆነ ርግጠኛ ልትሆን ይገባሃል። ይህ ባይሆን ኖሮ ወደዚህ ልገብኝህ አልመጣም ነበር። ምኞቴ ሁሉ በእውነት አንተን ለማግኘት ነበር። እርስ በርሣችን ልንደማመጥና ልንግባባ እስከቻልን ድረስ ሁሉም መልካም ነው»

«እውነት ነው» አለ ጆን ባፕቲስት ቢጋለና ከልብ በመነጨ ድምፅ። «የጀመርኩትን ሥራ ከፍፃሜ እንዳደርስ ስለፈቀዳችሁልኝ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ያ ባይሆን ኖሮ የደከምኩበት ሁሉ መና ይቀር ነበር»

«ሙሴ ፖንሴ» አለ ቆንሲሉ በድንገት ተነስቶ ቆሞ፣ ጣሪያ ጣሪያውን እያየ። «ለመሆኑ የመድሃኒት ቅመማ ሥራ ማከናወንህ እውነት ነው?»

«አዎ፣ ይህ ዓይነቱ ጊዜ እንደሚመጣ ሁልግዜም እጠብቅ ነበር፣ ክቡር ሆይ። ከዚህ በኋላ እውነቱን ልንደብቅዎ አንችልም። ስለዚህ ጉዳይ ቀደም ብለን ባለመናገራችን የቅሬታ መነሻ እንደሚሆን ይሰማኛል። በርግጥ ለሁሉም መልካም የሆነን ጉዳይና ሥራ በመደበቅ ደስታ እንደሌለም አውቃለሁ። እርስዎ ይህን ሥራ እንደሚጠሉትም አውቃለሁ። አሁኑኑ እዚሁ እያሉ ናሙናዎችን አሣይዎታለሁ።

«ስማ ፖንሴ፣ ጥያቄዬ ቀላልና ቀጥተኛ ነው። የሥራ ፈቃድ የመከልከል ሃሣብ በውስጤ የለም። እንዲያውም የተገላቢጦሹ ነው። በድጋሚ እጠይቅሃለሁ። አንተም በቀላሉ እንድትመልስልኝ እፈልጋለሁ። የመድሃኒት ቅመማ ሥራ ታከናውናለህ?»

«አዎን?»

«ለምሣሌ በአገሬው ሰዎች ላይ የሚታየውን ቁምጥና መሰል የቆዳ በሽታ ፈንገስ ማከም ትችላለህ?»

«እንዲህ በቀላሉ የምመልሰው ጥያቄ አይደለም። ይህ ማለት መፍትሔ የለውም ማለቴ ግን አይደለም። በሕክምና ላይ እያንዳንዱ ሕመም በየግሉ ነው የሚታየው»

«በዚህ ነጥብ ላይ ይህ በቂ ነው» ሲል ቆንሲሉ አቋረጠውና «ሌላ ጥያቄ ላቅርብልህ? እዚህ የመጣሁት ታላቅ ክብደት ያለውን አንድ የዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ እንድትቀበል በክብር ልጠይቅህ ነው»

«ዠረሚ! ይህ ሽቦ፣ ይህ ሽቦ!» በመስሳሉ ላይ ያለው ሰው ጮኸ

«ሰምተኸኛል?» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀው

«አዎን፣ አዎን፣ ይቀጥሉ»

«የፈረንሣይ ንጉሡ ነገስትን መልዕክት ተቀብለህ ለማድረስ ትፈቅዳለህ?»

«ምን አይነት?» ሲል ፖንሴ ጭንቅላቱን ወደ ፎቁ ብቅ እያደረገ በከፍተኛ ድምፅ ጠየቀ።

«ይህ የመዳብ ሽቦ፣ እባክህ አዲስ ጥቅል ልታመጣልኝ ትችላለህ? ጓደኛዬ፣ ይህ እዚህ ያለው ይበጣጠሳል»

«ሙሴ ፖንሴ፣ የማነጋግርህ እጅግ በጣም ታላቅ በሆነ ጉዳይ ላይ ነው። ከዚያ ዛፍ ላይ ወርደህ ሁለት ደቂቃ ያህል እንኳ ልትሰጠኝ አትችልም እንዴ?» ሲል ቆንሲሉ በሰከነ እርጋታ ጠየቀው።

«ጨርሻለሁ፤ ሁለት ወይም ሦስት ቋጠሮዎች ቢቀሩኝ ነው። እንዳለ ከተውኩት ሁሉም ነገር ይወድማል። አይዞዎ አይስጉ። የተናገሩትን ሁሉ ሰምቻለሁ። ለንጉሡ ነገስቱ የዲፕሎማቲክ መልዕክት . . . »

«የክርስትና እምነት ታላቅ መሣሪያ ሊያደርግህ የሚችል ፣የብፁዕ ሊቀ ጳጳሱ አኩሪ መሣሪያ ሊያደርግህ የሚችል ተልዕኮ ነዋ»

«ነገርኩዎት ክቡር ሆይ። ጥያቄዎን ሊያረካና እርስዎን ሊያስደስት የሚችል ማንኛ ውንም ነገር እሰራለሁ። ነገር ግን ለነዚህ ይፋ ለሆኑ ጉዳዮች እምብዛም ደስታ የለኝም» ሲል እንዳችም የጉጉት ስሜት በሌለበት ድምፅ ፖንሴ ተናገረ።



«ይህን ጉዳይ በሌላ መልክ ላቅርብልህ። ጥያቄው ለአንድ የነፃ አገር መሪ ሕክምና የመስጠት ጉዳይ ቢሆንስ?»

«ለንጉሰ ነገስት ሉዊስ 14ኛ?»

«አይደለም። ነገር ግን የፈረንሣይ ንጉሡ ነገስት ሲልኩህ ወደሚፈልጉት ነፃ የአገር መሪ ነው። ይገባሃል? የአንድ ታላቅ ንጉሥን ሰውነት በማከም መደነቅና ክብር አለ። አይመስልህም?» ሲል ቆንሲሉ፣ በዚህ የሕይወት ተሞክሮው አነስተኛ በሆነ ገራገር ሰው ሁኔታ ትዕግስት በማጣት ተናገረ።

«እዩ ጌቶች! እኛ ሐኪሞች የሰውን አካል ስንመለከት እንዳችም ንጉሡ ነገስትነት የሚባል ነገር የለም።»

ሙሴ ማቼ ቀና ብሎ ቆንሲሉን ሲመለከተው፣በርሱ ውስጥ የተፈጠረውን ዓይነት ተስፋ አስቆራጭ አዝማሚያ አነበበት። ይህ ስሜት ደግሞ በማንኛውም ጊዜ የእፍ እላፊ ዘለፋና ስድብ ሊያስከትል ወይም ወደ ልቅሶ ሊለውጥ ይችላል።

«እንግዲህ፣ ክቡር ቆንሲል፣ እዚህ ድረስ የመጡት እኔን ፈልገው ስለሆነ ሃሣቤን እሰውጣለሁ። ሕክምና የሚሻው ንጉሥ ቢሆንም ባይሆንም እርስዎ እኔ እንዳክመው የሚፈልጉት ሰው እስከሆነ ድረስ ስርስዎ ስል አደርገዋለሁ። ተስፋ የማደርገው ግን ቦታው ከዚህ እጅግ እንደማይርቅ ነው። ምክንያቱም አሁን የያዝኩት እጅግ ብዙ ሥራ ስላለኝ፣ ለረዥም ጊዜ ልቆይ አልችልም»

«እንዲህ ከሆነ እስከአሁን ስንነጋገር የነበረው ሁሉ እርባና የሌለው ነው ማለት ነው።» በማለት ተናግሮ ቆንሲሉ ወንበሩ ላይ ተመልሶ ዘጭ አለ።

«ይቀጥሉ፣ እስቲ ልወቀው»

«እንደእውነቱ ከሆነ ይህ ሥራ ለአጭር ጊዜ የሚደረግ የቤት ውስጥ ደርሶ መልስ ጉብኝት አይደለም። እንደምገምተው የሕመምተኛውን አልጋ ለመድረስ በትንሹ ከስድስት በላይ ይወስድብሃል ብዬ እገምታለሁ።»

«ስድስት ወሮች፣ እንዴት ሊሆን ይችላል ይላሉ?»

«የአበሻውን ንጉሥ በራሱ ቤተመንግስት ውስጥ ለማከም ነው?» አለ ቆንሲሉ:: በዛፉ ቅርንጫፎች ውስጥ ረዥም ፀጥታ ሆነ:: ከዚህ በኋላ መሰላሉ ሲንቀጠቀጥና ሁለት እግሮች በመወጣጫው ላይ ቁልቁል ሲወርዱ ጉብኝዎቹ ተመለከቱ::

ጆን ባፕቲስት ፈጥኖ ወለሉ ላይ ደረሰ:: በሸሚዙና በፀጉሩ ላይ የተጣበቁትን ትንንሽ ቅጠሎች አራግፎ ወደ ዲፕሎማቶቹ በዝግታ አመራ::

ምናልባት በሕዝብ አዕምሮ ውስጥ፣ አንድ ሐኪም እንደ አንድ ብልህ ሊቅ ሰው፣ ሽምግል ያለ ይመስላል ከሚለው ጠንካራ አስተሣሰብ በመነሣት ሲያስበው እንደነበረው ሣይሆን፣ ሙሴ ዴ ማይሉ ከገመተው ይልቅ ፖንሴ በጣም ወጣት ሆኖ አገኘው::

ከዚህም ባሻገር፣ ቆንሲሉ አሁን ከፊት ለፊቱ ስለሚመለከተው ሰው አካላዊ ቁመና ብዙም አላስተዋለም:: ቆንሲሉ አስቀድሞ ያስተዋለው ስላላስደሰተው ባህርይው ነበር:: በፀሎት ሥነ-ሥርዐት ላይ ያለውን ትህትና፣ ገና የመጀመሪያውን እንቅስቃሴ ሲመለከት፣ ተገድዶ ለማስመሰል የሚያደርገው ዓይነት ነገር የለበትም:: እንኳንስ ሊቅለሰለስ የአክብሮት ምልክት አይታይበትም:: ግልፅና ተፈጥሮአዊ ቢሆንም ስሜቱን ስለሚነኩ ጉዳዮች አንዳችም የሚታወቅ ነገር የለም:: ሁለቱ ጉብኚዎች እመዳቸው ቡን አሉ:: ቀጥሎም ሳብ አዘፈቃቸው:: የባለሥልጣንነት አቋማቸውን ለማረጋገጥ ጨነቃቸው:: የውይይታቸው ተካፋይ የሆነው ሰው ለማንኛውም ሰው እንደሚሆነው ሁሉ ጠንካራ የማወቅ ፍላጐት ያለው፣ ግልፅና የርህራሄ ስሜት ያለው ቢሆንም ለእነርሱ ግን የብልግና ቁንጮ መሪ መሰላቸው:: እንዲህ ካለ እንግዳ ባህርይ ጋር የተፋጠጠው ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ከመቼውም በበለጠ ራሱን ተቆጣጥሮ ፀጥ አለ:: ሙሴ ማቼ፣ ሰውነቱን ሁሉ ወዲያውኑ ጥላቻ ሲወርረው ተሰማው::

ቆንሲሉና ፀሐፊው ነፃነትን ወዳያውኑ ጠሏት:: ምክንያቱም በአንደኛቸው አስተሣሰብ ነፃነት እጅ እንድትሰጥ የምትደረግ አይደለችም:: በሌላኛው አስተሣሰብ ደግሞ ነፃነቱን እሹሩሩ ሳይሉት በመኖሩ ተፀዕኗል:: ሁለቱም በየምክንያቶቻቸው ነፃነትን ጠሏት:: ይሁንና ሁለቱም እዚሁ ፊት ለፊታቸው በመንለፅዋ የግዳቸውን አወቋት:: ከአጭታ ፀጥታ በኋላ፣ ጆን ባፕቲስት የመጨረሻውን እርምጃ ወደፊት ተራምዶ አጠገባቸው ከደረሰ በኋላ ፈገግታ በተሞላበት

«የአበሻው ንጉሥ! ይህ ከሆነ ጌቶቼ:: ይህ በቁም ነገር የምንነጋገርበት ጉዳይ ነው» አላቸው::



# 7

ማዳም ዴ ማይሌ፣ በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ቆማ ባለቤቷን ትጠብቀዋለች:: ትንፋሽን በሚያጠፋው ሙቀት ውስጥ በቻይናውያን ዕጌረዳዎች የተጊያጊያጠውን የወረቀት ማራገቢያ በጭንቀት ታወዛውዘዋለች:: ሰረገላው በአምስት ሰዓት ላይ ተመለሰ:: ቆንሲሉ ከረዳቱ ጋር ወረዱ:: ማዳም ዴ ማይሌ ወደ ባሏ ሮጠች::

«ውዶ ሆይ! እባክህ ጥቂት ዕረፍት እንድታደርግ እለምንሃለሁ:: ዕረፍት እኮ አጣህ:: የአየር ጠባዩም በጣም አደገኛ ነው:: ልብህም . . . »

«ስለኔ ስጋት አይደርብሽ:: ይልቅስ በከባድ ችግር ውስጥ ስላለው ስለመንግሥት ጉዳይ ተጨነቂ:: አሁን ግን አባ ቬርሣውን በዚህ ሰዓት የት ላገኛቸው እንደምችል ንገሪኝ» አላት ቆንሲሉ

«ዛሬ ጧት ሲጉበኟቸው ከመጡ ሁለት የጀስዊት ቀሣውስት ጋር ከአንድ ሰዓት በላይ ለሚሆን ጊዜ ክፍላቸው ውስጥ ዘግተው ነው ያሉት»

ቆንሲሉ፣ ለሙሴ ማቼ፣ እንዲንቀሳቀስ ምልክት በመስጠት ወደሁለተኛው ፎቅ ጉዞ ጀመረ::

ለጀስዊቱ ቄስ የተወሰነላቸው በጣም ሰፊ ክፍል በጓሮ በኩል ዝቅ ያለ ጣሪያ ወዳለው የጽሕፈት ቤት ያመራል:: ቀሣውስቱ በዚህ ክፍል ውስጥ ከጧቱ ጀምረው ቆይተዋል:: ሙሴ ዶ ማይሌ፣ ሲያንኳኳና እንዲገባ ሲፈቀድለት ዘው አለ:: ሙሴ ማቼም ተከትሎት ገባ:: ጥቁር ካባ ለብሰው በጠረጴዛው አጠገብ ከተቀመጡት ሦስት ካህናት ዘንድ ተቀመጡ::

«ከምታውቋቸው ከአባ ጋቦሬ እና እስከአሁን አይናችሁን እንዳላሳረፋችሁባቸው ተሰፋ ከማደርግባቸው ከአባ ዴ ብሬቬዳንት ጋር እንዳስተዋውቃችሁ ፍቀዱልኝ» አሉ አባ ቬርሣው

ዲፕሎማቶቹ ለሁለቱ ካህናት ሠላምታ አቀረቡ:: አባ ጋቦሬ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ቢያንስ ለአሥራ አምስት ዓመታት ኖረዋል:: አራት ማዕዘን ቅርፅ ያላቸው፣ ወፍራም፣

የእጆቻቸው ቅላት ከፊታቸው ጋር የሚመሣሰል ናቸው:: የፈረንሣውያን ማህበረሰብ ልጆችን ያስተምራሉ:: በሁሉም አቅጣጫ በቅሎ ምስቅልቅል ያለው ወጣ ገብ የላይኛው ጥርሣቸው፣ ከታችኛው ጥርሣቸው ጋር ሣያስቸግራቸው በእኩልነት ነጥሞ እንዴት እንደሚዘጋላቸው ብዙ የሕፃናት ትውልድ ለመረዳት ሙከራ ያደርጋል:: ይሁን እንጂ እኚህ መልካም አባት ንግግራቸውን ሲያቆሙ ተአምረኛው ጥርሣቸው ተመልሶ ያው ነው:: የአውሬ የሚመስለው አስፈሪው አፋቸውም እንዲሁ በርጋታ ይከደናል:: የዚህ የመንጋጋቸው መንሻፈፍ ዋናው ሰበብ፣ በሌላው ሁሉ ረገድ እንከን የለሽ ቢሆኑም ለፈሣሽ ነገሮች የተለየ ዝንባሌ ያላቸው መሆናቸው ነው:: ቀደም ሲል እንደገለፅነው ቆንሲሉ በወይን ጠጅ ንግድ ላይ የሞኖፖል አቅም ቢኖረውም፣ የአልኮል መጠጦችን ለካህናት በዋጋው በማቅረብ በኩል ቸር ነው:: በደረሱት ካባና በጫኑት ቆብ መሠረት ፍጆታቸውን በተወሰነ ገደብ ውስጥ ካደረጉ፣ ቆንሲሉ የለመደውን ትርፍ ቀንስ ያደርግላቸዋል:: ይህን ዓይነት ሥርዓት የሚጥሱት አባ ጋበሪ ብቻ ነበሩ:: ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ቄሱን ቅድስና የሌላቸው ሰካራም ናቸው ሲላቸው፣ ቄሱም፣ እርሱን ተራ ሌባ ነው ማስታቸው አልቀረም::

ሌላኛው የጄስዊት ቄስ በሁለመናቸው ተቃራኒ ናቸው:: ቁመተ ረዥም ሆነው እግረ ሰባራ ናቸው:: ቀጭን ናቸው ባይባልም አጠቃላይ አኳኋናቸው ለስላሣና ደካማ ነው:: በሽምብራ አፍንጫቸው ላይ የመዳብ ፍሬም ያለው የአይን መነጽር ሰክተዋል:: መንማናው የፊታቸው ክፍል በአጭሩ ከተቆረጠው ፀጉራቸው አፈንግጠው የሚታዩትን ግንባራቸውን፣ አፉቸውንና አገጫቸውን ያጐሏቸዋል:: እነዚህ ወደውጭ በጣም አፈንግጠው የወጡት የፊታቸው ክፍሎች ደግሞ ከአጥንት ይልቅ የሥጋ ክምሮች ይመስላሉ:: ወፍራሙ ከንፈራቸው በቀላሉ አይከደንም:: የአንገታቸው ቆዳ ወደ አገጫቸው መንጠልጠል ጀምሯል:: እኒህ ጉባጣ ሽማግሌ የግንባራቸው ወጣ ወጣ ማለት፣ መነፅር ማድረጋቸው፣ አጥንትና ቆዳ የሆኑት እጆቻቸው፣ የወየቡ የወረቀት ገፆችን የማገላበጥ ልማዳቸው ተዳምረው ድንገት ሲታዩ ምሁር ያስመስሏቸዋል::

«በጣም ትክክል ነዎት፣ አባ ዴ ብሬቤደንትን አላውቃቸውም» አለ ቆንሲሉ እጅ እየነሣ



«ከመጡ ገና ሁለት ወራቸው ነው:: እንደምታውቀው ቱርኮች በጣም ያስቸግሩናል:: በአፊሴል እዚህ ቋሚ ኗሪ ሲኖረን የሚችለው አንድ አባላችን ብቻ ነው:: ሌሎች ተራ ጐብኚ ዎች ናቸው:: ስለዚህ ባለሥልጣናቱን በተመለከተ አባ ዴ ብሬቬደንት ተራ ጐብኚ ናቸው»

አባ ዴ ብሬቬዴንት በፍርሃት ፈገግ አሉና ጭንቅላታቸውን ሙሉ በሙሉ ሣያዞሩ ቆንሲሉን በዐይናቸው ቂጥ አዩት::

«እና ሆኖም ግን፣ ሊሆን የሚችል መልዕክተኛ አገኘህ?» አሉ አባ ቬርሣው

«አዎን አባቴ፣ ቀላል ባይሆንም አንድ አግኝቻለሁ:: ሰውዬው በወስጡ ጠንካራ የተፈጥሮ የጀብድ ስሜት ያለበት፣ የህክምና ባለሞያና የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ፈረንሣዊ ነው»

«ይህ በርግጥ እግዚአብሔር ፀሎታችንን ሰምቶ የሰጠን መልስ ነው» በማለት የጄስዊቱ ቄስ ንግግራቸውን እንዲያፀድቁላቸው ዙሪያቸውን ቃኙ «ሙሉ በሙሉ ተቀበለ?»

«እንዴት ልበል . . . ከምሣ በኋላ እዚህ ይደርሣል:: ውሣኔው ገና አልተቋጨም:: እንደሚመስለኝ ግፊት ባናደርግበት ጥሩ ነው:: የተልዕኮውን ዝርዝር እርስዎ በቀጥታ እንዲገልፁለት ዕድሉ ይኖርዎታል:: እርስዎ ይፍቀዱት እንጂ ቃል ኪዳኑን ሊያጠናክርለት በሚችለው በስልጠናው ላይ ሁላችንም እንገኛለን»

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ወዲያውኑ ስለተባለው ሰው ዝርዝር መግለጫ ሰጠ:: የሰውዬውን ባህርይ እያደነቀና ግራ የሚያጋባም መሆኑን እያስረዳ፣ የአረማመዱን ጥበብ ለማሣየት ጥንቃቄ የተሞላበት እርምጃ አከናወነ:: ስለዕጋው በግልፅ የሚገመት የዕድሜ መጠን ለአባ ቬርሣው መግለፅ አስተዋይነት እንዳልሆነም ገመተ::

«ሲያዩት ወጣት ነው:: ነገር ግን በእጃችን የሚገኝ የፖሊስ መረጃ፣ ሰውዬው ሲያዩት እንደሚመስለው ሣይሆን ጠና ያለ ነው::»

ቆንሲሉ እየሣቀ «ምናልባት በተክሎች ላይ ክልቡ የሚያከናውነው ሙከራ በትክክል መሥራቱን ለማረጋገጥ በራሱ ላይ ስለሚፈትሽ የዚያ ውጤት ይሆናል»

«ወባት መድሃኒት ቀማሽ?» ሲሉ አባ ቬርሣው ጠየቁ። አባ ቬርሣው ዕድሜአቸውን ሙሉ መጠኑ የተወሰነ የእትክልት ጭማቂ እንደመድሃኒት ይወስዱ ነበርና ትንሽ ተሣክቶላቸዋል።

«እንደዚያ ማይሆን አይቀርም ብዬ አስባለሁ። አለበለዚያ ያልተለመደውን ዓይነት የተክሎች አጠባበቁን ሁኔታ ለመግለፅ አዳጋች ነው»

ማዳም ዴ ማይሌ፣ የምሣ ገበታ መዘጋጀቱን ለመግለፅ አንድ ተላላኪ እስከ ላከችበት ጊዜ ድረስ ሁሉንም ዓይነት በሽታ ማዳን ይችላል ስለሚባል መድሃኒት፣ ቀማውስቱና ሙሴ ዴ ማይሌ ስጥቂት ጊዜ ሲወያዩ ቆዩ። ከዚህ በኋላ ሁሉም ወደምድር ቤት ወረዱ።

ማዳም ዴ ማይሌ፣ በምሣ ገበታው ላይ ተካፋይ ሆነች። በንጉሠ-ነገስት ሉዊስ 14ኛ ትዕዛዝ ወደ ኢትዮጵያ የሚደረገውን ተልዕኮ ለማደፋፈርና መልዕክተኛው እንዲቀበለው ለማደረግ፣ አባ ቬርሣው ማንኛውንም ዝርዝር መግለጫ እጅግ በማጣፈጥ በውይይቱ ላይ አቀረቡ። ቆንሲሉ፣ የተልዕኮው አጠቃላይ ምስጢር መገለፁ ግብዝነት እንደሆነና ምናልባትም ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ተሰማው። ይህን አብይ ጉዳይ በተመለከተ ፍፁም ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ መያዝ እንዳለበት ዛሬ ማታ ስሴት ልጁ ለመንገር ለራሱ ቃል ገባ። በዚህ ሁሉ መካከል የቀረበው ምግብ ግሩም ነበር። አባ ቬርሣው፣ ስለአበሻ ነገሥታት የሚታወቀውን ሁሉና በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ በጀስዊቶች ሃይማኖቱን ስለለወጠውም ንጉሠ ነገስት ጭምር ተናገሩ። ጀስዊቶች፣ ሲታሰቡ የሚኖሩባቸውን ታሪኮች በኢትዮጵያ ውስጥ መሥርተው እንደነበር፣ በተጓዳኝ ደግሞ ከአገር እንዲወጡ ታላቅ ሃይማኖታዊ ጥቃት በካቶሊካዊያን ላይ እንደተፈፀመባቸውም አስረዱ። ከዚህ በመቀጠል ተልዕኮው ሊያጋጥመው የሚችለውን አደጋ፣ የአየር ጠባዩንና በጉዞው መስመር ላይ የሚገኙ ሕዝቦችን እጅግ አሰቃቂና ጭካኔ ያለባቸው መሆናቸውን ገለፁ። ምሣ ሲጠናቀቅ ሁሉም ተጋባዥ በደስታና በፈንጠዚያ ስጋዊ ስሜቱ አመዝኖበት ይታይ ነበር። ምንም እንኳ የውይይቱ ርዕስ ክስተር ያለ ጉዳይ የያዘ ቢሆንም፣ እንዲህ ያለ ታላቅ ደስታና የጋለ ስሜት በዚህ ቤት ውስጥ የማይታወቅ



መሆኑን ቆንሲሉ አመነ። ሁለቱ እንግዳ ጀስዊቶች፣ በንፅፅር ሲታይ ጥሩ ሁኔታ ላይ አልነበሩም። አንደኛው፣ በተለይም አባ ብሬቬዳንት፣ ስለሚፀፀታቸው ጉዳይ የሚናገሩትን አላቋርጥ አለ። ሌላኛው፣ ከበፊቱ ይልቅ እያለቀሱና በርበሬ እየመሰሉ ከሦስተኛው ብርጭቆ ወይን በኋላ በተቀመጡበት ማንጐላጀት ጀመሩ።

ጋባዦችና ተጋባዦች ምሣቸውን አጠናቅቀው ገበታው ከፍ በሚልበት ጊዜ፣ አስተናጋጁ ቀርቦ ሙሴ ፖንሴ መምጣቱን ተናገረ። ሴቶቹ ወዲያውኑ ወጡ። የቀሩት የንጉሠ ነገስቱ ሥዕል ባለበት የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ቡና እየጠጡ ሊቀበሉት ወሰኑ።

ፖንሴ ወደ አዳራሹ ገባ። ልብሶቹን ለመቀየር አልተጨነቀም። ጥቁር ሰማያዊ ጃኬቱን ሳያቆልፈው በሸሚዙ ላይ ደርቧል። ባርኔጣ የለውም። እጅጌዎቹ ቁልፎች የሏቸውም። ከዘራም አልያዘም። ዞር ሲል፣ ጥቁር ጥምልምል ፀጉሩ በነፃነት ይዘናፈላል። ሲገባ፣ እርሱን የሚመለከተው ጭውውት ወደ ደስታ ስለተለወጠ፣ አረንጓዴ ምልክት የሚታይባቸውን ቀጫጭን እጆቹን እያወዛወዘ በአየር ውስጥ የሚንሣፈፍ ይመስል ወደፊት ተራመደ። ቆንሲሉና ሦስቱንም ቀሣውስት፣ እያንዳንዳቸውን አይኖቻቸው ውስጥ እየተመለከታቸው ሰላምታ አቀረበላቸው። ቆንሲሉ የመግቢያውን ንግግር አደረገ።

በቀጥታ ከንጉሠ ነገስቱ ሥዕል ሥር በባለመደገፊያ ትልቅ ወንበር ላይ የተቀመጡት አባ ቬርሣው በግርማ ሞገስ ተናገሩ።

«ሙሴ ጆን ባፕቲስት ፖንሴ» ሲል በትህትና ጀመረ። «ወደ አበሻ ንጉሥ በሚደረገው ጉዞ ተካፋይ በመሆን የፈረንሣዩን ንጉሠ ነገስት መልዕክት ለማድረስ መስማማትህን በይፋ ተናግረህ ልታረጋግጥልን ትችላለህ?»

የፖንሴ ፊት በደስታ ፈካ።

«ጌቶች፣ በአንድ የሚያባድፍ ጉዳይ ላይ ያላችሁ ይመስለኛል» አለ እየሣቀ። «እስከአሁን ከፊት ለፊታችሁ እንደተገተርኩ አለሁ። ከሰዓት በፊት፣ ሙሉውን ጊዜ ስስራ ነው የዋልኩት። ሙቀቱ ሌሎቹን ሰዎች ከመንቀሣቀስ ባገደበት በዚህ ሰዓት ወደዚህ የመጣሁት

ጭር ባለው ጐዳና ብቻዬን ተጉገዤ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ቡናና ብስኩቶችም እመለከታለሁ፡፡ . . . »

«ትክክል ነህ» አለ የጥድፊያ ጉዳይ ስላለበት ማድረግ ይገባው የነበረውን ያላከናወነው ቆንሲል፡፡ «እባክህ ተቀመጥ? ምን እናቅርብ? ማቼ፣ እባክህ ጣዕም ያለው አንድ ስኒ ቡና፣ ለሙሴ ፖንሴ . . . »

ወጣቱ ሰው የሚፈልገውን ወዲያውኑ አገኘ፡፡ ቡናውን ቀስ እያለ ጠጣው፡፡ የጭውውቱን ርዕስ ወደ ንጉሠ ነገስቱ ሥዕል በመቀየር፣ የታደሰበትን ዘዴ፣ በግቢው ሲገባ በቆንስላው የአትክልት ሥፍራ ስላያቸው ዛፎች ተናገረ፡፡ ጭውውቱ እየሞቀ ሲሄድ ሌሎችም በዚያው ርዕስ ላይ የበኩላቸውን ሲያክሉበት በድንገት ርዕሱን ለውጦ አሁን በጀመሩት ጉዳይ ላይ አደረገው፡፡

«ክቡራን ሆይ! እንግዲህ የነገስታትን ንጉስ እንዳከም ልትልኩኝ ትፈልጋላችሁ? በእውነት እምልላችኋለሁ ሃሣቡ ግሩም ነው፡፡ እንዲያውም እጅግ በጣም ግሩም ነው፡፡ ስለጉዳዩ በጥልቀት ሳስብ፣ ወደዚያች አገር ሲገባ ወዲያውኑ የማይገደል ሰው ቢኖር፣ ሐኪም ብቻ ሊሆን እንደሚችል በግልፅ ማየት ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን አሁን በዙፋኑ ላይ ያለው ንጉሠ ነገስት የኔን አገልግሎት መሻቱን እንድታስቡ ያደረጋችሁ ምክንያት ምንድነው?»

«ንጉሡ ራሱ የህክምና ባለሞያ ፈልጉ ለዚሁ ሲል ሰው ልኳል፡፡ በዚህ ሰዓት፣ ሃላፊነት የተሰጠው አንድ መልዕክተኛ፣ ሐኪም ይዞለት ለመሄድ እዚሁ ካይሮ ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህን መረጃ በጣም ከሚታመን ምንጭ ያገኘነው ነው፡፡ ስለዚህ አንተ አብረኸው ትኄዳለህ»

«ንጉሡ እኔ ሳልደርስ በፊት ካልሞተ መልካም ነው፡፡»

«በማንኛውም መልኩ ግን ሙከራ መደረግ አለበት» ሲል ቆንሲሉ አከለ፡፡

«ከሥራችን ዘርፎች አንዱ የሕክምና ጥያቄ ጉደይ ነው» በማለት በጣም በተለመደ ቅላፄ ጣልቃ ገብተው አባ ቬርሣው ተናገሩ፡፡ «ሆኖም ግን አንተም እንድታመጣልን የምንፈልገው መልዕክት አለ»



«ምን እንደሆነ በትክክል ቢነግሩኝ?» ሲል ጃን ባፕቲስት ጠየቀ

«ደህና» አሉ አባ ቬርሣው፣ ጭውውቱ ወደተፈለገው ጉዳይ በመለወጡ ተደስተው፡፡ «ከዚህ በኋላ የግርማዊ ንጉሡ ነገስት ሉዊስ 14ኛ መልዕክተኛ መሆንህንም በትህትና ታስታውቃለህ፡፡ የፈረንሣይ ንጉሠ ነገስት፣ በአበሻ የክርስቲያን ግዛት ዘውድ ላይ ታላቅ ስሜት እንዳላቸውም ታስረዳለህ፡፡ የፈረንሣይን ንጉሠ ነገስት በኃያልነት፣ በታላቅነት፣ በቅድስና ደረጃ የሚመጣጠናቸው እንደሌለ በተቻለህ መጠን ታስረዳለህ፡፡ የአበሻው ንጉሥ፣ እስከመጨረሻው ድረስ፣ የምዕራቡ ዓለም ንጉሥ ምን እንዳለው እንዲረዳ በማድረግ፣ የፈረንሣይን ንጉሥ ለመጐብኘት እንዲፈቀድለት እንዲጠይቅ ማድረግ ይገባል፡፡ ከዚህም በላይ የኢትዮጵያው ንጉሥ ወደዚህ ደማቅ ብርሃን ፊቱን የመመለስ ፍላጐት የራሱ ነው፡፡»

«ባማረ ሁኔታ የተገለፀ ነው፡፡ እንበልና እኔ መልዕክቱን በሚገባ ሳስተላልፍ፡፡ ነገር ግን ከዚህ ሁሉ ጥረት እናንተ ምን ተጨባጭ ውጤት ይታያችኋል?» አለ ፖንሴ

«የምንሻው፣ የአበሻው ንጉሥ በአፀፋው ወደ ቬርሣይለስ መልዕክተኛ እንዲልክ ነው፡፡ የሚላከው የኤምባሲ ጓድ በጣም ብልህና አስተዋይ መሆን ይኖርበታል፡፡ የሚመራውም የንጉሡን ሙሉ እምነት ባገኘና በከፍተኛ መኳንንትና መሣፍንት አጀብ ውስጥ ሊካተት በሚችል ሰው መሆን ይኖርበታል፡፡ በመጨረሻም አንድ በጣም ወሳኝና እጅግ ከፍተኛ ጉዳይ አለ፡፡ ኤምባሲው፣ ፖሪስ በሚገኘው በታላቁ የሉዊስ የቅደመ ዝግጅት ትምህርት ቤት ገብተው ሊማሩ የሚችሉ ብዙ ወጣት ኢትዮጵያውያንን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡ እነዚህ ወጣቶች በቋንቋችን፣ በባህላችንና በሃይማኖታችን በዓለም ሁሉ ላይ የተቀዳጀናቸውን ክብር ይመሰክሩልናል» ሲሉ አባ ቬርሣው ቀጠሉ

«ስለተፈፃሚነቱስ የምትሰጡኝ ደብዳቤ አለ?» ሲል ፖንሴ ጠየቀ፡፡

«አስፈላጊ የሆኑ ማህተሞችና ጥብጣቦች የተለጠፉበት ኦፊሴል ደብዳቤ» ሲል ቆንሲሉ ጣልቃ ገብቶ ተናገረ፡፡

«ሆኖም እንዳይነካብህ ደብቀህ ልትይዘው ግድ ነው። መልዕክቱ የሚሰጠው ለንጉሡ ለራሱ ብቻ ነው» ሲሉ አባ ቤርሳው ቀጠሉ።

«ገብቶኛል። ሊያጋጥም የሚችለውን ችግር ከኔ አንፃር ሆናችሁ ልትመለከቱት ብትችሉ፣ እንደሚመስለኝ ዲፕሎማሲያዊው ተልዕኮ ተጨማሪ ሥራ ነው ማለት እንችላለን» አለ ጆን ባፕቲስት

ያልገባው ይመስል ተደንቆ «ተጨማሪ?» በማለት ቆንሲሉ ተናገሬ።

«አዎን ተጨማሪ ነው። ሁላችሁም እንደምታውቁት እኔ መጀመሪያ ነገር በሙያዬ ዲፕሎማት አይደለሁም። ወደዚያ የምሄድ ከሆነ የምንዘው ንጉሡ ነገስቱን ከሕመሙ ለማዳን ነው። መነጋገር ያለብንም ይህንኑ ነው»

«ምንድነው የምንነጋገረው። በቀላሉ አዎን ወይም አይሆንም ብለህ ትነግረናለህ። ጉዳዩም በዚህ ላይ ይቋጫል» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀ።

«ይቅርታ ክቡር ሆይ። አሁንም ሊታሰብባቸው የሚገቡ ዝርዝር ጉዳዮች አሉ። የመጀመሪያው በክፍያ መልክ ምን ማግኘት እንደምችል ማወቅ እፈልጋለሁ።» አለ ጆን ባፕቲስት።

«ክፍያ አሉ?!» ሲሉ አባ ቬርሣው በመደነቅ ደገሙ። «የንጉሰ ነገስቱን ፍላጐት እንድታደርስ ነው የተጠየቅከው። ክብሩ . . . »

«እያንዳንዱ ሰው የሌለውን ይሻል።» ሲል ፖንሴ በትንሹ እንደማሣል አድርጐ አቋረጣቸው። «እኔ የሌለኝ ደግሞ ገንዘብ ነው።»

ቆንሲሉ በድንጋጤ አተያይ አባ ቬርሣውን ተመለከታቸው።

«ባለፀጋ የማይከፍል ከሆነ ድሃውን እንዴት በነፃ ላክመው እችላለሁ?» አለ ጆን ባፕቲስት በከበበው ትልቅ ዝምታ ያልተረበሸ በመምሰል።



«ጌታዬ» አሉ አባ ቬርሣው በመጨረሻ። «ንጉሡ ነገስቱ ሃኪም ይፈልጋል። ስለዚህ የህክምናውን ወጭ እርሱ ራሱ ይከፍልሃል። የኛ ድርሻ የጉዞህን ወጭ ብቻ የሚመለከት ይሆናል»

«አስተሳሰብዎን እቀበላለሁ» አለ ፖንሴ የቀረፋ ብስኩቱን እየነከሰ።

«ስለክፍያው ለንጉሰ ነገስቱ አመለክታለሁ። ሆኖም ግን እስቲ ወጭውን እንመርምረው»

ከዚህ በኋላ ሁሉንም ሰው ያሣተፈ ውይይት ቀጠለ። በዚህ መካከል፣ ቆንሲሉ በፅሁፍ ሊሠፍር ይገባዋል ያለውን ቃል ከዳን ዶክተሩ አንጥሮ አወጣው። በዚህ መሠረት የዕቃ ማጓጓዣ ወጭውን፣ ባለመኖሩ ምክንያት ከሥራውና ከደንበኞች ሊያገኝ ሲገባው የሚያጣውን ሂሣብ ለመተካት የሚሉት በፅሁፍ ይጠቀሣሉ። ያመጣቸው የህክምና መገልገያ ቁሣቁሶች ዋጋ፣ መሣሪያዎቹ ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆኑ ሲደረጉ አስቀድሞ ይከፈልባቸዋል። በዚህም ላይ ሙቀት የሚሰጡ ልብሶችና መሣሪያም እንዲታከልለት አጥብቆ ጠይቆ ነበር። በተጨማሪም ለጉዞው የሚሆኑ የከርቻ የጋማ ከብቶች ሂሣብ፣ እያንዳንዱ መስፍን ግዛቱን የሚያቋርጡ ሁሉ ሊከፍሉት የሚገባውን የቀረጥ ሂሣብ በሚታሰበው ወጭ ላይ መደመር ነበረበት።

ቆንሲሉ በወጭው መናር ቢደነግጥም በተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ ተስማማ። በዚሁ መሠረት በዚያኑ ዕለት ለዘመዱ ለሙሴ ፖንቻርትሬይን ወጭው እንዲፀድቅ የሚጠይቅ ደብዳቤ ለመፃፍ ወሰነ።

«እሺ እንግዲህ፣ ጥያቄውን ተቀብያለሁ። እናንተ በፈለጋችሁበት ጊዜ ወደ አበሻ አገር እሄዳለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት በመጨረሻ

በክፍሉ ውስጥ በጉልህ የሚታይ እፎይታ ሰፈነ።

ስምምነቱ አንድም ነገር ሳይስተዋል እንዳይተላለፍ መከናወን ስላለበት «እንዲያው አንዱት ነገር ማከል እፈልጋለሁ» አሉ አባ ቬርሣው።

እጃቸውን ወደ ሥራ ባልደረባቸው በመዘርጋት «አጅበውህ የሚሄዱት አባ ብሬቬዳንት እኒሁና»

«የጀስዊት አማኝ ወደ አበሻ አገር ሊሄድ? የአበሻው ንጉሥ ነገስት ላለፉት ሃምሣ ዓመቶች እንደጠላት ሲያወግዛችሁ ነበር። አባቴ፣ ይህን አይነት አደጋ ያለበት ሁኔታ ማንም ሰው እንዲቀበለው በበኩሌ አልጠይቅም» አለ ፖንሴ።

«አንተ እንዲቀበሉ እየጠየቅሃቸው አይደለም። እኛ የታዘዝነው በንጉሥ ነገስታችን ነው። አሁን በትክክል እንደጠቀስከው ጉዳዩ የተፈፀመው ከሃምሣ ዓመት በፊት ነው። መቼም ነገሮች ይለዋወጣሉ። አባ ብሬቬዳንትንም ጀስዊት አስመስለህ አትወስዳቸውም። በዚህ ረገድ ጥያቄ እንደማይኖር ርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ። እዚህ እጣቸውን የሚያውቃቸው አንድም ሰው የለም። በአጭሩ ተራ አገር ጎብኚና ሂሪ ናቸው። እዚያ ስትደርሱ ደግሞ እንበልና አገልጋይህ ይሆናሉ»

ፖንሴ፣ ለአፍታ ያህል የመከላከያ ምሽግ እንዳገኘ ተዋጊ ሰው በመደሰት ከአባ ዴ ብሬቬደንት ጋር ዓይን ለዓይን ተያየ።

«እርሳቸው ከፈቀዱና ከተስማሙ እሺ፣አገልጋይ ናቸው» አለ ፖንሴ

ከዚህ በኋላ ወደ ጀስዊቱ ቄስ ዞር ብሎ «ከእንግዲህ በኋላ ዮሴፍ ብለን እንጠራዎታለን። ይህን ስም ይስማማዎታል አባቴ?»

አባ ብሬቬደንት ወደ መሬት አቀረቀሩ።

«ይህን የጉዞ ዘመቻ እስከመረጥን ድረስ እኔ እንዳችም ነገር ያለርሱ ላከናውን የማልችለው ሸሪክ አለኝ። ይህ ሰው አብሮን ሊጓዝ የሚችልበት ሁኔታ ካለ . . . » አለ ጆን ባፕቲስት

«ሁጎኖቱን?» ሲል ቆንሲሉ በድንገት በከፍተኛ ድምፅ ተናገረ። /ሁገኖቶች የፈረንሣይ የካልቪኒስት ፕሮቴስታንት አባላት ሲሆኑ በ16ኛውና በ17ኛው ክፍለ ዘመን በተከታታይ ከብዙሃኑ ካቶሊኮች ጋር የርስ በርስ ጦርነት ያካሄዱ አማኞች ናቸው/



ይህን እንደተነገረ አባ ቬርሣው ከመቀመጫቸው ላይ ብድግ አሉ።

«ጌታዬ፣ ጥያቄህን ሁሉ እንደተቀበልን እምናለሁ። በሌለህ መብት ላይ ብዙ አታስቸግረን። ንጉሥ ነገስታችንና ቤተክርስቲያናችንን በእጅጉ በሚመለከት ጉዳይ ላይ አንድ የፖለቲካ ስደተኛን መጨመር ከቶም ሊታሰብ የሚችል አይደለም። ይህን በቀላሉ መረዳት ትችላለህ። ስለዚህ ጉዳይ ከእንግዲህ በኋላ አናነሣም»

ስለ ጉዞው ሜትር ዠረሚን ያላማከረው ፖንሴ፣ ርዕስ ጉዳዩን አጥብቆ መያዝ ዋጋ እንደሌለው ስለተረዳ እዚሁ ላይ እንዲቆይ ወሰነ።

ሁለቱም ወገኖች ስምምነታቸውን በክብር አፀደቁት። ቆንሲሉ፣ ፖንሴን እስከ አዳራሹ ፊት ድረስ ሸኘው። ሲመለስ በክፍሉ ውስጥ በነበሩ ሰዎች ፊት ላይ የሚታይ ርካታ ነበር። የምስጋና መዝሙር ሲደረግ ቆንሲሉም ተካፈለ። ማቼ፣ በተለመደው ዘዴው ጉዳዩን በሰላም ለመጨረስ እንዲቻል አሳሰበ።

«እንግዲህ ሃጂ አሊ፣ ከካፑቺኖች ጋር የገባውን ስምምነት እንዲሰርዝ ማግባባት ብቻ ነው ያለብን» አለ በቁጣና በማስፈራራት ዓይነት።

ጆን ባፕቲስት፣ በቆንስላው ዕሕፈት ቤት በረንዳ ደረጃዎች ላይ ቆሞ በረዥሙ አየር ሣበ። በአቅራቢያው ከሚገኘው ከእዝባኪያ መናፈሻ ለአፍንጫው የደረሰው የጥድ ዛፍ ሽታ፣ በሞቃቱ አየር ውስጥ እየተግለበለበ አወደው። ነገር ግን ከበረሃ ገነቶች ጠረን ባሻገር፣ ከበረሃው መሃከ ማዶ የሚገኘውን አገር፣ እንዲያስሰው፣ እንዲያጠናውና እንዲመረምረው የተሳከበትን ምድር ለይቶ ያወቀው መሰለው። አየራት ከሚመነጉበት ከደጋማዎቹ ምድር ማህፀን ፈልቆ፣ የታላቁን ጅረት የፍሰት አቅጣጫ ተከትሎ፣ ከተራሮች ቁልቁል ወርደው የደረሱትን የእጣንና የቅመማት ሽታ መነሻ ያገኘ መሰለው። የአበሻን ምድር . . . ያልመው ነበር። ቬነስ በነበረበት ጊዜ ጓደኛው ባርባሪጐ፣ ስለ ጆአ ቤርሙዴዝ ታላቅ የጀብድ ጉዞ ነግሮት ነበር። ባርባሪጐ፣ የክሪስቶፈር ዳጋማ አሣሽ ሠራዊት አባል ነበር። ክርስቶፈር ዳጋማ፣ የቫስኮ ዳጋማ ልጅ ነው። ክሪስቶፈር ዳጋማ ማለት፣ ከአንድ ክፍለ ዘመን በፊት የሙስሊሞች ወረራ ኢትዮጵያን

ባሰጋበት ጊዜ ለድጋፍ የተላከ ሰው ነበር፡፡ ጆን ባፕቲስት ወደዚህ አገር ቀርጦና ተዳፍሮ ለመንዝ አይቃጣም ነበር፡፡ ወደ አዲስ ምድር፣ ወደ አበሻ ምድር የመንዙ ነገርም ህልም ብቻ ሆኖ ይቀርበት ነበር፡፡ አሁን ግን ሁልጊዜም በርግጠኝነት የሚያምንበት፣ የራሱ መልካም ዕድል ወደዚህች አገር የሚሄድበትን ሁኔታ አስገኘለት፡፡ ዕድሜውን ሙሉ አዲስ ዓለም ለማየት ይጓጓ ነበር፡፡ እንደ አፈታሪክ ስትነገር ከነበረች፣ ዝነኛና ሊደረስባት ከቶም አስቸጋሪ ከሆነች አገር የበለጠስ፣ ምን ዓለም አዲስ ሊሆን ይችላል? የአበሻ አገር፣ ጭር ያለችና የማትታወቅ ብትሆንም በወርቅና በታሪክ ክምችት ሀብታምና የበለፀገች ስለሆነች የሚመኟት አገር ነች፡፡

ፈረንሣይ ውስጥ በነበረው የፍሮንድ አማፅያን ዘመን፣ በመከራና በችግር ጊዜ ቢወለድም፣ አንዳችም ሀብትና መጠጊያ እንኳ ባይኖሩትም፣ ሃዘንና ተስፋ ቢስነት የሟት ዕድሉ ቢሆኑም፣ እንደዚህ ላሉ ስሜቶች ላለመሸነፍና እጁን ላለመስጠት ከረዥም ጊዜ በፊት ወስኖ ነበር፡፡ ጆን ባፕቲስት ፖንሴ፣ ያሣለፋቸውን የተድላና የደስታ ወቅቶች ወይም ደግሞ በአስገዳጅ ውጫዊ ሃይል ሥር ያልወደቀበትን ጊዜ ማሰብ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ አሁን የሚኖርባትን ከተማ በሚገባ አበጥሮ ካወቃትና እየሰለቸችው መምጣቷንም መገንዘብ ከጀመረበት ቅፅበት ጀምሮ፣ ዕድሉ - ያ መልካም ገዱ ጣልቃ ገብቶ፣ በአረቦች ወግ ውስጥ እንደሚጠቀሰው ዓይነት፣ ሕልሙ እውን ሊሆን ወደሚመኘው አገር ወሰደው፡፡

የነገሮች እንዲህ አዲስ የታሪክ አቅጣጫ መያዝ እየገረመውና እያስደነቀው፣ ጆን ባፕቲስት የቆንሲላውን ደረጃዎች በዝግታ ተራምዶ ወረዳቸው፡፡ በቆንስላው ግቢ ውስጥ በምትገኘው አነስተኛ የአትክልት ሥፍራ ፊት አዘውትሮ ቢመላለስም እንዲህ ወደ ውስጥ ገብቼ አያለሁ የሚል ቅድመ ሃሣብ ጨርሶ አልነበረውም፡፡ አሁን ግን ቆም ብሎ በሚገባ ተመለከታት፡፡ በስተቀኝ ባለችው ጠባብ የጠጠር መንገድ በኩል ጉድጓዳ ሣህን የመሰለ አረንጓዴ መስክ ሲኖር መሃሉ ላይ ከድንጋይ ውስጥ እየፈለቀ የሚንዠቀዠቅ ምንጭ አለ፡፡ ወደ ምንጯ ሄደ ፡፡ ከምንጯ በስተኋላ ከዚህ በፊት አይቶ የማያውቀው አንድ ትንሽ ዛፍ ተመለከተ፡፡ በራሱ የሕልም ዓለም ሃሣብ ቢጨነቅም፣ ጆን ባፕቲስት ዓለምን በአዝርዕትና ዕፅዋት ተመራማሪ ዓይን አያት፡፡ በዛፉ ቁጥቋጦ አጠገብ ተንበርክኮ፣ ክብ ቅጠሎቿን መረመራቸው፡፡ ቀጥሎም፣ አንድም ምን የሚባል ዕፅ እንደሆነ በመፅሐፎቹ ውስጥ ለይቶ ሊያውቀውና ሁለተኛም የዕለቱ ማስታወሻ እንዲሆነው በማለት የእንጨት እጀታ ያለውን ቢላዋ



ከኪሱ አውጥቶ ትንሽ ቅርንጫፍ ቆርጦ ለመውሰድ አሰበ፡፡ በመጀመሪያ፣ በዙሪያው የሚመለከተው ማንም ሰው እንደሌለ ለማረጋገጥ ዐይኖቹ አማተሩ፡፡ ወዲያውኑ እነዚያ ድንገተኛ አይኖቹ በሁለተኛው ፎቅ ላይ ቆማ እግሮቿን በደፋ ላይ ካሳረፈችው ከማዳሞዜል ዱ ማይሌ አይኖች ጋር ተጋጯ፡፡ እንደርሱው ሙሉ በሙሉ ተገርማ ስለነበር ዓይኖቹን ይነቅላል ብላ አልገመተችም፡፡

ጆን ባፕቲስት፣ አሁን ባለበት ጥሩ መንፈስ ውስጥ ሆኖ ይህን የሁለተኛ ጊዜ ግንኙነት ለብዙ ቀናት እንደአስደሣች ምልክት ሲተረጉመው ቆየ፡፡ በዚህም የራሱ ትርጉሜም ፈገግ ይላል፡፡ እርሷ አሁንም እነዚያን ለማያዊ ጥብጣቦች ሸብ አድርጋቸዋለች፡፡ ይህን የተለመደ ጉልቶ የሚታይ ነገር ከሩቅ ስላየ ጆን ባፕቲስት የወጣቷን ሰልከክ ያለ ሰግላጋ ቁመና ሆን ብሎ በበለጠ ነፃነት ለማየት አሰበ፡፡ አፍንጫዋ አጭር ቢሆንም ቀጥ ያለ ነው፡፡ ኩል ከመሰሉት የገረጡ ዓይኖችዋ ለርሱ ፈገግታ ምላሽ በምትሰጥበት ጊዜ የስበት ሃይላቸው ሁሉ ተሟጦ ይጠፋል፡፡ ነገር ግን አፍታም ሳትቆይ እነዚያን በሰልፍ የተሰደሩትን ነጫጭ ጥርሶችዋን ገልጣ አሣይታው፣ የርሱን አይታም አቀጣጥላ ምልስ አለች፡፡ ጆን ባፕቲስት፣ በመስኩ ላይ ተንበርክኮ ለጥቂት ጊዜ ከቆየ በኋላ ተመልሣ ብቅ እስክትል ድረስ ለመጠበቅ ሲል ብድግ አለ፡፡ መስኮቱ እንደተከፈተ ቀርቷል፡፡ በዝግታ ወደ ጠባቧ መንገድ አምርቶ ጉዳናው ውስጥ ገባ፡፡ ከዚያም ጊዜውን ለማኅባደድ ወደ ቤቱ ተጓዘ፡፡

ይህ የቀረበለት ያልተለመደና እንግዳ የሆነ የጉዞ ሃሣብ ዳግመኛ ተመልሶ ህሊናውን ያዘው፡፡ የማዳሞዜል ዱ ማይሌ በድንገት ብቅ ማለት፣ ትናንትና በሃዘንና በትካዜ ውስጥ ጥሎት የነበረው፣ ዛሬ ደስታውን ጨመረለት፡፡ ሁሉም ነገር እንደገና ሊሆን የሚችል ሆነ፡፡ ከዚህ በፊት በቬነስ፣ በፖርማና በሊዝቦን እንደነበረባቸው ጊዜያት ሁሉ እንደገና እግር ተወርች ያልታሠረ ነፃ ተጓዥ መሆኑ ተሰማው፡፡ ይህን ማሰቡ በራሱ ደስታን እንዲያስበው አደረገው፡፡ የሚፈልገው፣ የሚሻውና የሚጠይቀውም ይህንኑ ነበር፡፡

# 8

የአሥራ አራት ዓመት ኮረዳ እስክትሆን ድረስ፡ አሊስ ዴ ማይሌ መልከ ጥፉ ሕፃን ነበረች:: ወላጆችዋ ውጭ አገር ለመኖር ከሄዱ በኋላ፣ ያደገችው ቺኖን አጠገብ በሚገኝ የእመምኔቶች ገዳም ውስጥ ነበር:: በውፍረቷና በርበሬ በሚመስሉት ጉንጬችዋ ምክንያት የሚያስቁ የቅፅል ስሞች ነበሩዋት:: እርስዋ ከምታስታውሳቸው መካከል ሁለቱ «በርበሬ ጉንጮ» እና «ዱባ ፊት» የሚሉት ይገኙባቸዋል:: ምንም እንኳ በተፈጥሮዋ መልከ ጥፉ ብትሆንም፣ አንዳንዶች የሚጠሯት ለራሳቸው ለመደሰትና እርስዋን ለማብሸቅ በማለ ነው:: የሚፈራት ወይም የሚቀናባት አልነበረም:: በርስዋ መልከጥፉነት ሣቢያ ሌሎች ኀሸሸ ሲያደርጓቸው፣ እርሷ ደግሞ ፍቅራቸውን ትቸር ነበር:: የሰውነትዋ መጠን የተለየ መሻሻል ባይታይበትም አካሏ የራሱን የዕድገት ለውጥ ማሣየቱን ቀጠለ:: በስድስት ዓመቷ መልከ ጥፉ ሆና የገባችበትን የእመምኔቶች ገዳም፣ በአሥራ አራት ዓመትዋ ግብፅ የሚገኙትን ወላጆችዋን ለመቀላቀል ስትለቅቀው መልከ ጥፉ እንደሆነች ቆይታለች::

ከዚህ በኋላ ግን አንዳች የትኩሣት ሀመም በሰው ፊት ላይ እንደሚፈጥረው ድንገተኛ ሽፍታ፣ ሲገለፅ የማይችለው ድንቅ ውበትዋ መፍሰስ ጀመረ:: ቁመቷ ረዥምና ሸንቃጣ ሆነ:: መልከ ጥፉ ያደረጋት የውፍረት ክምችት ሁሉ ቀልጦ ሽቅብ እንድትመዘዝ አደረጋት:: በርበሬ ይመስሉ የነበሩ ጉንጬችዋ ገርጣ ማለት ጀመሩ:: የፊትዋ ፀዳል ያልተለመደ አዲስነት፣ የሚያበራና በእጅ ቢነኩት የሚቆሸሽ መሰለ:: ወደ ኋላ ተስቦ ሲታሰር ወይም ከህፃንነትዋ ጀምሮ በሹርባ ሲጐነጐን የነበረው ወፍራም ፈዛዛ ቢጫ ፀጉርዋ፣ መልኩን ወደ ጥቁር ሃርነት በመቀየር ላይ ሲሆን ፊትታ ለቅቃዋለች:: እንዳለመታደል ሆኖ፣ ይህ ውበት በርስዋ ላይ መፍሰስ የጀመረው ማንም ከውጭው ዓለም ይህን ትመስያለሽ የሚል ማረጋገጫ ሊሰጣት በማይችልበት የብቸኝነት ጊዜዋ ነበር:: የወላጆችዋ ዕይታ ለርስዋ የሚገልፅላት አንዳችም ሚዛን የለውም:: የመልኳንና የአካሏን ሁኔታ ልትገልፅላት የምትችል የሴት ጓደኛም አልነበረቻትም:: ዘወትር የምትጠቀመው መስተዋትም፣ ብቻውን የሚነግራት አንዳችም የለውም:: አካላዊ ለውጡ በመሻሻል ላይ መሆኑ ቢሰማትም፣ ራሷን በተመስከተች ቁጥር ሊያጋጥም የሚችል አደጋም ይታሰባታና ይታያት ጀመር:: በብቸኝነት የቆየችበት አስፈሪ ጊዜም



ስሜቷን እንዲያዛብባት ስጋት አደረባት:: ካይሮ በሚገኘው ውብ የወላጆችዋ መኖሪያ ውስጥ አንድም ሰው አይታ አታውቀም:: ወይም በሌላ አገላለፅ አንድም ሰው አይቷት አያውቅም::

ወደ ካይሮ እንደመጣች፣ ከጥቂት የቀድሞ የትምህርት ቤት ጓደኖችዋ ጋር የልጃገረድነት ደብዳቤ ልውውጦችን ታደረግ ነበር:: ይሁን እንጂ ምንም ዓይነት የመልስ ደብዳቤ ሳይደርሣት ሲቀር ወይም ቢመጣላትም እንኳ ከረዥም ጊዜ በኋላ ሲሆንባት ከሌሎች ሰዎች ደብዳቤ መጠበቋን ተወችው:: እርስዋም መፃፏን አቋረጠች:: በካይሮ ቆይታዋ ጥቂት የፒያኖ ትምህርቶችን ቀስማለች:: ነገር ግን የዚህ መማሪያ መምህርቷ፣ ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ቆንስላው ግቢ ስታመራ ድንገት በመንገድ ላይ በመውደቁ ለአሥር ቀናት ያህል ራሷን ስታ ቆይታ ሞተች:: አባ ጋቦሪ ደግሞ የላቲን ቋንቋ ሊያስተምሯት ሞክረው ነበር:: እንደ እውነቱ ከርሣቸው ይልቅ እርስዋ ቋንቋውን በተሻለ ታውቀዋለች:: በእመምኔቶች ገዳም ትምህርት ቤት ቆይታዋ፣ በላቲን ቋንቋና ባትወደውም እንኳ በሂሣብ ትምህርት ጉብዝ ተማሪ ነበረች:: የላቲን ትምህርቱን እንዲቋረጥ አባቷን አጥብቃ ለመነችው:: ከዚህ በኋላ የቀራት ነገር ማንበብ ብቻ ነበር:: የቆንስላው ቤተመፃሕፍት በበቂ መጠን የተሟላ ነው:: የተፈጥሮ ሣይንስችና የጥንታዊ ትራጀዲ መፃሕፍት ያስደስቷታል:: የሚያንቃቁ መፃህፍት በጣም ያበረታቷታል:: ከነዚህ መካከል የላፎንቴይን እና የፌኔሎን ቴሌማኩ መፃህፍት ተጠቃሾች ናቸው:: አባቷ እንዳታነብባቸው የሚያወግዛቸውን፣ እርሱ ራሱም ያላነበባቸውንና ሌላም ሰው እንዳያነብባቸው፣ ግን ሣይሸሽጋቸው ያሉትን የተለያየ አቀራረብ ያላቸውን ረዥምም ልብወለዶችን በራስዋ ጥረት ማግኘት ቻለች:: ጆግናይቱ ሴት በፍቅር የተጨቆነችበት ላፐሪንሲስ ዴ ክልቬስ የተሰኘው መጽሃፍ፣ አዲስ ዓለምን አሣያት:: ይህን መፅሀፍ ዳግመኛ ከእጇ ሳትጥለው አቆየችው:: ሕልም ለማለም ማንም ቢሆን ቆንጆ መሆን አይጠበቅበትም የሚለውን ከህፃንነትዋ ጀምሮ ያረጋገጠችው እውነታ ነው:: በዚህ ዓለም ህይወት ውስጥ፣ ደስታን የማስገኘት ዕድል ይሰጥ እንደሆን በሚል ለተወሰነ ጊዜ የአካልዋ ጉዳይ በሃሣብ ውስጥ ከትቷት ነበር:: በመጨረሻ ግን እርግጠኛነት ወደሌለውና ወደራስ አለመተማመን መራት:: በዚህ ሣቢያ የራስዋን ስሜት በሚቀሰቅስና ደስታን በሚሰጣት ዓለም ውስጥ ተመልሣ ገባች:: በዚህም፣ ቢያንስ ከሁሉም ይልቅ አመዛዛኝ ስለሆነች በሁሉም ዙሪያ አድናቆትን አገኘች::

ከጁስዊት ቀሣውስት ጋር ምሣ ከበላች በኋላ፣ ይህች ወጣት በመኝታ ቤትዋ መስኮት አዘንብ ተቀምጣ በቆንስላው የአትክልት ሥፍራ ውስጥ የሚገኙትን የዛፎች ቅጠሎች

ታስተውል ጀመር፡፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት ሲነገር ስለነበረው ስለአበሻ አገር ማሰብና ማሰላሰል ጀመረች፡፡ በዙሪያዋ ያለው ዓለምና የአበሻ አገር እጅግ በጣም ቅርቧ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን በቀላሉ አይደረስባቸውም፡፡ ሌሎች ልጀገረዶች ይህን ጊዜ ስለነዚህ አገሮች ያልሙ ይሆናል፡፡ በአንፃሩ በዚህ ቦታ እርስዋ ልትወለድበትም ትችል ነበር፡፡ ቀለሟ ጥቁር ቢሆን ኖሮ ብላ መቃዠትም ጀመረች፡፡ እንደ ወተት አረፋ በሚነጣው ክንዷ ላይ የሚገኘውን አምባሯን ተመለከተችውና ደኸው ብጫና አብረቅራቂ አምባር፣ በጥቁር መደብ ላይ ቢሆን ኖሮ ምን ሊመስል እንደሚችል ብላ አሰባ ተደነቀች፡፡ ክንዶችዋን በመስኮቱ ላይ እንዳሣረፈች በዙሪያዋ የሚገኙትን ቁሣቁሶች ሁሉ ዘንግታ ጤናማ በሆነው የራስዋ ተመስጦ ውስጥ ሰመጠች፡፡ የጊዜው መንጉድ ሣይታወቃት ሃሣቧን ከአንዱ ርዕስ ወደሌላው እያቀያየረች ጭልጥ አለች፡፡

እርስዋ በታች በሚገኘው ፎቅ የፊት ለፊት ደረጃ ላይ በድንገት ድምፅ ሰማች፡፡ ድምፁ በበሩ አጠገብ ሰው የተመለከተው የአባቷ ድምፅ ነበር፡፡ ሰውዬው ከፎቁ ሲወርድ በአይኖችዋ ተከታተለችው፡፡ ከኋላ ስትመለከተው ቀጭን፣ ባርኔጣ ያላደረገ፣ የራስ ቅሉ በሚዘናፈል ፀጉር የተሸፈነ፣ የቆዳ ቦት ጫማ ያጠለቀ ሰው ነው፡፡ በጠባቡ መንገድ ላይ ሲሄድ ቆም አለ፡፡ እርስዋም መከታተልዋን ቀጠለች፡፡ እርሱ ግን ከመንገዱ ፈንጠር ብሎ በመውጣት በመስኩ ላይ ተራመደ፡፡ እርስዋ ራሷ አስተውላው በነበረውና ከሌሎች ተራ እፅዋት ጋር ከማይመሣሰለው ትንሽ ዛፍ አጠገብ ሲደርስ ተንበረከከ፡፡

የጕብኚውን ሰው ቅርፅ መለየት ቻለች፡፡ ሰውዬው፣ ከትናንት በስትያ በክዛሊጅ ድልድይ ላይ ያየችውና እስዋን በተለየ ሁኔታ ሲመለከታት የነበረው ነው፡፡ ተክለ ሰውነቱ ቁፍጥን ብሎ፣ማራኪ ቁመና ያለውን ነው፡፡ እንዴት ተዝናንቶ በርከክ እንዳለና እንዴትስ አድርጐ ቢላዋውን ከኪሱ ውስጥ እንዳወጣው፣ ቅርንጫፉንም እንዴት በቀላሉ እንደጨበጠው አስተዋለች፡፡ በቆንስላው ውስጥ ያጋጠሟት ጥቂት ሰዎች ሁለት ፍፁም ተፃራሪ የሚመስሉ ዓይነቶች ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ የአጋጣሚ ዓይነት ምሁራን፣ ትሁቶች፣ ለራሣቸው ሙሉ ክብር የሚሰጡ፣ ግትሮች፣ በጣም የሚከበሩ፣ በተለይም በሚተገበር ጉዳይ ላይ ተፈጥሯዊ እንቅቃሴን ማከናወን የማይችሉ አስመሣዮች ናቸው፡፡ ሌላኛዎቹ ዓይነቶች ሕዝባውያን፣ ሁሉንም ተግባር የሚያከናውኑ ነገር ግን ከምንም የማይቆጠሩ ናቸው፡፡ ምግብ አዘጋጆች ይሁኑ፣ ጋሪ ነጂዎች ይሁኑ፣ ዘበኞች ይሁኑ እንደ ጠበብት ክችች ያሉ ናቸው፡፡ በዚህ ሣቢያ፣ ማንም ቢሆን ፀጥ፣ረጭ ብለው ተደብቀው ቢቆዩለት ይመርጣል፡፡ ከፊት ለፊትዋ የሚታየው ወጣት ግን



የሁለቱንም የህብረተሰብ ክፍሎች በጋራ አጣምሮ የያዘ ቅይጥ ይመስላል፡፡ ተክለ ሰውነቱ የጌታ ነው፡፡ ትዕግስቱ የአጃቢ ነው፡፡

እንዲህ እየተከታተለችው እያለች ምናልባት በድንገት እታይ ይሆን? የሚል ስጋት አልተሰማትም፡፡ በርስዋ ፍልስፍና በእንቅልፍ ላይ ያለ ሰው ከቶም እንደማይጋለጥ ሁሉ፣እሲስ አሁንም በህልም ዓለም ውስጥ ነች፡፡ ሆኖም ግን ይህ ወጣት ሰው ዓይኖቹን ወደርስዋ ወረወራቸው፡፡ በማህበረሰቡ መካከል፣ በማይታወቅ ሰው እየተመረመሩ ለሚኖሩ ሁሉ በጣም ጤነኛ የሆነው ይህ ልዩ ስሜት ከተሰማት ምን ያህል ጊዜ ይሆን ይሆን? በርግጥ ከህፃንነት ካለፈች በኋላ ምናልባት አንዳንድ ጊዜ አባቷ ራት ከሚጋብዛቸው ሽማግሌ ቀሣውስት በስተቀር እንዲህ ያለ ስሜት አንድም ጊዜ ተሰምቷት አያውቅም፡፡ ነገር ግን ራሱን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ሰመፈተሽ ያቀረበ፣ ተፈጥሯዊ አቋሙን የጠበቀና ግልፅ መደነቁን የሚገልፅ ሰው አይታ አታውቅም፡፡ እንዲህ ባለ ግራ መጋባት ውስጥ ሆና፣ ለርሱ ፈገግታ፣ የፈገግታ መልስ ሰጠች፡፡ ከመፍራቷ የተነሣ ከመስኮቱ ሦስት እርምጃ ወደኋላ ተራመደችና ወዲያውኑ ተፀፀተች፡፡ እጆችዋን ጀርባዋ ላይ አጣምራ፣ የመኝታ ክፍሏን የእንጨት በር እየዳበሰች፣ በሃይል እየተነፈሰች፣ ስሜቷ ታውከባት ለረዥም ጊዜ ፀጥ ብላ ቆመች፡፡ በነዚያ ዐይኖች ውስጥ የነበረው የጋለ ስሜት ግን አመለጣት፡፡ ስሜታዊ መልስዋ ግን፣ አንድ ህፃን በጣም የሚያስደስት ገጠመኝን ተመልክቶ እንደመቦረቅ ፈንታ አደጋ ይኖራል ብሎ ሲያስብ እንደሚሮጥ ዓይነት ነው የሆነችው፡፡

ለምንስ ወደኋላ ተራመድኩ? ስትል ራስዋን ጠየቀች፡፡ ያ ወጣት የሚያስፈራ አይደለም፡፡ እኔም አልፈራሁም፡፡ አልፈራሁም፡፡ ከዚህም በላይ ፍፁም ታማኝና ትሁት ይመስላል፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ አባቴ በፍፁም ወደዚህ አይጋብዘውም ነበር፡፡ በመስኮቱ ወደ ውጭ ማየቴ ምን ጥፋት ነው? አንድ ጐብኚ ከቆንስላው ግቢ ሲወጣ መመልከትስ ምን የሚያስነውር ነገር አለበት?

ለረዥም ጊዜ ከራሷ ጋር ተከራከረች፡፡ በመጨረሻም አንደኛው ሃሣብ አመዝኖ የክርክሩ ትግል ሲቋረጥ ተመልሣ ወደ መስኮቱ ሮጠች፡፡ እንግዳው ሰው ግን የለም፡፡

ጠበቀችው፡፡ ሰውዬው ግን አልተመለሰም፡፡ በመጨረሻም ፊቷን ወደ ክፍሉ መለሰች፡፡ በቤቱ ውስጥ ያለው ሙቀት ማቃጠል ጀምሯል፡፡ ከውጭ፣ ረጋ ባለው ነፋስ የሚወዛወዙት

ዛፎች ጥቂት እፎይታን ቢያስገኙም በቤቱ ውስጥ ግን አንዳችም የለም። አረንጓዴ የአልጋ ልብስ የተነጠፈበትን አልጋ፣ የስሚ የመጀመሪያ ፊደል የተጠለፈበትን ትራስዋን፣ ወፍራም አረንጓዴ ጨርቅ የለበሰውን ትንሽ ጠረጴዛ፣ ተጣጣፊውን ወንበር፣ መፃህፍቶችና፣ ጥቂት የሸክላ አሻንጉሊቶችን ተመለከተቻቸው። እነዚህ የተለመዱ ዕቃዎች ብዙ ቀን ያፅናኑዋት ቢሆኑም፣ እንዳታመልጥ አስረው ያስቀመጧት ናቸው። የሰውዬው እይታ እነዚህን ዕቃዎች እርቃናቸውን አስቀርቶ አጋለጣቸው። ከነዚህ እቃዎች አንዳችም የመፅናኛ ነገር ሳታገኝባቸው ፊትዋን በእጆችዋ ውስጥ ሸፍና ቆማ አነባች።

«አረንጓዴ!» አለ ቆንሲሉ፣ ቁርጥ ባለ ድምፅ «በትክክል ሰምተኸኛል። ከሁለት ቀናት አስፈሪ ስቃይ በኋላ እንደበሰበሰ ፍሬ ወደቀ»

«ክቡር ሆይ፣ እንዳስተረጉም ጥቂት ጊዜ ይስጡኝ» አለ ሙሴ ማቼ እጆቹን እያወራጨ

ሃጂ አሊ፣ በፊቱ ላይ አስፈሪና ስሜት የሚነካ ሁኔታ እየታየበት በጆርባው ተንጋልሏል።

«ሕመምተኛው ሞቶ እንደሆነ ማወቅ ይፈልጋል» ሲል ፀሐፊው አስተረጐመ

«የለም። እስከአሁኗ ሰዓት ድረስ በርግጥ አልሞተም። ለረዥም ጊዜ ያህል ግን ተሰቃይቷል። እንዲያውም ከስቃዩ እንዲገላገል በመፈለግ እንዲገድሉት ሁሉ ተማፅኗል። ይሁን እንጂ እኛ ክርስቲያኖች ነፍስ ማጥፋት በእምነታችን አይፈቀድልንም» አለ ሙሴ ማይሴ እንደ ምሁር።

ሀጂ ግንባሩን በእጁጌው ጠረገና ወደ ዲፕሎማቱ ዞሮ፣ ሙሉ በሙሉ ዓይኖቹ ውስጥ አየው።

«ለመሆኑ በትክክል የሆነውን ነው በእርግጠኛነት እየነገርከን ያለኸው?» ሲል ጠየቀው።



«እርግጠኛ ነኝ። ዜናውን ያገኘሁት እየሩሣሌም ከሚገኙት የተከበሩ የሥራ ባልደረባዬ ነው። ሰውዬው፣ ቁስጥንጢንያ ለሚገኙት አምባሣደር ሙሴ ዱ ፌሪዩል በራሣቸው እጅ ነው የፃፉላቸው። ለአምባሣደሩ ደግሞ አስቸኳይ መልዕክት በሚያደርስ ሰው በኩል ይህንኑ ገለፁልኝ። እንዲያውም ፈረሱ እስከአሁን ነጭ ላብ እያላበው መሆኑን በፈረሰኞቹ ጋጣ ውስጥ ሲያዩት ይችላሉ»

ማቼ አስተረጐመ።

«አንድ የካፑቺን መነኩሴ ነው» ካለ በኋላ አስቸጋሪ ትምህርት ወደቤቱ ይዞ የሚገዝ ተማሪ ይመስል ዝግ ባለና በግልፅ አነጋገር «እንዲያውም ራሱን የሕክምና ዶክተር እንደሆነ በማስመሰል በቅርቡ ከእየሩሣሌም ለቅቆ ወደ አሌክሣንደሪያና ካይሮ በሚመጣ ጀልባ ላይ የተሣፈረ ነው። ይኸው የሚባለው ሰው መሆን አለበት። አይደለም?»

«መሆን አለበት» አለ ሃጂ።

«በቁምጥና ሕመማቸው ላይ እርሱ አከሚኤአቸዋለሁ ያላቸው ሦስት በሽተኞች፣ እርሱ ከለቀቀ በኋላ ወደ ቆንስላው መጥተው ነበር። የሥራ ባልደረባዬ አንዱን በሕይወት አግኝቶታል። የቀሩት ሁለቱ ሞተዋል። የሁለቱ ሰዎች እጆቻቸው ወደ አረንጓዴነት ሲለወጡ አንደኛው ግን ኢጆቹን እንዳለ አጥቷቸዋል።»

ሊያስመልሰው ሲቃጣው አፉን በክርኖቹ መካከል ወሽቆ «ይበቃል። ሁሉንም ነገር ደጋግሚ እንዳትነግሩኝ» በማለት ሃጂ አሊ በከፍተኛ ድምፅ ጮሆ ተናገረ።

«ደግሜ የተናገርኩት አንተ ለመስማት ፈቃደኛ ስላልሆንክ ብቻ ነው። ታሪኩን አሁንም አላመንክውም»

«ያላመንኩትማ ሌሎች ካፑቺኖች ስላሉና ምናልባት እነሱ እንዳይሆኑ በማለት . . . »

«ይህን ርዕስ ጉዳይ በዚህ ላይ እናብቃው። እንዲያውም ላስጠንቅቅህ፣ ለንጉሡ፣ የሆነ አስመሣይ ሐኪም ይዘህለት የመሄድ ሃሣብ ካለህ ውሣኔው ያንተ ነው። ይህ ሚና እኔን መቼም አይመለከተኝም» አለ ሙሴ ዱ ማይሴ ተነስቶ እየቆመ።

«ይህን ካፑቺን ካልወሰድኩት ሌላ ምን አማራጭ አለኝ»

«በፈረንሣይ ማህበረሰብ ውስጥ መቶ በመቶ ብቃት ያለው ፈረንሣዊ ዶክተር አለ።»

«እርግጥ ነው? ለመሆኑ ማነው?» አለ ሃጂ አሲ ፊቱ በአድናቆት እያበራ

«ፓሻውን ራሱን የሚያክም አንድ መድሃኒት ቀማሚ ነው»

«ኦ አዎን፣ አዎን፣ ስለርሱ ሰውዬ ሰምቻለሁ። ግን እኮ ሁሉም ያው ነው። ፈረንሣውያን ደግሞ ከቱርኮች ያለችግር ምስክርነት ያገኛሉ። ታድያ ይህ ትንሽ አያስቸግርም?»

«የቱርኮች ምስክርነት ስትል ምን ማለትህ ነው። የኔ ምስክርነትስ? የሰም፣ የሰም፣ የዚህን ሰው ብቁ መሆን በይፋ የምመሰክር እኔው ነኝ። የራሴን ባለቤት አክሞ የፈወሳት ሰው ነው»

ሃጂ አሲ የተጠራጠረ መሰለ።

«ካፑቺኖዎች ከዚህ ሰው እንድጠነቀቅ ነግረውኛል» አለ በመጨረሻ

«በምን ምክንያት? ቅር ባትሰኝብኝ እነዚህ ሰዎች በስም ማጥፋት ዘመቻ ላይ ተሰማርተዋል ማለት ይሆን?»

«ሃይማኖተኛ አይደለም»

«ሃይማኖተኛ እንኳን አይደለም?!» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ በመደነቅ ተናገረ። «በመጀመሪያ ነገር ይህ ሐሰት ነው። ሰውዬው ቤተክርስቲያን ይሄዳል፣ ይጸልያል። ሁለተኛው ነገር፣ የሃይማኖት ጉዳይ ከተነሣው ጥያቄ ጋር ምን ግንኙነት አለው? ሰውዬው ጥሩ ሐኪም ከሆነ ሌላው ጉዳይ ምን ይፈይዳል»

«በዚህ ጉዳይ ላይ እግዚአብሔር ካልተጨመረበት በስተቀር ምንም የሚሆን አይደለም።» አለ ግመል ነጂው ራሱን እየነቀነቀ



«እስቲ አንተ ራስህ ምን ይሰማሃል? አንተ ሞሃመዳዊ ነህ። ሐኪሙ ካቶሊካዊ ነው። ንጉሡ ደግሞ ፕሮቴስታንት ነው። በዚህ ላይ ምን ዓይነት እግዚአብሔር ነው ሊታሰብ የሚችለው?»

«እግዚአብሔርማ እግዚአብሔር ነው» አለ ሃጂ አሲ። ጣቶቹን ከንፈሮቹ ላይ እያማረፈና ሽቅብ ወደ ሰማይ እየተመለከተ።

«እንግዲያው የአሌክሣንደሪያውን የክፕቲክ ፓትሪያርክ ይዘሃቸው ሂድና እስቲ አባክዎ አባቱ ተአምር ያሳዩ ብለህ ጠይቃቸው» ሲል ቆንሲሉ ጮኸ።

ሙሴ ዴ ማይሌ አሁን እየተገነዘበ ያለው፣ ሰውዬው በእግዚአብሔር የማያምነውንና እርሱ መርጦ ያቀረበውን ውሰደው ይለኛል ወደሚል አዝማሚያ እየገፋው መሆኑን ነው። ዝሂህም ሳቢያ ፀጥ አለ። ነጋዴውም ለረዥም ጊዜ በራሱ ሃሣብ ተውጦ ቀረ።

ከእየሩሣሌም መጣ ስለተባለው መልዕክተኛ ታሪክ ለማመን ወይም ላለማመን ሃጂ አሲ ግራ ተጋባ። የርሱ ዓለም የበረሃ ዓለም ነው። በርሱ ዓለም ውስጥ የማይመስሉ የሚባሉ ነገሮች እምብዛም እውነት አይባሉም። ሃጂ አሲ በጣም እርግጠኛ ሆኖ ያወቀው ጉዳይ ግን፣ የቆንሲሉ ፍላጎት፣ እርሱ ከካፑቺኖ መነኩሣት ጋር ያለው ግንኙነት እንዲቋረጥ፣ በነርሱ ፈንታ ይህን ፈረንሣዊ ሃኪም እንዲወስድ ጠንካራና ጥያቄ የማይቀርብበት ፍላጎት እንዳለው ነው። ሃጂ አሲ፣ ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም በፍጥነት አሰላና ሰባኪዎቹ ለዚህ ሃላፊነት እንደማይኖርባቸው ወይም እንደማይወቀሱ ተገነዘበ። አንደኛ፣ ሰባኪዎች የገቡለት ምንም ቃል ኪዳን የለም። እንዲያውም እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ ለርሱ ውለታ እንደሚውሉለት ዓይነት እያስመሰሉት ነው። ከዚህም በላይ መነኩሣቱ ቅፍለቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ ናቸው። በነርሱ ሣቢያ ቱርኮች ብቻ ሳይሆኑ በጉዞው መስመር ላይ የሚገኙ ተወላጅ ሃይሎች ሳይቀሩ ድንጋጤ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። በአንፃሩ ለፈረንሣዊው ሃኪም የሚኖረው ጥርጣሬ ግን አነስተኛ ነው የሚሆነው። ይልቁንም ይህ ሐኪም እንዲሄድ የራሱ መንግስት የሚፈልግ ከሆነ በክፍያው ላይ ሊደራደሩ ይችላሉ።

ሃጂ አሲ በአሣዛኙና አስቸጋሪው ሁኔታ ምክንያት እርር ኩርምት ብሎ አለቀሰ።

«ለምን እንደሚያለቅስ እስቲ በቅን መንፈስ ጠይቀው» አለ ቆንሲሉ፣ ሙሴ ማቹን እየተቆጣው።

«እቅዱን ለውጦ ሌላ ሐኪም ሲወስድ የሚያጋጥመውን ከፍተኛ ወጭ በማሰብ እንደሆነ ነው የሚናገረው»

ምስጋና ይግባህ አምላኬ፣ በመጨረሻው ከምንፈልገው ላይ ደረስን በማለት፣ ቆንሲሉ ለራሱ ተነፈሰ።

ውይይቱ ለተጨማሪ ግማሽ ሰዓት ቀጠለ። ሙሴ ዴ ማይሌ ወደትንሽ ሣጥን ሦስት ጊዜ መመላለስ ግድ ነበረበት። ግመሎች መቀየር አለባቸው፣ መልዕክተኞች አስቀድመው መላክ ይኖርባቸዋል። የምሥጋና ፀሎትም ለእግዚአብሔር መቅረብ ይገባዋል። በከፍተኛ አትኩረት ሲከናወን የነበረው ጉዳይ በሁለቱም መካከል በመተማመን ተቋጨ። እያንዳንዳቸው ረክተው ተለያዩ።

ஜ

የድርድሩ ውጤት በመልካም ሁኔታ መቋጨቱን ሲያውቁ፣ አባ ቬርሣው በማግስቱ እንደሚሄዱ አስታወቁ። የጉዟቸው አቅጣጫ ሌላ ሥራ ወደሚጠብቃቸው ወደ ደማስቆ ነው። እራት በፍጥነትና በፀጥታ ተበላ። አባ ብሬቪዳንት፣ የአለቃቸውን የመጨረሻ መመሪያ ለመቀበል ከዕኩለ ለሊት በኋላ መጡ። ሁለቱ ቀሣውስት ውይይታቸውን በሁለተኛው ፎቅ ላይ አደረጉ።

ሙሴ ዴ ማይሌ በሥራ ብዛት ስለደከመው በጊዜ ተለያቸው።

ከማህበረሰቡ ሰፈር በማይርቅ በአንድ የመጨረሻው ትንሽ መንገድ ላይ ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዣረሚ የሚወዱትን አንድ ጠርሙስ የወይን ጠጅ በደስታ ጨለጡ። አሥር ሰዓት ሲሆን ወደ በረንዳው ወጡ፡ ከባድ የአሸዋ አቧራ የተሸከመው ነፋስ የምሽት ከዋክብቶችን ሸፈናቸው። በአየር ውስጥ የነበረውን የቀን ሙቀት አንቆ የያዘው የጋብቻ ወራት ገና በመጨረሻዎቹ ሣምንቶች ላይ ስለሆነ፣ ከአረቦች መንደሮች ሁሉ የእታሞዎችና የዕልልታ ድምፆች ያስተጋቡ ጀመር።



«የለም፣ የለም፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የኔ መካፈል ጨርሶ ጥያቄ የሚነሣበት አይደለም» አለ ሜትር ዣረሚ ውይይታቸውን በመቀጠል።

«ቢሆንም ቆንሲሉ ጨርሶ ሊያውቀው አይገባም። እኔ አንዳችም ቃል አልተነፍስም። እኔና አንልጋዬ ከተማውን ለቅቀን እንወጣለን። አንተ መንገዱን ወርደህ ትንሽ ራቅ ብለህ እናግኝህ»

ዣረሚ፣ የእርሳስና የቆርቆሮ ቅይጥ የሆነውን ዋንጫ በአንድ እጁ ይዞ ሌላውን እጁን በባለሥልጣን አነሣስ መልክ ከፍ አደረገው።

«እርባና የለውም! መልሱ አይሆንም ነው»

«እንዲያ ከሆነ የየራሣችንን የተለያየ መንገድ እንሄዳለን?»

ለመጀመሪያ ጊዜ ከአምስት ዓመት በፊት የተገናኙት ቬነስ ውስጥ ነበር። ጆን ባፕቲስት፣ የሻምላ ውጊያ መምህር ይፈልግ ነበር። በፖለቲካ ምክንያት ከአገሩ ወጥቶ አንዳች ታላቅ ነገር ይሻ የነበረና በሌላ ስም የሚታወቀውን፣በቀላሉ የሚበሣጭ፣ ባልጥቁር ፀጉር ፈረንሣዊ ስደተኛ አገኘው። ተማሪዎቹ ሜትር ዣረሚ በሚባል ስም ያውቁታል።

«እና እንዲህ መሆኑ ነው» አለ ፕሮቴስታንቱ እንደመተከዝ ብሎ።

የጦር መሣሪያ ባለሙያነት ላይ ከመሠማራቱ በፊት፣ ዣረሚ ከፀሐይ በታች በሚገኙ የተለያዩ የእጅ ሥራዎች ላይ ተሰማርቶ ነበር። ከነዚህ ሁሉ ይልቅ ይበልጥ ፍቅርና ዝንባሌ የነበረው በመድሃኒት ቅመማ ዝግጅት ላይ እንደሆነ ያስታውሣል። ይህ የሆነው፣ ጆን ባፕቲስት ቁሶች በውስጣቸው ምን እንደያዙ የሚያስገነዝበውን የሙከራ ሥራ ስላስተማረው ነበር። በዚህ ትምህርት ሣቢያ የኮራዶ ውጊያውን ሙያ ተወው። የሁለቱም ጓደኝነት ተጠናክሮ፣ ሸሪኮች መሆን ችለው ወደ ምሥራቃዊ ሜዲቴራኒያን ተሰደዱ።

«ደህች ዓለም!» ሲል ዣረሚ በሰገነቱ ላይ ከሚገኘው መደገፊያ በድንገት ተስፈንጥሮ ወደ ኋላው ተራመደ። በኋላም «ይህ ሁሉ የእኔ ጥፋት ነው» አለና ተንሰቅስቆ አለቀሰ።

በረንዳው ላይ ሁለት ጊዜ ሃይል የታከለባቸው እርምጃዎች ከተራመደ በኋላ ወደ ሸሪኩ መለስ አለ።

«የምንለያየው፣ እኔ ለመቅረት ስለፈግሁ ሣይሆን አንተ ለአንድ ወገን ብቻ የሚያደላ የሥራ ስምምነት በችኮላ በመቀበልህ ነው» አለው።

«ካይሮን ትቼ ወደ አዲሱ ዓለም መሄድ እፈልጋለሁ ስትል የነበረው ትናንት አይደል እንዴ?» አለ ጆን ባፕቲስት ራሱን በመከላከል።

«አዲሱ ዓለም! እና ይህ ማለት እኮ በዚያ ቆንሲል ትዕዛዝ ማለት አይደለም። ሰው ወዳልደረሰበት ምድር እንኳ የምሄድ ብሆን፣ እመነኝ ከጀስዊቶች ጋር ስንተት አልሄድም»

«ወይ ጉድ፣ ጀስዊቶች? እነሱ እኮ ማስመሰያዎች እንጂ፣ ምንም አይደሉም። ለመሆኑ ለዚህ ተልዕኮ እኔ ጠቀሜታ ያለኝ ይመስልሃል? ለኤምባሲያቸውና ለንጉሡ አገልግሎት ደንታ የለኝም። ነገር ግን ፈረሶች፣ ትጥቅና መሣሪያዎች ሰጥተውኝ ሊያጀቡኝ ቢሞክሩ፣ እኔ የባሰ ጅል ሆኜ ስጦታውን አልቀበልም ልበል እንዴ?»

«ምንም ልዩነት የለውም። አሁንም ታስረሃል።»

«ታስረሃል? ትቀልዳለህ። እነሱ ከኔ የሚጠብቁትን መፈፀም እንዳለብኝ የተፃፈ ነገር የለም። አንዳች ቦታ ቀልቤን ከሣበው እዚያው እቀራለሁ፣ ወይም አንዳች የሚመራኝ መንገድ ካገኘሁ እከተለዋለሁ። ኤምባሲያቸው ቢሻው ራሱን ያንጠልጥል። የአበሻን አገር ለማየት ከፍተኛ ጉጉት አለኝ። የምሄድበትም ብቸኛው ምክንያት ይኸው ነው። ከዚህ በላይ አገሩ የሚስማማኝ ከሆነ በዚያው እቀር ይሆናል»

ለረዥም ጊዜ ዝም ተባባሉ። ሜትር ገሬሚ ምንም ሳይተነፍስ ቆይቶ፣ ሻማ ይበራበት ወደ ነበረው ቤት ገባ። ሁለት ሻምላዎችን አነሣ፣ ከተለፉ ቆዳ የተዘጋጁትን ሁለት የደረት መከላከያዎችንም ያዘ። ወደ መድሃኒት ቀመማው ሙያ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የሻበላ ግጥሚያ በበጋው ወራት ምሽቶች የጊዜ ማሣለፊያቸው ነበር።

«በል ተነስ፣ ደህና አድርጌ አውቅሃለሁ። ትሄዳታለህ» አለው ጆን ባፕቲስት፣ ሻምላቸውን ሣያገናኙ በፊት።

«የለም፣ አላደርገውም። ሃሣቤን ልታስለውጠኝ አትችልም። ቢሆንም መልካምና ሰላማዊ ጉዞን እመኝልሃለሁ» አለ ሜትር ገሬሚ

ሁለቱ ሻምላዎቻቸው እንደተጋጩ፣ ሲጫናቸው አሰፍስፎ የነበረው ትካዜ ብትን አለ።



# 9

ወደ አቢሲኒያ ለሚደረገው ቅፍለት፣ ዝግጅት መደረግ ነበረበት። የቅፍለቱ መሪ ሃጂ አሊ ሲሆን፣ ፖንሴና ወንድ አገልጋዩ ዮሴፍን ያካትታል። የቱርኮችን ጥርጣሬ ላለመቀስቀስ ሁሉም ነገር በተቻለ መጠን ሰላማዊ መምሰል ነበረበት። በዚህ የተነሣ፣ ቆንሲሉ በቅፍለቱ ውስጥ አንዳችም ተሳትፎ አይኖረውም። ጆን ባፕቲስትም ቢሆን ምንም ዓይነት የመነሣሣት ፍላጐት ማሣየት የለበትም። ግመሎቹንና በቅሎዎቹን፣ ኮርቻዎቻቸውን፣ ልጓሞቻቸውንና የጭነት ዕቃዎቻቸውን ሁሉ የገዛው ሃጂ አሊ ነበር። ለጉዞው ለሚያስፈልጉ የልብስ ዓይነቶች ነጋዴው የሚጠራውን ምንም ዓይነት ዋጋ የሚሸፍነው፣ ሙሴ ዱ ማይሌ እንዲሆን ታቅዶ ነበር። ይህ ስምምነት ሃጂ አሊ ተጨማሪ ትርፍ እንዲያገኝና በዚህም የሚችለውን ያህል ሽቀጣሽቀጥ በከብቶቹ ላይ ለመጫን ያስችለዋል። ይህ ነገር አቢሲኒያ ደርሶ፣ ሸቀጦቹ በወርቅና በጥሪኝ ዝባድ ከተለወጡ የነጋዴውን የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት በአሥር እጥፍ ያሣድግለታል።

ቆንሲሉ፣ ኦፊሴል ደብዳቤ አዘጋጅቶ ለአበሻው ንጉሥ ፃፈ። ጽሁፉ በሙሴ ማቼ አማካይነት ወደ አረብኛ እንዲተረጐም አደረገ። ይበልጥ ጥንቃቄ ለማድረግም ሲል ትርጉሙን በአረቦች መኖሪያ የሚኖሩት ሶሪያዊ ምሁር መካከሌ፣ ወንድም ፍራንሲስ እንዲያጣሩት አደረገ። ይህ ተከናውኖ ሲያበቃ፣ በደብዳቤው ላይ የፈረንሣይን ማህተም አሳርፎበት ለፖንሴ ተሰጠው። ከዚህ በተረፈ ቅፍለቱ ለሚያልፍባቸው አገሮች ገዢዎች የሚሰጡ ገፀ በረከቶች መሰብሰብ ነበረባቸው። የቀረጥ ክፍያውም ጥብቅ በሆነ የጉዞ ሰዓት የተወሰነ ነው። ይህ ዓይነቱ አሠራር ከጥንት ጀምሮ ሲተገበር የነበረ ነው።

ጆን ባፕቲስት በበኩሉ ሊገመት የሚችለውን ማንኛውንም ድንገተኛ አደጋ ለማከም የሚያስፈልጉትን የሕክምና መሣሪያዎች በመሰብሰብ ተወጥሯል። መድሃኒቶቹን የሚያስቀምጥበትን አዲስና ሰፊ የጠርሙስ ሣጥን፣ ሙሴ ዱ ማይሌ ሰጥቶታል። የዘመቻውን መሣሪያም፣ ጆን ባፕቲስት መርጧል። አንድ ትልቅ መስኬቶ ጠመንጃ በዮሴፍ ኮርቻ ላይ ሲጫን፣ ባሩዱና እርሣሶቹ ግን በፖንሴ ጥበቃ ውስጥ ሆነዋል። ከጥንድ ጉራዴዎች ሌላ፣ ለጆን ባፕቲስት ሁለት ሽጉጦችም ተገዝተውለት በኮርቻው ኮሮጆዎች ውስጥ ጭኗቸዋል።

ዝግጅቱ እየተካሄደ ሳለ፣ ቀንስላው የእንቅስቃሴው ጠቅላይ መምሪያ መሰለ። የቅፍለቱ አባላት የየዕለቱን እርምጃ ለመወያየት በየምሽቱ ልክ ከአራት በኋላ ይገናኛሉ። የወንድ አገልጋይ የተባሉት ዮሴፍ ጥርጣሬ እንዳያድርባቸው ሲባል የጀስዊት አለባበሳቸውን ተዉ። የቆንሲሉ የራሱ አገልጋዮች ምናልባትም አንዳንዶቹ ሰላዮችም ስለሆኑ ፈጥነው ሊጠረጥሯቸው ስለሚችሉ አልባሽ የተባሉትንም ማግግቻ እስካሁን አልተዋሃዱትም። አሊ፣ ፖንሴና ጉብሁን የማይከፈለው ነገር ግን በዝግጅቱ ላይ ድጋፍ የሚያደርገው ዝረሚ መግባታቸውና መውጣታቸው ሳይጠቀስ ወደ ቆንስላው ይመላለሳሉ። እንዲህ ያለው እንቅስቃሴ ከአጭር ጊዜ በኋላ እንደሚያስከትም ስለሚያውቅ የመግባትና መውጣቱን ነፃነት የፈቀደው ሙሴ ዱ ማይሴ ነው።

ሽርጉዱ ማዳም ዱ ማይሴን ቢያደክማትም፣ ልጇ አሊስ፣ በቤታቸው ዙሪያ ጥቂት ጉብኚዎችን በማየት መደሰቷ ርካታን ሰጥቷታል። ከሁሉም በላይ ግን በአትክልቱ ሥፍራ ውስጥ ብዙ ጊዜና በቅርብ ርቀት ያስደነገጠቻውን ወጣት ሰው በሚገባ ለመለየትና ማን መሆኑን ለማወቅ ዕድሉን አገኘች። እርሱ ግን በቀጥታ ጠርቶ እንዳያሽኮረምማት ብርቱ ጥንቃቄ ያደርጋል። ይሁን እንጂ፣ አሊስ በርግጥ ፊት ለፊት የሚነጋገሩ የሚመስላትን አስገራሚና አስደሳች ስሜት በውስጧ ፈጥራለች።

ይህን የመሰለው ስሜት የተፈጠረባት ሰዎቹ፣ ክቡዱን ጭንት መሸከም ያለባቸው ግመሎች ናቸው? ወይስ በቅሎዎች? በሚል ረዥም ክርክር ባደረጉበት ዕለት ነበር። ከተለመደው ዕውቀት በተቃራኒው ግመሎች ከበቅሎዎች ያነሰ ጭነት ይሸከማሉ በሚል ጆን ባፕቲስት ሙዝዝ አለ። እርሱና ሃጂ አሊ ሲከራከሩ፣ ቆንሲሉ፣ ሙሴ ማቼና አባ ብሬቬዳንት የየራሳቸውን አስተያየት አሰሙ። በሮች ሁሉ ክፍት ሆነው በቆንስላው ውስጥ አዲስ ስሜት ሰፍኖ ባለበት ውይይት መካከል አሊስ ገባች። ወደ አንድ ወገን ፈቅ ብላ፣ በአነስተኛ ብርኩማ ላይ ተቀምጣ፣ ጥልፏን እየሰራች እንግዶቹን ማጤን ጀመረች። ወዲያውኑ፣ ያ ወጣት ሰው ለራሱ እንጂ ለሌሎች እንደማያወራ ተሰማት። ይህ ስሜቷ በጣም እንግዳ ነው። የጆን ባፕቲስት ቃላት፣ ከፊት ለፊቱ ሆነው የሚመለከቱት ሰዎች ጠጣር አካል ላይ ነጥሮ የሚመለስና ከሰዎቹ በስተጀርባም ብርሃን የሚታይ መሰላት። ቃላቱ በጣም ልስልስ ብለውና በወራጅ ወንዝ ውስጥ እንዳሉ ክብ ጠጠሮች፣ ቀለሞቻቸው የማይነበቡና ዋናው ትርጉማቸው የተፋቀ ሆነው ደረሷት። በአጭሩ ለርስዋ የተረፋት እንድትደሰትበት ተብሎ የተሳከላትና



በትክክልም ግቡን የመታ ሙዚቃ ነበር። ሁለቱ ብቻቸውን ውይይት ቢያደርጉ ኖሮ፣ ስለቃላቱ ትርጓሜ ይበልጥ አትኩረት ትሰጣቸው ነበር። ነገር ግን ይህ የዝምታ ሃሣብ መለዋወጥ ከንፁህ ስሜት የመነጨ ነው።

ወጣቱ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደርስዋ አቅጣጫ ይመለከታል። ዓይኖቹ ከመስኮቱ ባሻገር ባለ ነጥብ ላይ ያነጣጠሩ ይመስላሉ። ሌሎች ሰዎች እንዲህ ያለውን አተያይ፣ ሃሣቡን ለመሰብሰብ የሚጥር ተናጋሪ የሚያደርገው ዓይነት ነው ብለው አስበው ይሆናል። እርስዋ ግን፣ አተያዩ ሁሉ ሙሉ በሙሉ በርስዋ ላይ ማረፉን በርግጠኝነት ተሰምቷታል። ከፊትዋና ከፊቱዛ ቢጫው ፀጉርዋ የሚወረወረው የብርሃን ፀዳል መልዕክቷን ተሸክሞ፣ እርስዋንነትዋን ታዝሎ፣ ወደ ጥልቁ የዓይኖቹ ውሃዎች ውስጥ፣ ወደ ምስጠራዊው ልቡ ውስጥ እንደዘለቀ አወቀች። ዓይን ወርወር የማድረግና የዕይታ ጨዋታ ስሜትን ካቀጣጠለ፣ የሚቀሰቅሰውን ውስጣዊ ስሜት ሊያባብሰው አይችልም። አሊስ፣ ወጣቱን ሰው ለመቅረብ ያላትን ስሜት ከማቀዛቀዝ ይልቅ እነዚህ አስቸጋሪ ምልክቶች ጭራሹኑ አባባሱት። እርሱ በበኩሉ በመካከላቸው ያለውን የመለያያ ርቀት ለማገናኘት አልጣረም። እርስዋ ደግሞ ይህን ልዩነት እንዲታስወግደው ያለችበት ስፍራና ያታዋ የማይፈቅዱላት ሆነ።

ከዕለታት አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ፣ አሊስ፣ ሊደርስባት ከሚችል የሞራል ውንጀላ ለመዳን፣ እናቷን መከላከያ አድርጋ ወጣቱ ሰው ወደ ቆንስላው ሲገባ እንደማንም ልታነጋግረው ቻለች። ሁለቱ እመቤቶች በትንሿ የመናፈሻ ሥፍራ ይንሸራሸሩ ነበር። ጆን ባፕቲስት፣ በነርሱ ቁመት ልክ ባለችው ጠባብ መንገድ ሲደርስ፣ እርሱ እንዲሰማት ጮክ ብላ፣ እርሱን ተንበርክኮ ያየችበትን ትንሽ ቁጥቋጦ እያመለከተች።

«እማዬ ይህ ሰው ስለዕፅዋት ብዙ ያውቃል። ትናንት ያየውና ለኛ የተለመደ ያልሆነውን የዚህ ቁጥቋጦ ስም ለምን አትጠይቂውም?»

ጆን ባፕቲስት ቆም ብሎ፣ ከወገቡ ጐንበስ አለና ባልተረበሸ ድምፅ መልስ ሰጣቸው።

«አዎ እንደናንተው አስተውዬዋለሁ። ምንነቱን ለማወቅም ጓጉቼ ነበር። ግን ተክሉ አውሮፓ ውስጥ የማይታወቅ ዝርያ ነው። ሌላው ቀርቶ፣ ጆን ሬይ በዕፅዋት ስም ዝርዝሩ ውስጥ አላካተተውም። ስለዚህ ዕፅ የተጠቀሰ ነገር ያገኘሁት በአንድ የግብፃውያን መፅሃፍ ላይ ነው። ዝርያው ራቅ ብሎ ወደ ደቡብ በጣም የተለመደና ተራ ነው። ተክሉ አሁን ከሚታየው በላይ ቁመቱ አያድግም። በሕይወት ዘመኑም የሚያብበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። አንዳንድ

ሰዎች፣ በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጠቀሰው አለባበት ቁጥቋጦ መገለጫ ትርጓሜ ነው ይላሉ»

እነዚህን የመጨረሻዎችን ቃላት ሲናገራቸው በቀጥታ በወጣቷ ልጃገረድ ዓይኖች ውስጥ እየተመለከተ ነበር። ወዲያውኑም ቀለበች። ሴትነትዋ በረታ። ጉንጮችዋ ፋሙ። እርሱም ዝቅ ብሎ ሰላምታ ሰጥቷቸው ተለያቸው።

የልጅዋን ግራ መጋባት ያላጤነችው ማዳም ዶ ማይሴ፣ ስለመፅሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የተገለፀውን በተደጋጋሚ እያሰበች ተደሰተች። በሚቀጥለው ሳምንት ታሪኩን ለንስሃ አባቷ ስትነግራቸው፣ እንዲህ ያሉ የመፅሀፍ ቅዱስን መልዕክት በምሣሌያዊና በሣይንሣዊ ማብራሪያዎች የሚገልፁ በድብቅ ሥልጣን ለመያዝ የሚሯሯጡ አድመኞችና የፍልስፍና ሰዎች እንደሆኑና እነርሱም ፀረ ሃይማኖት አቋም እንዳላቸው ተገነዘበች።

በቅፍለቱ ጉዞ ዋዜማ ላይ እነዚህ አስደሣች ትርምሶች ሁሉ ማብቂያቸው መድረሱን አሊስ በድንገት ስትገነዘብና ያንን ወጣት ሰው በቀጥታ እንዳለነጋገረችው ስትረዳ፣ በዚህ አደገኛ ጉዞ ላይ ይሞትም ይሆናል ስትል አሰበች። ልታደርገው የምትችለውስ ነገር ይኖር ይሆን? እንደተለመደው ከህልም ዓለሟ የሚመልሣት ነጥብ ላይ ስትደርስ አሊስ አቅማማች። ስለእውነተኛው ህይወት ምን ያህል ትንሽ ተሰጥኦ እንዳላት ተሰማት። ስሜቶችዋ ሁሉ፣ ፅይታዋ ሁሉ፣ የወጣቱ ሰው እሆናለሁ ብላ ስታስበው የነበረው ሃሳብ ሁሉ ምናልባት ከራስዋ የመነጨ እንደሆነ ስትል ለራስዋ ነገረች። ከዚህም ባሻገር፣ ለመሆኑ ሰውዬው ራሱ ሊያነጋግራት ሞክሯል? ወይም ደግሞ የፍቅር ደብዳቤስ ልኮላታል? የመጀመሪያውን እስተያየት ወይም ጥያቄ እርስዋ ብታቀርብለት በርግጥ ስህተቷን ይገልፅላታል። ዱብዬ ምን ትፈልጊያለሽ? እነዚህ በርበሬ ጉንጮች የት ያደርሷት ይሆን? ለነዚህ ማረጋገጫ እስካላገኘች ድረስ ተናቅሁ ብላ አትበሣጭም። እንዲህ ከሆነ ባለፉት ጥቂት የደስታ ዕለቶች አብረቃቅማ ያከማቸቻቸውን ጣዕረ ሞቶችና ጣፋጭ ህልሞች ሳይበላሹ ትጠብቃቸዋለች። ሌላ ምን ተስፋ ልታደርግ ትችላለች?

ግራ በመጋባት፣ ጆን ባፕቲስት የባሰ ነው። ሲመኘው የነበረውንና ጥልቅ ስሜት ያሣደረበትን ጉዞ ሊጀምረው ነው። ይህ ደግሞ ለጀብዱና ለእሰሳ ላለው አምሮት የሚመች ነው። ለዚህም በጋለ ስሜት በዝግጅት ላይ ተጠምዷል። አሁን ግን ይህችን ወጣት ሴት



ከተዋወቀበት ጊዜ ጀምሮ የጥርጣሬ ስሜት አድሮበታል። የተሟላና ትክክለኛ በነበረው ደስታው ላይ ጥላ አጥልቶበታል።

ለመጀመሪያ ጊዜ በከዛሊጅ ድልድይ ላይ በድንገት ሲገናኙና በቆንስላው ግቢ ለሁለተኛ ጊዜ ሲተያዩ ከነበረው የልበ ሙሉነት ትምክህት በኋላ፣ ተከታታይ የሆኑ ጉብኝቶችና መተያየቶች ተከስተዋል። ጆን ባፕቲስት፣ ይህችን ወጣት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያያት ብልጭ ያለበትን ስሜት፣ በቅርብ ሆኖ ሊያስተውላትና ሊያስላስላት ትርፍ ጊዜ ነበረው። በመሆኑም አሁን ስሜን ማወቅ ችሏል። ባለፉት ጥቂት ቀናት ያደረጓቸው ቅርርቦሾች፣ ሲጀመር የነበረውን ስሜቱን እያበለፀገለትና በጉልህ የሚታይ በማድረግ፣ በአዕምሮው ውስጥ የተቀረፀው የመጀመሪያው ውበቷና ምስጢራዊነቷ ሳይበታተኑበት፣አካል ቁመናዋ ሕልሙን ፈታለት። እንዲያውም፣ ባላያት ጊዜ፣ ያጣት ያህል የሚሰማው ስሜት ላይ ደረሰ።

በማህበራዊ መደቦቻቸው መካከል ያለው ልዩነት በመጀመሪያ ክፉኛ ይሰማው ነበር። እያደር ግን ችላ ሊባል እንደሚችልም ሲያስብ፣ ቀዝቀዝ ቢልለትም አሁን ደግሞ እንደገና ብቅ ማለት ጀመረ። በመካከላቸው የተጋረደው ግዳግዳ የማይገፋ ቢሆንም፣ ዓይኖቻቸው ግን እየጣሱት ይንከራተታሉ። ጆን ባፕቲስት ተስፋ መቁረጥ ጀመረ።

ዝግጅቱና የየዕለቱ ግንኙነት የለከበተው ለጥቂት ሣምንት ነበር። ብዙው ነገር በቅፍለቱ እንቅስቃሴ ስለተሸፈነ፣ ጆን ባፕቲስት የራሱን ስሜት እንኳ ለማጤን ጊዜ አላገኘም። ከዚህም ባሻገር ምስጢሩን ለማን ያካፍል? ሜትር ዝሪሚ እንዲህ ካሉ ጉዳዮች እንደሚሸሽና በዝምተኛ ፕሮቴስታንት ስጋት፣ በሻካራ ቋንቋ ሌሎች ላይ በሚደነፋ መካከል፣ መሃል ሥፍራ እንደሌለም ያውቃል። ጆን ባፕቲስት፣ የካይሮን ምስጢሮች ሁሉ ያገኛል። እርሱ ግን እህ ብሎ የሚያዳምጠው አንድም ሰው የለውም። ይህን ሁሉ በድንገት ሲያስበው ፍፁም ብቸኛውና ደስታ ቢስ ሰው የመሆን አዲስ ስሜት ይመጣበታል። ይሣካልኛል፣ ይሆንልኛል፣ ብሎ በታላቅ ስሜት በሚጀምረው ድንቅ ጉዞ ላይ ደንቃራ ይሆንበታል። ርህራሄን ለራሰ በመስጠት፣ ውቢቷ ላይ የሚኖረውን ተፃራሪ የሆነ ጥፍጥና ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰማው። በመነሻው ዋዜማ ሶስት ፀሐይ እንዳቆለቆለች ወደ አረቦች መንደር አመራ።

የሚያውቃቸውን ሁሉ ትቶ የሚሄድ ሰው አስቀድሞ በጥሞና ለማሰብ የሚችለው፣ ሣንዶቻቸው ዘርጣጣ የሆኑ ዘንባባዎች ባሉበት፣ ቅርንጫፎቻቸው የተጥመለመሉባቸው እጅግ

ትላልቅ የማንጎ ዛፎች በሞሉበት፣ ሻካራና ክቾች ያሉ ግራሮች በተጠቀጠቁበት፣ ለወይራ ተራራ ጥሩ አቻ ይሆናል ተብሎ የሚገመተውን የካይሮ ሰፈር ነው።

ሉተስፋ መቁረጥ ምንም ተሰጥኦ የሌለው መሆኑ የተሰማው ጆን ባፕቲስት፣ ወደዚህ ብቸኛ ቦታ ድርሽ ብሎ አያውቅም ነበር። የመናፈሻው ሰምሰም ተክሎች፣ ዘይታማ ሽታቸውን በፀሃይ ግለት ከምድር እየለቀቀ በሚነግው አየር ውስጥ ይተነፍሣሉ። በትካዜ ውስጥ ሆነው በባዶ እግራቸው ያሉ ሽማግሌ አትክልተኞች የሰጋ ችግኞችን ሥር ውሃ ያጠጣሉ። በደረቁ መሬት ላይ የሚፈስሰው ውሃ ሰስላሣና ውብ ድምፅ ይፈጥራል። ቀኑ ረዥም ነው። ፀሐይ የጠለቀች ቢሆንም፣ ሐምራዊ ጥላ የመሰለው ብርሃንዋ እስከምሽቱ ይዘልቃል። ጆን ባፕቲስት በአንድ አግዳሚ ላይ አረፍ አለ። በስህተት ምክንያት ባጣው ነገር ሃዘንና ትካዜ ስለገባው፣ ይህን ሁሉ ሰዓት እንደቅጣት በመክፈሉ በራሱ ድድብና ሣቀ። ዳግም ግን እንዲህ ላያደርግ ማለ።

በተቻለው መጠን ሁኔታውን በርጋታና በፀጥታ ሊመረምረው አሰበ። በመጀመሪያ ምንም ዓይነት ተሞክሮ የሌለው መሆኑን አመነ። ከረዥም ጊዜ በፊት ጀምሮ፣ የሴቶችን ስጦታ ያለድካም ይደሰትበት የነበረ ቢሆንም፣ ፍቅርን እርሱ በሌሎች ውስጥ ሲቀሰቅሰው እንጂ ፣አያውቀውም ነበር። እንዲህ ካለ አድሷዊ ስሜት የተማረው፣ ከቁጡ ቀናተኛ ባል እንዴት እንደሚያመልጥ ብቻ ነበር። አንድ ጊዜ፣ አንድ ግልፍተኛ ባል በአደገኛ ሁኔታ ከሼነስ እንዲለቅቅ አስገድዶት ነበር። ካይሮ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ግን፣ አንዳችም አደጋ እንዳይደርስበት ከቆንጃጅትና ፍላጐታቸው እያየለባቸው ጠልፈው ሊያስገቡት ከሚከጅሉት የኦቶማን ወይዛዝርቶች ሁሉ በጥንቃቄ ራሱን ሰማላቀቅ ችሏል። ከቤዮች አንዱ፣ ከተወዳጀው በኋላ ትልቋን ልጁን ሊጋብቻ ሰጥቶት ነበር። ይህ ጉዳይ በርግጥ አንዳች ግጴታ ታክሎበት ነበር። ይኸውም ጆን ባፕቲስት የእስልምናን እምነት መቀበል ነበረበት።

እንደዕድል ሆኖ፣ መቃበጦችንና ጊዜ ማሣለፊያዎችን ለፍቅር ሲል እንደማይወስዳቸው በጣም ግልፅ ነበር። እንዲህ ያለ ስሜትም እንደሌለው ያውቃል። ይህ ታዲያ ሃዘን ወይም ቅሬታ የሚፈጥርበት ሣይሆን ደረቅ እውነታ ነው። በመሆኑም እንዲትም ሴት ሰረዥም ጊዜ የሚቆይ ወይም አብሮ የሚኖር፣ ሽብርና ቅብጥብጥነትን የምትፈጥርበት፣ አዕምሮውን የመግዛት ሃይል ያላት፣ ፍቅርን ሲገልፅ የሚችለውን የልብንና የስሜት ህዋሣትን የማሸነፍ ስሜት የፈጠረችበት የለችም። እስከዛሬ የገጠሙትን ብሩህ እውነታዎች በመሰማመዱና በመደሰቱ፣ በነፃነቱ ላይ ገደብ የሚጥልበት ፍቅር አግኝቶት አያውቅም። ታላቅ የጀብዱ ተግባር ለመፈፀም ለጉዞ ሲነሣ፣ እጅግ የሚሣሣለት፣ ጥንቃቄ የሚሻውና ጭንቀት ውስጥ የሚከትተው የማዳሞዜል ዴ ማይሴ ሃሣብ፣ በቁርጠኛነት ሊከተላትና ሊያገኛት እንደሚገባው በውስጡ የተፈጠረበት የመጀመሪያው ትግል፣ ደስታ አልሰጠውም።

በአህያው ጀርባ ላይ ተንጋድዶ የተቀመጠ አንድ ሽማግሌ ሰው፣ በመንገዱ ላይ በዝግታ ያመጣል። እስካሁን ፀጥ - ረጭ ባለው ምሽት፣ የሽማግሌው ሰውዬ የድፍረት ማሽካካትና ለዚህ ምላሽ ደግሞ የታፈነ ድምፅ የሚመስለው የአህያው ኮቴ ዜማዊ ቅላፄ ይሰማል። በአህያው ጐን የተንዘሰጠሉት ክሮጆዎች እሾሃማ ፍሬ ተሞልተዋል። ሰውዬው ቀረብ ሲል፣ ጆን ባፕቲስት ምልክት አሳየው። በመቀጠልም ሣንቲም ሰጥቶት አራት ፍሬዎችን ተቀበለ።

በፍቅር ወጥመድ በመያዙ ፀፀት አልሰማህ አሰው። ምክንያቱም አሁን የያዘው በርግጥ ፍቅር ነው። ነገር ግን ምን ሊያደረግ ይችላል? በአዕምሮው የሚመጣለት ብቸኛው መፍትሔም እርባና ቢስ ነው። ካይሮ ውስጥ ቢቆይ ቆንሲሉ እጅግ በጣም ይቆጣል። ሊያጠቃው እና ምናልባትም ዳግመኛ እንዲሰደድ ሊያስገድደው ይችላል። በዚህ መልክ የቆንሲሉን ሴት ልጅ ማሰብ በራሱ የማይመስል ነገር ነው። ልጅቱ በርግጥ ምላሽዋን ሰጥታዋለች። ይህን ያደረገችው በብቸኝነት ስለኖረች ቢሆንም፣ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ በሁሉም ነገር ከፍ ከሚል ቤተሰብ የተገኘች ወጣት ሴት ነች። በተለይም አሁን በርስዋ ዓለም ደረጃ ሊሆን የሚችለውን አጭር የዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ የማይቀበለው ከሆነ፣ እርሱን የመሰለ ሰው፣ እርስዋን የመሰለች ሴት ለማስደሰት የሚያስችል ሃሣቡ እንኳ ሊኖረው አይችልም። በሌላ በኩል ይህን ተልዕኮ የማይቀበለው ከሆነ፣ እርስዋንም እስከነአካቴው ዳግመኛ ላያያት ይችላል። ምናልባት ደግሞ ይህ የተሻለው መፍትሔ ይሆናል። በዚህ መልክ ሁሉም ነገር ያልፋል። ጉዞ ደግሞ ትዝታን ያስቀራል። መጥፎውን ከደህናው፣ ምናልባት ጥቂት አዲስ ግምትን በነርሱ ላይ በማሣደር ያልፋል።

ሆኖም ግን ሊታረቁ የሚችሉ የማይመስሉትን ሁለቱን መስመሮች ሊያገናኛቸው እንደሚችል አንዳች ነገር ነገረው። አንዱም አቢሲኒያን የማየቱና ከዚያም ራሱን ታዋቂ አድርጎ ማቅረቡን ፈፅሞ ክዶ ይተወዋል። ወይም ደግሞ የማይደረስባትን አሊስ ዴ ማይሴን፣ በሁሉም የርሱነቱ የደም ሥር ሥሪት፣ እርሱን ለማስደሰትና ለርሱ ብቻ የተፈጠረች መሆንዋን ማመኑን ይክዳል።

እሾሃማው ፍሬ፣ ውሃ የሞላውና ጣፋጭ ነበር። በትንሹ ፍሬ ውስጥ ባለው ጠንካራ ዘርና የሚገመጠው ለስላሣ ሥጋው መካከል ያለው ንፅፅር አስደሰተው። እሾሁ ጨርሶ ተልጦ ስላልተወገደ ወጋው። የወጋው ደግሞ ፍሬው ጣፋጭ ስለሆነ ነው ሲል አሰበ።

አንዳንድ ጊዜ አንዳችም ፍቾ የሌላቸው ዐረፍተ ነገሮች በሃሣብ ባቡር ውስጥ ሥፍራ ይይዛሉ። ሊገልፀው ይገባው የነበረው፣ የበለሱ እሾህ፣ ጣፋጭን ፍሬ ከሚመኙት እንስሳት የሚከላከል ነው የሚል መሆን ነበረበት። ይሁን እንጂ አዕምሮውን አስጨንቆ የያዘው ፕሮብሌም ስላጃጃለው፣ ይህን እርስ በርሱ የሚጋጭ ሃሳብ እርሱ በሚገኝበት ሁኔታ ላይ አገለባብጦ እንዲያስበው አደረገው። በቀጥታ ራዕይ የታየው መስሎት ተደነቀ። ፍሬዎቹን ወረወራቸውና በትክክል ይኸው ነው ሲል አሰበ። በኔና በርስዋ መካከል ያልተለመደ ዓይነት እንቅፋት አለ። ይህን ማሸነፍና ድል ማድረግ የሚችለው ደግሞ ያልተለመደ ሁኔታ ነው። ካይሮ ውስጥ የምቀር ብሆን ኖሮ ፍፁም ላያት አልችልም ነበር፣ ፍፁም ላነጋግራትም አልችልም ነበር። በሁለታችንም መካከል አንዳችም ነገር ስኬታማ ሲሆን ከቶም አይችልም ነበር። ነገር ግን በሃላፊነት የተጣለብኝ ተልዕኮ፣ በታላቅ አደጋ ውስጥ የሚያቆየኝ ቢሆንም ምናልባት ታላቅ ድል አድራጊነትንም ያጐናፅፈኝ ይሆናል። እንደታሰበው ወደ አበሻ አገር እሄዳለሁ። ንጉሡን ከበሽታው አክሜ አድነዋለሁ። እንደተጠየቅሁትም ከአቢሲኒያ ኤምባሲ ጋር ተከትዬ እመለሣለሁ። እስከ ቬርሣይለስም አጅቤው እሄዳለሁ። ሉዊስ 14ኛም የክብር ዘቡችው ያደርጉኛል። ያን ጊዜ ሴት ልጁን ብጠይቀው፣ ቆንሲሉ ፈፅሞ እምቢ አይለኝም። ይኸው ነው። የዛሬ ተዋጊ እሾህ፣ ይዋጋል። ነገ ደግሞ ይመስገነው ለፈጣሪ፣ ጣፋጭ መዓዛው ይገኛል።

ወጣቱ ሰው ተነስቶ ቆመ። ለራሱ አንዳች ነገር እጉተመተመና ወደ አትክልት ሥፍራው መግቢያ በር በፍጥነት ተንደረደረ። በአዕምሮው ውስጥ የተፀነሰው ሰፊ ንድፍ መሠረት ስለያዘ ቀሪው ጉዳይ ያለብዙ ድካም መምጣት ይችላል። የተግባር እንቅስቃሴ ለማድረግ እቅድ አወጣ። በተለያዩ አቅጣጫዎች ገምግሞ በጣም ጥሩ መሆኑን አረጋገጠ። እስከ ፍፃሜውም ይህንኑ ሊያከናውን ማለ።

ሁሉም ነገር፣ በተለይም ሃላፊነት የተሰጠው ዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ በአዲስ መልክ ብሩህ ሆኖ ታየው። በመጀመሪያ ይህ ሁሉ ተግባር የፈረንሣዩን ንጉሥና የጳጳሱን ፍላጐት ብቻ ለማሟላት ነው ሲል አስቦ ነበር። እየዋለ እያደረ ግን የርሱንም ደስታ እውን ሊያደርግ እንደሚችል ተገነዘበ። ቀሪው ተግባርና ሥራ ሁሉ የሱ መሆን ጀመረ።



# 10

በአባይ ወንዝ ላይ በምትገኘው ቡላክ በተባለች የካይሮ ወደብ የሚገኙትን ጀልባ ቀዛፊዎች ሙሴ ማቼ ሲጠይቃቸው፣ ሁለት የካፑቺን መነኮሣት ከደለሉ ምድር ተነስተው በአንድ በተበላሸች ጀልባ ላይ ተሣፍረው ሽቅብ እየተጓዙ መሆናቸውን ተረዳ። እነዚህ ሰዎች አሁንም ከከተማዋ የሦስት ቀን ርቀት ላይ ናቸው። የመድረሣቸው ዜና አደጋ ያለበት ስለሆነ ከወዲሁ ዝግጅት እንዲከናወን የሚያነሣሣ ነበር። ቅፍለቱ ከሁለት ቀናት በኋላ በዕለተ ሰኞ እንዲንቀሣቀስ ተወስኗል። አንድ ቀን ቀደም ብሎ ሣምንታዊውን የቅዳሴ ፀሎት ሥርዓት አባ ዶ ብሬቬደንት ራሣቸው በቆንስላው ውስጥ ለማከናወን እንዲችሉ ቆንሲሉን ጠይቀውታል። እኒህን ካህን ሁልጊዜም እንደሠራተኛ መገመቱ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ቆንሲሉ የግል ስሜቱን እያንሀባረቀ ፈቀደ። ዋናውን የሀሉት ቤት ቢጠቀሙ የማህበሩ አባላት በሙሉ ሊካፈሉት የሚችሉበት ይሆናል። ይህ ደግሞ በምስጢር ሲጠበቅ የነበረውን እንቅስቃሴ ሁሉ ማወጅ ይሆናል። ስለዚህ ለተዳነርቼ የሚደረገው የፀሎት ሥነ-ስርዓት የንጉሡ የቅብ ስዕል ባለበት የእንግዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ ይሆናል። ከሙሲ ዱ ማይሌ ቤተሰብ ሌላ በዚህ ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙት አባ ጋብሪ፣ ሙሴ ማቼ፣ ሙሴ ፍሬሴንቲና ጆን ባፕቲስት ነበሩ። እንደተለመደው ጆን ባፕቲስት ለወጣቷ አሊስ ምንም ምልክት አልሰጣትም። ግን በጣም ረዥም ጊዜ የቆየ የመጨረሻ መተያየት አደረጉ። በዚህም ጊዜ ውስጥ እነበችው፣ እርስዋኑ እስኪደንቃት ድረስ ውስጧ ተደሰተ።

ቆንሲሉ፣ ስለ ወጣቱ ሐኪም ባህርይ ግዴለሽ ቢሆንም፣ በጣም መሠረታዊ ስለሆነው የቤተክርስቲያን ሥርዓት ግን ምንም ዕውቀት እንደሌለው አስተውሎታል። ይህ አነስተኛ ማስረጃ፣ ግለሰቡ አሣፋሪ የሃይማኖት ክህደት በውስጡ እንዳለው አረጋገጠለት።

ሥነሥርዓቱ ከተከናወነ በኋላ ቀጥሎ በሚገኘው የሣሎን ክፍል ውስጥ ቀላል ቁርስ ቀረበ። እንኳን ደስ አለን! የምስራች! ተባባሉ። በዚህ ሰዓት ጆን ባፕቲስት፣ ቆንሲሉን ለመጨረሻ ጊዜ የግል ጉዳዩን በተመለከተ ሊያነጋግረው ፈቃድ ጠየቀው።

«በል እንግዲህ ንገረኝ። ምንድነው?» አለው ቆንሲሉ ብቻቸውን በሆኑበት ጊዜ፣ ትዕግስት በማጣት

«ክቡር ሆይ፣ እኔ ከዚህ ከወጣሁ በኋላ ጓደኛዬ ካይሮ ውስጥ ሊቀር እንደማይችል አውቃለሁ። እርሱ የሚያዘጋጃቸው ፍቱን መድሃኒቶች ሁሉ የሚቀመሙት በኔ መመሪያ መሠረት ብቻ ነው። ብቻውን አንዳችም ነገር መሥራት አይችልም። ስለዚህ፣ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን አብሮት እንዲሰራ የሚፈልግ አንድ መድሃኒት አዋቂ፣ ወደ አሌክሣንደሪያ እንዲመለስ ጠይቆታል።»

«ደህና፣ እኔ ደግሞ ልጠይቅህ፣ ይህ ጉዳይ እኔን ምን ይመለከተኛል?» አለ ሙሴ ዱ ማይሌ

«ወደዚያው እያመራሁ ነው። የዚህ የሥራ ባልደረባዬ ወደ አሌክሣንደሪያ መሄድ ጊዜያዊ ነው። እኔ ከአቢሲኒያ ስመለስ . . . »

ቆንሲሉ አይኖቹን ሰበራቸው

«. . . አዎን» ሲል ጀን ባፕቲስት ንግግሩን በቁርጠኛ ድምፅ ቀጠለ። «እኔ ከአቢሲኒያ ስመለስ፣ ሜትር ዠረሚ ወደ ካይሮ ተመልሶ ሥራችንን በጋራ እንቀጥላለን»

«ድንቅ ሃሳብ ነው»

«የዚህ ውጤቱ . . . »

«የዚህ ውጤቱ?»

«መኖሪያችንን እንዳለ ትተነው ነው የምንሄደው»

«በዚህ ላይ ምንም ችግር አይታየኝም። ስለኪራዩም ከሆነ ራስህን አታስጨንቅ» አለ ቆንሲሉ፣ ፖንሴ ወዴት እያመራ መሆኑን በሚገባ ሲያውቅ።

«ባቀረብኩት የወጭ ዝርዝር ውስጥ የአንድ ዓመት ኪራይ አስቤ ነው የሠራሁት። እኔ የምለው ጉዳይ ግን ሌላ ነው»



«ታዲያ ሁሉም ነገር ተከናውኗላ?»

«የለም» አለ ፖንሴ፣ ሁለት ጊዜ በትንሿ ክፍል ውስጥ ዞር ዞር አለና በማስፈራራት መልክ፣ በቆንሲሉ ላይ እንደሚከመርበት ዓይነት ፊት ለፊቱ አፍጥጦ ቆመ። ፖንሴ፣ ከአንገቱ በላይ ከቆንሲሉ ይረዝማል «ቤቱ ምንም ማለት አይደለም። በውስጡ የያዛቸው ዕቃዎች ግን እጅግ በጣም ጠቃሚዎች ናቸው። በርግጥ ብዙ አይደሉም እንጂ እቃዎቻችን በሙሉ እዚያው ናቸው። ነገር ግን ጨርሶ በዋጋ ሲተመኑ የማይችሉ እጅግ ከፍተኛ ትዕግስትና ጥንቃቄ ወስደን ባለፉት ዓመታት ያዳቀልናቸው ብዙ ልዩ ልዩ ዕፅዋት አሉ። እነርሱ መጥፋት የለባቸውም»

«አሽከሮቹ ውሃ እንዲያጠጧቸው ትዕዛዝ መስጠት የሚኖርብኝ ይመስለኛል»

«ውሃ እንዲያጠጧቸው! አሽከሮችም! ስለነዚህ ነገሮች ለመሆኑ ምን ያህል ያውቃሉ ጌታዬ!» አለ ፖንሴ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ በልጥጦ እያንከባለላቸው። «እንዲያው ያስቡት፣ ማንም አላዋቂ ሰው በማንኛውም አሣቻ ሰዓት እየመጣ ጥቂት ውሃ እያፈሰሰና እየረጨባቸው፣ እነዚህን የመሰሉ ሃብቶችን በርግጥ በሕይወት ያቆያቸዋል ብለው ያምናሉ?»

«ስገምተው አዎን፣ እንደዚያ ብዬ አምናለሁ» ሲል ቆንሲሉ ተንተባተበ

«የለም፣ እንደዚህስ አይደለም» ሲል ፖንሴ በሃይል ተናገረ። «እዩ የሚከፈለንም በዚሁ መጠን ነው። ምክንያቱም ስለዚህ አስገራሚ የዕፅዋትና የአዝርዕት ዓለም ሁሉንም ነገር በሚገባ ማወቅ ይኖርብናል። ከዚህ ቀጥሎ ያለው የሰው ልጆች ተንከል፣ በሣቅ የሚታለፍ ቀላ ነገር ነው። እነዚህን ዕፅዋት በተገቢው ሥርዓት ለማልማትና ለማሣደግ የነበረውን የትዕግስት መጠን፣ ጥልቀትና የስሜት ብርታት የሚገነዘቡ አይመስለኝም። ዕፅዋቱ በተፈጥሮ እንዱ ለሌላኛው ጠላት ነው»

በአንድ ትምህርታዊ ርዕስ ጉዳይ ላይ ተመስጦ ሲይዝ እንደሚያደርገው ሁሉ፣ ጀን ባፕቲስት ቃላቱን አበክሮ ሲናገራቸው፣ እጆቹን በሃይል ያወናጭፋቸዋል።

«ለምሣሌ አንድ የዕፅ ዘር፣ የሙቀት መጠኑ በጥቂት ዲግሪዎች ከፍ ቢል ሊሞት ይችላል። ይህን ሲያውቁ መስኖት በመክፈት ችግሩን የሚፈቱት ይመስልዎታል? ነገር ግን አይደለም። ይልቁንም መቅሰፍት ነው የሚሆንበት። ተክሉ በነፋስ ከተመታ በኋላ በማግስቱ ደርሰው ቢያዩት ጠውልጎና ሞቶ ያገኙታል»

የድምፁ ቃና የዕፅዋቱ ጉዳይ ምን ያህል አሣዛኝ እንደሆነ እንዲሰማ ሆኖ ተሰቀቀ። ሙሴ ማይሴ፣ አይኖቹን በድንጋጤ በሰጠጣቸው።

«ሴላም አለ» ሲል ጆን ባፕቲስት፣ የቆንሲሉ ውስጣዊ ስሜት እንዲቀሰቀስ ለማድረግ ሲል ቀጠለ። «ዕፁ የሚሰጡትን ውሃ በሙሉ ይመጥጣል። በዚህም ሳቢያ በውሃ ብዛት ቁንጣን ይይዘዋል። ቅጠሎቹ ያብጣሉ፣ ይፋፋሉ፣ ይወድላሉ። ከዚያም እስከ አፍ ጢሙ የሞላ የፍየል ስልቻ ይመስላሉ። በየዕለቱ አንዳንድ ባልዲ ውሃ ይደፋበታል። እርስዎ ከመንቃትዎና ከማጠቅዎ በፊት ተክሉ ውሃ የማይሻበት ወይም በድርቅ መቆየት የሚገባው ደረጃ ላይ ይደርሣል። ይህን የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ውጫዊ ምልክት የለም። በርግጥ ዓይን የማይገቡ ምልክቶች አሉ። ይህን ለማወቅ የተክሎችና ዕፅዋት ጥናት ባለሙያዎች ለዘመናት ደክመዋል። ከቀን ወደ ቀን፣ አንድ ብርጭቆ ውሃ በተክሉ ሥር ማፍሰስ ዕፁን ሙሉ በሙሉ ያበሰብሰዋል።ከዚህም ሌላ፣ ፈፅሞ የማይጣጣሙና አብረው መኖር የማይችሉ ዕፅዋት አሉ።እነዚህ ተለይተውና ተራርቀው መጠበቅ ይኖርባቸዋል። አለበለዚያ አንዱ ሌላውን በቅርንጫፎቹ ሃይል እያነቀው በመግደል ይበላዋል። ሰው ሲያስበው . . . »

«ገብቶኛል ብዬ አምናለሁ» ሲል ቆንሲሉ፣ ሌሎቹን ሰዎች ለመቀላቀል ካለው ፍላጎት በመነጨ አቋረጠው። «ይህን ሃላፊነት ማን ቢወስደው ትወዳለህ?»

«የተማረና በሚገባ ማንበብ የሚችል ሰው ቢሆን እሻለሁ። ምክንያቱም ሁሉንም ነገር ጽፈን አስቀምጠናል። እያንዳንዱን የዕፅ ዘር ከነሁኔታው፣ ከነመሠረቱ፣ ህመሙን፣ ረሃቡን፣ ጥማቱንና አተነፋፈሱን የሚገልፁ ማስታወሻዎች አሉን። ነገር ግን ይህ ብቻውን በቂ አይደለም። እንድን ተክል ሳይገድሉት የማይነኩት አንዳንድ ምሁራን አሉ። ምንም እንኳ ዕፅዋትን ለማወቅና ለመገንዘብ እኛ እጅግ ብዙ ጥረት ብናደርግም፣ እነርሱ ግን በተፈጥሮአቸው ገና ስንጠጋቸው ያውቁናል። ለምሣሌ፣ ማቹን በዚህ ሃላፊነት ላይ ቢያስቀምጡት ቤታችን በአንድ ሣምንት ውስጥ መቃብር ይሆናል»



«እና ማን ይሁን?» ሲል ቆንሲሉ ጠየቀ። የሚያቀርበውን ተመራጭ አልቀበልህም ሲለውና ሲሽማቀቅ ለማየት ጓጉቶ።

«አስቀድሜ እንደተናገርኩት ዕፅዋት አንዳንድ ሰዎች በሚያስተላልፏቸው ምልክቶች የሚስማማቸው መሆናቸውን የመለየት ሃይል አላቸው። እንዲህ ያሉ ሰዎችን እኛ የዕፅዋት ጥናት ተመራማሪዎችም ለይተን እናውቃቸዋለን። እዚህ፣ ተፈጥሮ ለዚህ ስጦታ መርጣ ያስቀመጠችው አንድ ሰው ብቻ አለ»

«መልካም፣ ቢያንስ አንድ ሰው መኖሩም ጥሩ ነው» አለ ጉዳዩን መቋጨት ያልቻለው ቆንሲል ትዕግስት እያጣ። «ስሙን ንገረኝና አሁኑኑ አዲሱን ሥራውን ላስታውቀው»

«ማዳሞዜል ዴ ማይሴ፣ የርስዎ ልጅ»

ይህን ፈንጂ ካቀበለው በኋላ፣ ጆንሴ ሁለት እርምጃ ወደ ኋላ ተራምዶ ጠበቀ። ቆንሲሉ መናገር ተሳነው።

«የኔ ልጅ?» ሲል ክብሩን በመቀማቱ የተሰማውን ብስጭት በሚገልፅ ቃና «እሷማ፣ በዶሬሽዋ እንዲህ ካለ ሥራ ፍፁም በላይ ነች»

«ያሁን እንጂ ተፈጥሮ ይህን ችሎታ የሰጠችው ለርስዋ ነው»

«ህብረተሰቡ እስካልፈቀደው ድረስ ተፈጥሮ የሚፈቅደው ነገር ውጤቱ ደካማ ነው፣ ለማንኛውም ይህን ሃሣብህን ተወውና ሌላ ሰው እንድትፈልግ እጠይቅሃለሁ።»

«ለዚህ የሚሆኑ ሰዎች ጨርሰውንም የሉም»

«ያ ካልሆነ ተክሎችህ ይሞታሉ፣ እኛም ዋጋቸውን እንተካልሃለን»

«የገንዘብ ጉዳይ አይደለም» አለ ጆን ባፕቲስት ክስተር ብሎ፣ ሰላማዊ በሆነና መዘራፈጡት በሌለበት አኳኋን ወደ ቆንሲሉ ቀረብ ብሎ

«እባቴ እጅግ በጣም አሣሣቢ ስላልሆነ ነገር የተጠየቁ አድርገው ያስቡ። እኔና ሽሬኤ ዘሞር እንሄዳለ። ቤቱ እናውን ይቀራል። ልጅዎ፣ በትልቁ መደርደሪያ ላይ ሁለት

ትላልቅ የማስታወሻ ደብተሮች ታገኛለች። በዚያ ውስጥ ሁሉም ነገር በሳቲንኛ ተፅፏል። ዕፅዋት የሚፈልጉትን ርህሩህና አስደሣች ባህርይ በርስዋ ውስጥ በደመነፍስ ያገኙታል። ሌላው ሁሉ ከዚያ በኋላ ስለራሱ ይጨነቃል።»

«ጥያቄው ተዘግቷል ብዬ ስናገር፣ በዚያው ላይ ሙጭጭ እያልክ መሆንህ ይታየኛል። ልጁ ግን በምንም ሁኔታ አትሄድም»

«ይህ ከሆነ» ብሎ ጆን ባፕቲስት ቱግ አለ። «እኔም አልሄድም፣ በንጉሡ ደዌ ዙሪያ የሚያነፈንፍ ሌላ ሰው ሊፈልጉ ይችላሉ»

«ጌታው! እንዳች አክብሮት ቢኖርህ ይሻላል። የምትናገረው ስለ ንጉሠ ነገሥት ነው»

«አዎን፣ ስለ ንጉሡ ነገስቱና ስለ በሽታቸው፣ ስለመልካም መስተንግዶዎ ስል የተቀበልኩት እደራ ነው»

ጆን ባፕቲስት ከአንገቱ ዝቅ ካለ በኋላ በሩን ከፈተው።

«ፖንሴ» አለ ቆንሲሉ «ይበቃል፣ ሲበዛም ማር ይመራል። ማስፈራራትህ ከመጠን እያለፈ ነው። በሩን ዝጋውና አዳምጠኝ»

ሐኪሙ ከበር ላይ አልተንቀሣቀሰም

«ለአንድ ሣምንት ሙሉ፣ እያንዳንዱን ፍላጐትህን እንድናሟላልህ ግራ ስታጋባን ቆይተሃል። ሁሉም ነገር ደግሞ መጠን አለው። እንዲያው ከልቤ ልንገርህና፣ ካቀረብክልኝ ሃሣብ በስተቀር፣ ስለቤትህ የምትሻውን ዓይነት ማደራጀት ማድረግ ትችላለህ። ያ ሃሣብህ ግን የማይሆን ነው። ከዚህ በኋላ ወደ አቢሲኒያ ትንቀሣቀሣለህ። አለበለዚያ . . . »

«አለበለዚያ ምን?»

«አለበለዚያ እሁኑኑ እንድትታሰር አደርግሃለሁ። በዚህ ከተማ ውስጥ በሚገኙ የአገራችን ዜጐች ላይ ያለኝ ሥልጣን ፍፁም ነው። ይህን ስጠቀም ደግሞ አንዳችም ርህራሄ አላደርግም»



«ታዲያ ለምን አሁኑኑ እንድታሰር አያደርጉትም?»

«አትገፋፋኝ!» ሲል ቆንሲሉ ጮኸ

ፖንሴ፣ እጆቹን ለካቴናው እንደዘረጋቸው ናቸው

«ምንድነው የሚጠብቁት?»

የከርከራቸው ድምፅ፣ ሙሴ ማቹንና አባ ዱ ብሬቬደንትን ስላሳሰባቸው፣ ጣልቃ ገብተው ሁለቱንም አቀዘቀዟቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፖንሴ ወደ ቤቱ ሄደ። ያቀረበው ሃሣብ የፀና መሆኑንና ዲፕሎማቱ ግን ለሲቱን ሙሉ ሲያስቡበት ሲያድሩ እንደሚችሉ ከመሰናበቱ በፊት ነገረው።

ሙሴ ዱ ማይሌ፣ በዚህ የመጨረሻ ግጭት ተፈታ። ያጋጠመውን ችግር ለፀሃፊው ወይም ለጁስዊቱ ወርውሮላቸው ወደ ክፍሉ ሄደ። ዕረፍት ለማድረግም አሻፈረኝ አለ። ባለቤቱ ወዲያውኑ ደረሰችና አልጋው ላይ ተንጋሎሉ፣ ጭንቅላቱ በሁለት ትራሶች ተደግፎ፣ ተዘርግቶ ስታየው ተጨነቀች። ትንሽ እርዳታ ሲያገኝ፣ ወጣቱ ሰው ያቀረበው ሃሣብ ለንዴቱ ሰበብ እንደሆነ ተነፈሰላት።

ማዳም ዱ ማይሌ፣ የክብር ወይዘሮ መሆንዋ አጠራጣሪ አይደለም። ከታላቅ ቤተሰብ መወለዷን ልክ ባለቤቷ የሚከራበትን ያህል እርሷም ትከራበታለች። ይሁን እንጂ በጣም አስፈላጊ ከሆነውና ተጨማሪ ከሆነው የቱ እንደሚሻል በመለየት ረገድ ሴቶች ከወንዶች ብዙውን ጊዜ የተሻሉ ናቸው። በእርጋታና በብዙ ብልሃት፣ የፖንሴን የመጨረሻውን ጥያቄ ከመቃወም ይልቅ ቢስማማና ቢቀበለው ፍላጐቱ ብዙም እንደማይጐዳ ነገረችው። መድሃኒት ቀማሚው የማይሄድ ከሆነ ቆንሲሉን እቤቱ ድረስ እየመጣ መፈለጉ ግን አይቀርም። ይህን ተከትሎ የሚመጣው ውስብስብ ሁኔታ የቆንሲሉን ጤንነት ያቃውሰዋል። ሆኖም ግን፣ ሙሴ ማይሌ ሃሣቡን ቢቀበለው ችግሩ በጣም አነስተኛ ይሆናል ወይም እስከነአካቴውም ይጠፋል።

«በርግጥ በዕፅዋትና በመፃህፍት የተሞላ መሆኑን ማንም ቢያውቀውም ቤቱ ባዶ ይሆናል። አሊስን ከአባ ጋቦሬ ጋር ወደ ቦታው እየላክናት፣ ዕፅዋት አጥኚ እንደሆነች

በቅድሚያ ቢነገር ሌላ ነገር የሚያስብ ሰው የለም። ለልጃችንም፣ ትንሽ ትንሽ ወጣ ማለት ይጠቅማታል። በዚያውም አካላዊ እንቅስቃሴ ታደርጋለች»

«ይህ እርኩሱ፣ እንዲያውስ በመጀመሪያ ደረጃ እንዴት ሊያስተውላት ቻለ?» አለ ድንገት ከተኛበት ደንብሮ በመቀመጥ። «በዚህ ቤት ውስጥ ምስጢራዊ ግንኙነት ፈፅመው ሊሆን ይችላል?»

«እንግዲህ ይህን ስታመነኝርክ አትዋል። ምን ጣጣ ነው? ልጃችን ጠንካራ ተፈጥሮአዊ ትህትና እንዳላት እኔ እናቷ እመሰክርላታለሁ። ሰወዬው ያነጋገራት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ለዚያውም እኔ በቦታው ነበርኩ።»

በትንሿ የአትክልት ሥፍራ የነበረውን ሁኔታ በአጭሩ አስታወሰችው።

«አዎም» ስትል ማዳም ዴ ማይሌ ቀጠለች። «ስለዕፀዋት አበቃቀል ያላትን ዝንባሌ ያወቀው ያን ጊዜ ነው። ሰውዬው ትክክል መሆኑን ላረጋግጥልህ እችላለሁ። በአትክልት ማብቀያ ውስጥ ከማበቅላቸው ትንንሽ ዕፅዋት መካከል በሙቀት ወይም በድርቁ ምክንያት ሽምድምድ የሚል ካለ ሁሌም ለእሊስ እሰጣታለሁ። ወደ ክፍሏ ትወስደውና ከጥቂት ቀናት በኋላ አረንጓዴና ጤነኛ ሆኖ መልሳ ትሰጠኛለች።»

ማዳም ዴ ማይሌ፣ በጥሩ ሁኔታ ተከራክራ ባሏን አሳመነችው። ፖንሴ፣ ከጉዞው የመመለስ እድል አይኖረውም ሲል ለራሱ አሰበ። የሰውዬው ሃሣብ ክብር የጐደለውና ሕገወጥ ዕቅድ ቢሆንም፣ ይህን ለማስፈፀም ግን ለምንጊዜውም ዕድሉ አይኖረውም። ይህን የመጨረሻ እንቅፋት በድል በመወጣቱ ሰላምና እርካታ አገኘ። ምንም እንኳ ለዚህ ሁሉ የርሱ ድርሻ ቢኖርበትም፣ ቆንሲሉ፣ ንቢያዋ አሽከሩን በጣም ተራ ማስታወሻ አስይዞ ላከው። «ልጄ፣ ከአባ ጋቦሬ ጋር ሆና ሁልጊዜ ማለዳ በቤትህ ተገኝታ እፅዋትህን ታጠናለች። አሁን ሂድ»



# 2

# ጉዞ ወደ አበሻ ሃገር